# እስቲ ምላስህ!

ዶ/ር መለሰ ወጉ

# እስቲ ምላስህ!

*"Estee Milassih!"*

"Show me your tongue!"

የመጀመሪያ እትም፤ ግንቦት ፲፱፻፺፯ ዓ.ም.
First Edition, May 2004

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት ከመጀመሪያውና ከሁለተኛው እትም የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱሶች ነው።

ይህን መጽሐፍ በከፊልም ይሁን በሙሉ በማንኛውም ዓይነት መንገድ ለማባዛት፥ በቅድሚያ ከኢትዮጵውያን የወንጌል አገልግሎት ዋና ጽሕፈት ቤት የጽሑፍ ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል።

Copyright © 2004 by Ethiopian Outreach Ministry
All rights reserved. No part of this book may be reproduced in any manner without written permission from Ethiopian Outreach Ministry except in the case of brief quotations in critical articles and reviews.

Produced by:

Ethiopian Outreach Ministry
P.O.Box 2241
York, PA 17405
United States of America

http://www.ethiopianoutreach.com

Ethiopia Office Address:
P.O.Box 7888, Addis Ababa, Ethiopia.

Printed in Ethiopia

## ማውጫ

ገጽ

መግቢያ..... 4

ምዕራፍ~~

1~ ምላስ፥ ውስጥን የሚያሳይ መስታወት..... 9

2~ መልካም ምላስ..... 33

3~ ክፉ ምላስ..... 52

4~ ነቃፊ ምላስ..... 71

5~ አሉባልተኛ/ሐሜተኛ ምላስ..... 94

6~ ተሳዳቢ ምላስ..... 117

7~ ውሸተኛ ምላስ..... 141

8~ ትዕቢተኛ ምላስ..... 162

9~ ሰሚ ያጣ ምላስ..... 185

10~ ምላሳችን ቀዶ ሕክምና ያስፈልገው ይሆን?..... 202

# መግቢያ

አንድ ጊዜ በአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በክርስቲያኖች መካከል የነበረውን ትግልና ግጭት የተመለከተች አንዲት ክርስቲያን እህት፥ *"የችግራችን ሕንደኛውና ትልቁ ምክንያት ምላሳችን ነውና እባክህን መለሰ ምላሳችንን ዘይት እየቀባህ ጸልይልን"* አለችኝ። በሽተኛን ዘይት ቀብቶ መጸለይ የእግዚአብሔር ቃል የሚደግፈው መሆኑን ባምንም (ያዕ. 5፥14)፥ ምላስን ዘይት መቀባቱ ግን ስላልታየኝ፥ ጥያቄዋን ሰምቼ *"እሺም! እምቢም!"* ሳልል በፈገግታ አለፍኩት። ሰይጣን የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን ለመከፋፈል ከሚጠቀምባቸው ዘዴዎች መካከል አንደኛው የምላስ ጦርነቶችን በክርስቲያኖች መካከል በማካሄድ ነው። ክፉ ምላስ የእግዚአብሔርን አገልጋዮች ከአገልግሎታቸው በማፈናቀል የእግዚአብሔርን ሥራ እንዳበላሸ፣ ምዕመኑን እርስ በርስ፥ እንዲሁ ምዕመኑን ከሽማግሌው ጋር በማጋጨት ቤተ ክርስቲያንን እንደከፋፈለ፣ በቃል ኪዳን የተጋቡትን ባልና ሚስት በመለያየት ለብዙዎች የልብ ስብራት ምክንያት እንደሆነ የታወቀ ነው። ያለአግባብ ሌሎችን *መንቀፍና* መሳደብ፣ ከሰዎች በስ ተኋላ ክፉ ወሬ ማውራት፣ አሉባልታ ማስፋፋት፥ የሰይጣን ዓላማ እንዲፈጸም የእርሱ ተባባሪ መሆን ነው። ችግሩ ያለው "ምላስ" ላይ ሳይሆን፥ "ልብ" ላይ ነው። ጤናማ ከሆነ ልብ፥ ጤናማ የሆነ ንግግር ይፈልቃል። ልቡ ሲለወጥ፥ ንግግሩም ይለወጣል። ሰው ልቡ ካልተለወጠ ግን ምንም ያህል ጥንቃቄ ቢያደርግ፥ *"...አፉ የሚናገረው በልቡ ሞልቶ የተረፈውን"* (የማቴ. 12፥34) ስለሆነ፥ ከአፉ መልካም ንግግር አይወጣም። ስለዚህ ከፍተኛ የሆነ ቀዶ ጥገና የሚያስፈልገው "ምላስ" ሳይሆን "ልብ" ነው። ከላይ የጠቀስኳት እህት፥ በወቅቱ እንዳደርግ የጠየቀችኝን አላድርግ እንጂ፥ ክፉ ምላስ በሰዎች ሕይወት ውስጥ ሊያደርስ የሚችለውን ጥፋት ከምንጊዜውም የበለጠ እንዳስብበትና እንዲሁም በተለያየ መንገድ ክርስቲያኖችን እንዳስተምር፥ መነሻ ምክንያት ሆኖኛል። ለዚህ ነው በአሁኑ ጊዜ ይህን፥ *"እሰቲ ምላስህ"* የሚለውን መጽሐፍ አዘጋጅቼ ለአንባቢያን ያቀረብኩት።

እግዚአብሔር ለሰዎች ልጆች ከሰጣቸው መልካም ስጦታዎች መካከል አንደኛው ራስን በንግግር መግለጽ መቻል ነው። ሰው በውስጡ የሚሰማውን ደስታውንም ሆነ ሀዘኑን፥ በጠቅላላው በአዕምሮው ውስጥ የሚመላለሱትን አሳቦች በቃላት መግለጥ መቻሉ ትልቅ በረከት ነው። እግዚአብሔር ለሰው ምላስን የሰጠው ለበጎ ነገር እንዲጠቀም በት ቢሆንም፥ በምን ዓይነት ሁኔታ መጠቀም እንዳለበት ወሳኙ ሰው ራሱ ነው። ምላሱን በትክክል መጠቀምን ካልመረጠ፥ በራሱም ሆነ በሌሎች ሰዎች ሕይወት ውስጥ ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስ እንደሚችል የታወቀ ነው። ሐዋርያው ያዕቆብ ምላስ አነስተኛ ብልት ብትሆንም፥ ብርቱ ኃይል እንዳላትና ሌላውን መጉዳት እንደምትችል ይገልጸል (ያዕ. 3፥2-7)። በምላስ ከተጎዱት ሰዎች መካከል አንደኛው ኢዮብ ሲሆን፥ጉዳቱን ሲገልጽ፥ *"ነፍሴ የምታደቅቁኝ እስከ መቼ ነው?"* (ኢዮብ 19፥2) አለ። ክፉ ምላስ ያለው ሰው የሚጎዳው ሌሎችን ብቻ ሳይሆን፥ ራሱንም ጭምር ነው። ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ግንኙነት ያበላሽበታል፥ ከሰው ጋር በሰላም አያስኖረውም፥ እንዲሁም በሀሊና ክስ እንዲሰቃይ ምክንያት ይሆንበታል።

ምላስ፥ ውስጣዊ ሕይወታችንን የሚያሳይ መስታወት ነው። ሉቃስ የተባለው ጸሐፊ *"ምላሳችን የአዕምሯችንን አቋም ያመለክታል"* አለ። አንድ ሰው "ክርስቲያን ነኝ" እያለ ከአፉ የሚወጣው ሁልጊዜ ክፉ የሆነ ንግግር፣ ማንንም የማያንጽና የማይገነባ፣ እንዲሁም ጸጋን የማይሰጥ ከሆነ፥ ያ ሰው ክርስቲያንነቱ በጣም ያጠራጥራል። ምክንያቱም የእግዚአብሔር ቃል፥ *"ምላሱን ሳይቆጣጠር እግዚአብሔርን አመልካ ለሁ የሚል ሰው ራሱን ያታልላል፥ ሃይማኖቱም ከንቱ ነው"* ስለሚል ነው (ያዕ. 1፥26)። ያዕቆብ *"...አንደበትን ሊገራ ማንም ሰው አይች ልም"* (ያዕ. 3፥8) ሲል፥ በምላሱ የማይስት ማንም የለም ማለቱ ነው። በመንፈሳዊ ሕይወታችን ፍጹም ወደ መሆን እናድጋለን እንጂ፥ ገና ከፍጹምነት ደረጃ አልደረስንም። ስለዚህ፥ ክርስቲያኖችም ሆነን አልፎ አልፎ በምላሳችን የመሳት ዝንባሌ ስላለን፥ ዘማሪው *"እግዚአ ብሔር ሆይ! ለአፌ ጠባቂ አኑር በከንፈሮቼም በር ዘዘኛ አቁም"* (መዝ. 41፥3) ብሎ እንደ ጸለየው እኛም ለራሳችን መጸለይ ይገባናል።

ምላስ የማቋሰል ኃይል እንዳለው ሁሉ የመፈወስም ኃይል አለው። በሰዎች መልካም ምላስ ፈጽሞ አልተጠቀምኩም የሚል ማንም የለም። የደህንነትን መንገድ ያወቅነው፣ ከሚወደን ጌታ ጋር መተዋወቅ የቻልነው፣ መልካም ምላስ ያላቸው ሰዎች የምሥራቹን ቃል አሰምተውን ነው። የምንወዳቸው፥ እንደ ዓይናችን ብሌን የምናያቸው በሞት ተለይተውን ልባችን በሀዘን በተሞላበት ወቅት፥ አጠገባችን ተገኝተው

በሚያጽናና ቃል ያጽናኑን መልካም ምላስ ያላቸው ናቸው። በዓለም ውስጥ ያለው ትግል ሲያይልብን፣ ሰይጣን ትግሉን ሲያፋፍምብን፣ ሲጋችን ሲፈታተነን ተስፋ ቆርጠን መንፈሳዊ ጉዞአችንን አቋርጠን ወደ ኋላ ለመመለስ በቃጣንበት ወቅት በሰዓቱ ደርሰው "አይዞህ!/አይዞሽ! ሁሉም ያልፋል" በማለት ያበረታቱንና ልባችንን ቡተስፋ የሞሉት መልካም ምላስ ያላቸው ሰዎች ናቸው። ማወቅ ያለብን እውነት ቢኖር፥ ሳናስብና ሳንጠነቀቅ የምንናገረው ንግግር ሌላውን የሚጎዳ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፥ በመጪረሻው ቀን በእግዚአብሔር ፊት ስንቀርብ ከአፋችን ለወጣው ክፉ ቃል ተጠያቂዎች መሆናችንንም ጭምር ነው (የማቴ. 12፥36-37)። የእግዚአብሔር ቃል *"የምታገኘው በረከት የመልካም ንግግርህ ሥራ ውጤት ነው"* (ምሳሌ 12፥14) ስለሚል፥ ንግግራችን መልካም ከሆነ ደግሞ በሕይወታችን በረከትን እናገኛለን።

ክርስቲያኖችን ከዓለማውያን የተለዩ የሚያደርጋቸው መጽሐፍ ቅዱስ በማንበባቸው፣ ቤተ ክርስቲያን በመሄዳቸው፣ መንፈሳዊ መዝሙር በመዘመራቸው፣ አንዳንድ መንፈሳዊ ቋንቋ በመጠቀማቸው፣ መኪናቸው ላይ *"ኢየሱስ ያድናል!"* የሚለውን ጽሁፍ በመለጠፋቸው አይደለም። ተለይተው የሚታወቁት በሚኖሩት ዕለታዊ ኑሮ፥ እውነተኛ ማንነታቸውን በሚያሳየው ምላሳቸው ወይም ንግግራቸው ነው። ይሁን እንጂ አንዳንድ ክርስቲያኖች ንግግራቸው ከዓለማውያን የተለዩ መሆናቸውን አያሳይም። የስድብ ቃል ከአፋቸው የሚወጣ፥ የሌላውን ሰው ስም በክፉ እያነሱ የሚያሙ፣ አሉባልታ የሚያወሩ፣ የሚዋሹ፣ ራሳቸውን ከፍ፥ ሌላውን ዝቅ ለማድረግ ሲሉ ብቻ ሌላውን የሚነቅፉ፣ በሌላው ላይ የሚያደርሱት ጉዳት የማይሰማቸው ናቸው። *"ከዶ ከአፉችሁ ክፉ ቃል አይውጣ፥ ነገር ግን ለሚሰሙ ጸጋን የሚሰጥና ለማነጽ የሚጠቅም ለሰዎችም አስፈላጊ የሆነውን ቃል ተናገሩ"* (ኤፌ. 4፥29) ለሚለው ትዕዛዝ ግድ የሌላቸው፥ እንዲሁም ክፉ ቃል መናገር ኃጢአት የማይመስላቸው ናቸው።

ይህ መጽሐፍ ብዙ ጠቃሚ የሆኑ ፍሬ ነገሮችን ይዟል። ምላስ የሰውን እውነተኛ ማንነት እንዴት እንደሚያሳይ፥ እንዲሁም መልካም ምላስ ምን ዓይነት እንደሆነ በሰፊው ይገልጻል። ክፉ ምላስ፣ ነቃፊ ምላስ፣ አሉባልተኛ (ሐሜተኛ) ምላስ፣ ተሳዳቢ ምላስ፣ ውሸተኛና ትዕቢተኛ ምላስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ፣ በትዳርና እንዲሁም በማሕበራዊ ኑሮ ውስጥ የሚያመጣው ጉዳትና ችግር እንዲሁም መፍት ሄውን ጭምር ይጠቁማል። የሰዎች ማንነት የሚበላሸው በሚናገሩት



ንግግር ብቻ ሳይሆን፥ እርስ በርሳቸው መደማመጥ ካለመቻላቸውም የተነሳ በመሆኑ መደማመጥ የሚቻልባቸውን መንገዶች በመጠኑም ቢሆን ሀሳብ ይሰጣል። መለስተኛና ትላልቅ ቀዶ ጥገና የሚያስፈልጋቸው ምላሶች የትኞቹ እንደሆኑ፥ እንዲሁም ምላሳችን ሲፈወስ ምን ዓይነት ቃል ከአፋችን ሊወጣ እንደሚችል ይገልጻል። አንባቢዎች መጽሐፉን ሲያነቡ እንዳይሰለቻቸው፥ እንዲሁም ትምህርቱ የበለጠ እንዲገባቸውና ለማስታወስ እንዲረዳቸው በማሰብ፥ ከትምህርቱ ጋር የሚሄዱ አንዳንድ እውነተኛና ልብ ወለድ የሆኑ ታሪኮችን መጽሐፉ ይዟል።

ከዚህ በፊት አዘጋጅቼ ያቀረብኳቸው መጽሐፎቼ ሁሉ ምክንያት እንዳላቸው ሁሉ፥ ይህኛውንም መጽሐፍ የጻፍኩበት ምክንያት አለኝ። መልካም ምላሳ ባላቸው ሰዎች በረከትን፥ እንዲሁም ክፉ ምላስ ባላቸው ሰዎች መራራ ጽዋን በሕይወቴ የጠጣሁባቸው ጊዜያት አሉ። *"አስቲ ምላስህ"* የሚለውን መጽሐፍ ለማዘጋጀት የተነሳሁበት ዋና ምክንያት፥ እኔን የጎዳኝ እንዳይጎዳቸው፥ እኔን የጠቀመኝ እንዲጠቅማቸው በማሰብ ለአንባቢዎቼ ጠቃሚ የሆነ አሳብ፥ እንዲሁም ምክርና ማስጠንቀቅያ ለመስጠት ነው። በምላሱ የማይሰት ማንም የለም። *ያዕቆብ ለዚህ ነው "...እኛ ሁላችን ብዙ ጊዜ እንሳሳታለን፥ በንግግሩ የማይሳሳት፤ እርሱ ሰውነቱን መቆጣጠር የሚችል ፍጹም ሰው ነው"* ያለው (ያዕ. 3፥2)። ጸሎቴና ምኞቴ "ራሴን መለወጥ አልችልም" ብለን ተስፋ ቆርጠን እንድንቀመጥ ሳይሆን፥ ዘማሪው *"እኔ በማደርገው ሁሉ እጠነቀቃለሁ፥ እንደበቴም ወደ ኃጢአት እንዲመራኝ አልፈቅድለትም፥ ክፉ ሰዎች ባሉበት ሥፍራ ምንም አልናገርም"* (መዝ. 39፥1) እንዳለው እንድንል ነው።

ይህንን መጽሐፍ ሳዘጋጅ በተለያየ መንገድ የረዱኝን፣ ከጎኔ የተሰለፉትን የአገልግሎት ባልደረባዎቼን፣ እንዲሁም እንቅልፋቸውን መስዋዕት አድርገው ጽሁፉን በማንበብና በማረም የረዱኝን፣ ጠቃሚ ምክርና አስተያየት የሰጡኝን ሁሉ ከልብ አመሰግናለሁ። ይህንን መጽሐፍ በቀና መንፈስ የሚያነቡት ሁሉ ጠቃሚ የሆነ ትምህርትና አሳብ እንዲያገኙበት ምኞቴና ጸሎቴ ነው።

መለሰ ወጉ

# ምዕራፍ ፭

# ምላስ፦ ውስጥን የሚያሳይ መስታወት

ሀኪሞች ታምሞ ለሕክምናና እንዲሁም ጠቅላላ የጤና ምርመራ ለማድረግ የመጣውን ሰው፥ አንዳንድ ጊዜ *"እስቲ ምላስህ! ኣኣኣ!... በል"* በማለት ምላሱን ሲመረምሩት እናያለን። ከልጅነት ዘመናችን ጀምሮ የምንሰማውና የምናየው ስለሆነ ለብዙዎቻችን ይህ አዲስ ነገር አይደለም። በተለይ ምግብም ሆነ ውሃ ሲውጡ የሚያማቸው ልጆችም ሆኑ አዋቂዎች፥ የግድ ምላሳቸውን በማውጣት በሐኪሙ መመርመር አለባቸው። አንዳንድ ልጆች ከፍርሃታቸው የተነሳ ትንሽ ነገር ምላሳ ቸውን ሲነካቸው በቀላሉ ስለሚያስመልሳቸው፥ ምላሳቸውን ለማውጣት ፈቃደኞች አይሆኑም። ይሁን እንጂ፥ በሽታቸው እንዲታወቅ የግድ ምላሳቸው በሀኪሞች መመርመር አለበት። ምላሱን እንዲያወጣ የሚ ጠየቀው ሰው ጉሮሮው ቆስሎ እንደሆነ ለማየት ብቻ ሳይሆን፥ ምላሱ ጠቅላላ የሰውየውን የጤንነት ይዞታ ወይም ሁኔታ የሚያመለክት በመሆኑ ነው። በመንፈሳዊው ኑሮም ልክ እንደዚሁ፥ ምላስ የውስጥን ሕይወት ያሳያል። ጌታ ኢየሱስ ይህን እውነት ሲናገር፥ *"ሰው በአፉ የሚናገረው በልቡ የተረፈውን ነው" (የማቴ. 12፥34)* አለ። ጠቢቡ ሰለሞን ደግሞ *"ውሃ እንደ መስተዋት ሆኖ ፊትህን እንደሚያሳይህ*

*አዕምሮህም እንደ መሰተዋት ሆኖ የራስህን ጠባይ መልሶ ያሳይሃ ል" (ምሳሌ 27፥19) ይላል።*

ምላስን መግታት የሁላችንም ትግል መሆኑን ያዕቆብ ሲያስረዳ *"...እኛ ሁላችንም በብዙ ነገር እንሰናከላለን፥ በቃል የማይሰናከል ማንም ቢኖር እርሱ ሲጋውን ሁሉ ደግሞ ሊገታ የሚችል ፍጹም ሰው ነው"* ይላል (ያዕቆብ 3፥2)። *"መሰናከል"* ማለት *"መደናቀፍ"* ማለት ነው። ሕጻናት መራመድ ሲጀምሩ፥ ጥቃቅኑ ነገር ሁሉ እያደናቀፋቸው በቀ ላሉ ይወድቃሉ። በዚህም ገና ያላደጉና ቀጥ ብለው መራመድ የማ ይችሉ መሆናቸውን እናውቃለን። ልክ እንደዚሁ በምላሱ የሚደና ቀፍ ወይም የሚሰናከል ክርስቲያንም፥ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ገና ያል በሰለ "ሕጻን ክርስቲያን" መሆኑን እንረዳለን። በምላሳችን ስንደናቀፍ ወድቀን የምንጎዳው እኛ ብቻ ሳንሆን በአካባቢያችን ያሉትም ሰዎች ናቸው። በምላስ መደናቀፍ ልማድ የሆነባቸው ወይም "ተፈጥሮዬ ነው" ብለው የተቀበሉት አንዳንድ ሰዎች አሉ። ራሳቸውን ለማረም ጥረት በማድረግ ፈንታ፥ ራሳቸውን ነጻ አድርገው፥ "በአካባቢያችን የምላስ አሰናካዮች ስላሉ ነው" በማለት ሌሎችን ምክንያት ያደር ጋሉ። ያዕቆብ *"...የማይሰናከል ቢኖር..."* ሲል፥ ማንኛውም ሰው ሊሰ ናከል እንደሚችል መግለጹ ነው። ንግግራችን አግባብ ያለውና የሌ ለው መሆኑ የሚለካው፥ አልፎ አልፎ በምንወረውራቸው መንፈሳዊ ቃላት ወይም የንግግር ምሁራን በሚያወጡት የንግግር ሥርዓተ-ሕግ ሳይሆን መለኪያችን መጽሐፍ ቅዱስ ነው። "...ፍጹም ሰው ነው" ሲል፥ "እንከን የማይገኝበት" ማለት ሳይሆን "የተሟላ" ወይም "የበሰለ" ማለት ነው። በእግዚአብሔር ቃል መሠረት "በንግግራችን መሰናከልን" ካላቆምን፥ በመንፈሳዊ ሕይወታችን ገና ያልበሰልን መሆናችን ነው። ያዕቆብ እንደገለጸው፥ ምላሳችንን መግታት ስንችል፥ የተቀረውን አካ ላችንን መግታት (መቆጣጠር) እንችላለን።

ሀኪሞች ታምሞ ለሕክምናና እንዲሁም ጠቅላላ የጤና ምርመራ ለማድረግ የመጣውን ሰው፥ አንዳንድ ጊዜ *"እሱቲ ምላስህ! ሉላላ!... በል"* በማለት ምላሱን ሲመረምሩት እናያለን። ከልጅነት ዘመናችን ጀምሮ የምንሰማውና የምናየው ስለሆነ ለብዙዎቻችን ይህ አዲስ ነገር ኔይደለም። በተለይ ምግብም ሆነ ዋሃ ሲውጡ የሚያማቸው ልጆችም ሆኑ አዋቂዎች፥ የግድ ምላሳቸውን በማውጣት በሀኪሙ መመርመር



አለባቸው። አንዳንድ ልጆች ከፍርሃታቸው የተነሳ ትንሽ ነገር ምላሳ ቸውን ሲነካቸው በቀላሉ ስለሚያስመልሱ ምላሳቸውን ለማውጣት ፈቃደኞች አይሆኑም። ይሁን እንጂ፥ በሽታቸው እንዲታወቅ የግድ ምላሳቸው በሀኪሞች መመርመር አለበት። ምላሱን እንዲያወጣ የሚ ጠየቀው ሰው ጉሮሮው ቆስሎ እንደሆነ ለማየት ብቻ ሳይሆን፥ ምላሱ ጠቅላላ የሰውየውን የጤንነት ይዞታ ወይም ሁኔታ የሚያመለክት በመሆኑ ነው። በመንፈሳዊው ኑሮም ልክ እንደዚህ ምላስ የውስጥን ሕይወት ያሳያል። ጌታ ኢየሱስ ይህን እንውነት ሲናገር፥

## 1. "ምላስ" የውስጥ ሰውነትን የሚያሳይ መስታወት ነው

ማንነታችን የሚታወቀው በፊታችን ቅርጽ፣ ባለን ቁመና፣ በለበ ስነው ልብስ ወይም ባለን ሀብትና ንብረት፣ በገቢያችን መጠን፣ በምንሠራው የሥራ ዓይነትና ደረጃ ብቻ ሳይሆን ምላሳችን በሚናገ ረው ንግግር ነው። *ሞሪስ ፊሽቤይን (Morris Fishbein) የሃንዲ ሆም የህክምና አማካሪ (The Handy Home Medical Adviser)* "ምላስ" የሰውን የጤንነት ሁኔታ እንዴት እንደሚያመለክት ከዚህ ቀጥሎ ያለውን መግለጫ ጽፏል።

> *"የደረቀ፥ እንዲሁም የጠቆረና ጸጉራማ የሆነ ምላስ ያለው ሰው፥ ጤናማ አለመሆኑን ያመለክታል። እርጥበት ያለው ወይም ንጹህ ምላስ ያለው ሰው ግን ጤነኛነቱን ያሳያል። ጤነኛ ሰው ምላሱን በቀስታም ሆነ በፍጥነት፥ በፈለገው አቅ ጣጫ ማንቃነቅ ይችላል። በጠና የታመመ፣ ራሱን የማያውቅ፣ ወይም በጣም የደከመ ሰው ምላሱን ማውጣት አይችልም። የተደናገጠ (nervous) ሰው ምላሱ ይንቀጠቀጣል። በአንድ ወገን ሰውነቱ የማይሰራ ሰው፥ የምላሱም አንዱ ወገን አይሠ ራም። የአዕምሮ ሕመም ያለበት ሰው ምላሱን እያቃጠለው በጣም ይሰቃያል። እንዲሁም ቫይታሚን የጎደለው ሰው፥ ምላሱን ያቃጥለዋል።"*

ሀኪሞች ምላሳችንን መርምረው ጤናማ መሆናችንን ወይም አለ መሆናችንን እንደሚያውቁት ሁሉ፥ ከአፋችን የሚወጣውን ቃል የሚሰማ ሁሉ፥ በመንፈሳዊ ሕይወታችን ያለንበትን ትክክለኛ አቋም ለይቶ ማወቅ ይችላል። ምላሳችን እንደ መስተዋት ውስጣዊውን

ሰውነታችንን ያሳያል። ለምሳሌ፥ በልባችን ውስጥ ከፍተኛ ሥፍራ ስለሰጠነው ወይም በጣም ስለምንወደው ነገር ብዙ ጊዜ እንደምናወራ የታወቀ ነው። ለምሳሌ ስለ እግር ኳስ ጨዋታ ብዙ የማወራ ከሆነ፥ የእግር ኳስ ጨዋታ የምወድ መሆኔ ይታወቃል። ብዙ ጊዜ የምንጠቀምባቸው ቃላት አስተሳሰባችንን፣ ስሜታችንን፣ እንዲሁም በአንዳንድ ሁኔታ ላይ ያለን አቋም ምን ዓይነት እንደሆነ ያመለክታሉ። ለምሳሌ ያገባ ሰው ሁል ጊዜ "እኛ" በማለት ፈንታ "እኔ" የሚል ከሆነ፥ በጋብቻ ላይ ስላለው አንድነት በደንብ ያልተረዳ ሰው መሆኑ ይታወቃል። ያንዱን ሰው ስም እያነሳ ሁልጊዜ መልካም ያልሆነ ነገር መናገር የሚያዘወትር ከሆነ፥ በውስጡ ለዚያ ሰው ጥላቻ እንዳለበት ያሳያል። እንዲሁም ክርስቲያን ሆኖ ስለ መንፈሳዊ ነገር መልካም የማያወራ ከሆነ፥ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ችግር ያለበት ሰው መሆኑን ማወቅ እንችላለን። በዚህ ዓይነት፥ ምላሳችን ውስጣዊ ሰውነታችን ምን እንደሚመስል፥ ምን ዓይነት አቋም ላይ እንዳለ ማወቅ ያስችለናል።

*ሰንዱና ወግደረስ*ትዳር መሥርተው የሚኖሩ ሁለቱም የተለያየ የተፈጥሮ ባሕሪ ያላቸው ባልና ሚስት ናቸው። *ወግደረስ* በጣም ዝምተኛ (introvert)፥ ብዙ ካልጎተጎቱት ከሰው ጋር በቀላሉ መነጋገር የማይወዱለት ሰው ሲሆኑ፥ *ሰንዱ* ግን በተፈጥሮዋ በቀላሉ ከሰው ጋር የመግባባት ባሕሪ (extrovert) ያላት፥ ብዙ መናገር የምትወድ ሴት ናት። ወግደረስ ለሚጠየቀው ጥያቄ ሁሉ በእርሱ ምትክ ሆና ጣልቃ እየገባች መልስ የምትሰጠው እርሷ ነች። ይህን የሚያይ፥ በደንብ የማያውቃቸው ሰው *"ወግደረስ መናገር አይችልም እንዴ? ለሚጠየቀው ጥያቄ ራሱ ለምን መልስ አይሰጥም?"* በማለት መታዘቡ አይቀርም። ቤታቸው እንግዳ ተጋብዞ ቢመጣ የሚያየው፥ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ድረስ ሰንዱ ብቻ ስታወራ ነው። ይሁን እንጂ፥ ብዙ የመናገር ጠባይዋ ወግደረስን ይህን ያህል ቅር አያሰኘውም ነበር። ሰንዱና ወግደረስ በተፈጥሮ ባሕሪያቸውI ወግደረስ ዝምተኛ፥ ሰንዱ ተናጋሪ መሆኗ ጥሩ ትዳር እንዳይኖራቸው እንቅፋት ሊሆን አይችልም። "ዝምተኛ" የሆነ ሰው፥ ከተናጋሪ ሰው በጠበቀ የበለጠ፥ ወይንም ያነሰ ነው ማለት አይደለም። ሰንዱ ብዙ መናገሯ "ጥሩ" ወይም "መጥፎ"፥ እንዲሁም ወግደረስ ዝም በማለቱ "ጥሩ" ወይንም "መጥፎ" ሰው አያሰኛቸውም። ሁለቱም በተፈጥሮ ባሕሪያቸው የተለያዩ እን



ደሆኑ ገና ከመጋባታቸው በፊት አውቀው ልዩነታቸውን ተቀብለው ታል። ወግደረስ ስለ ሰንዱ ቅር የሚለው ነገር አለ። ያም ሰንዱ ብዙ መናገሯ ሳይሆን፥ የምትናገረውን መምረጥ አለመቻሏ ነው። ሰንዱ ብዙ ጊዜ በንግግሯ ስለ ወላጅ እናቱ መልካም ያልሆነ ነገር በመናገር ታስቀይመዋለች። እርግጥ ነው የወግደረስ እናት እንደማንኛውም ሰው የራሳቸው የሆነ ድካም አላቸው። ይሁን እንጂ፥ ይህን ያህል ተጋኖ የሚወራ ድካም አይደለም። ሰንዱ ስለ እናቱ ሁልጊዜ የምትሰጠው አስተያየትና ነቀፋ ወግደረስን በጣም ቅር ያሰኘው ነበር። ይሁን እንጂ፥ ጭቅጭቅ ያስነሳል ብሎ ስለሚፈራ የሚሰማውን የልቡን ቅሬታ አይነግራትም ነበር። ለጊዜው የሚሰማውን ስሜት ደብቆ መኖር ቢችልም፥ በሰንዱ ላይ ያለው ቅሬታ ከጊዜ ወደ ጊዜ መጨመሩ ያሳስበው ነበር።

ወግደረስ ብቻ ሳይሆን፥ ሰንዱም በወግደረስ ላይ የራሷ የሆነ ቅሬታ አላት። ሰንዱ ወግደረስ ዝምተኛ ሰው መሆኑን ታውቃለች። ቅር የሚያሰኛት ወይንም የሚያበሳጫት ያ አይደለም። ብዙ ባይናገርም "እወድሻለሁ!" የሚለው ቃል ከአፉ ለምን አይወጣም? ባይወደኝ ይሆናል ብላ ሁልጊዜ ታዝናለች። ይህን ነጥብ ብዙ ጊዜ እንስታበሰፈው ተወያይተውበታል። ይሁን እንጂ፥ የሚያረካትን መልስ አላገኘችም። *"ያገባሁሽ ወድጀሽ ነው። አሳቤን ስለውጥ ብቻ እነግርሻለሁ። ሁልጊዜ 'እወድሻለሁ' ማለት አለብኝ እንዴ? እኔ ሚስቶቻቸውን ሁልጊዜ 'እወድሻለሁ' እንደሚሉት ፈረንጆች አይደለሁም። እኔ ኢትዮጵያዊ ወንድ ነኝ"* ይላታል። ይህን ሲላት *"ኢትዮጵያዊት ሴት 'እወድሻለሁ' መባል 'አትወደም' ያለህ ማን ነው?"* ትለዋለች። ማንኛዋም ሴት "እወድሻለሁ" የሚለውን የፍቅር መግለጫ ከባሏ መስማት እንደምትፈልገው ሁሉ፥ ሰንዱም ከባሏ በመፈለጓ "ጥያቄዋ አግባብ ያለው አይደለም" ማለት አንችልም። ወግደረስ በተፈጥሮው በልቡ ውስጥ ያለውን ሀሳብ፥ የሚሰማውን ስሜት መግለጽ የማይሆንለት ሰው እንደሆነ ገና ከመጋባታቸውም በፊት ሰንዱ ታውቃለች። ይሁን እንጂ፥ "እወድሻለሁ" ማለት ያቅተዋል ብላ አልገመተችም ነበር። ብዙ ጊዜ ይህን ነጥብ እያነሳች ወግደረስን መጨቅጨቋ ስለሰለቻት፥ ይህን ጥያቄ ማንሳቱን ትታለች። ታዲያ የወግደረስንና የሰንዱን ችግር እንዴት መፍታት እንችላለን? ወግደረስን *"ባሎች ሆይ! ሚስቶቻችሁን*

ውደዱ" ይላል ብለን ብንሰብክለት፥ "መች ጠላኋት?" ይለናል። ስን ዱንም "ከቶ ከአፋችሁ ክፉ ቃል አይውጣ" ይላል ብንላት፥ "የተናገርኩት እውነት ነው፥ እውነቱን ከተናገርኩ የእግዚአብሔርን ቃል አልጣስኩም" ትለናለች። የሰነ ልቦና አዋቂ አስመጥተን ሁኔታቸውን ካጠና በኋላ፥ "ወግደረስ ዝምተኛ የሆነው፥ በልጅነቱ ከአባቱ ፍቅር ሳያገኝ በማደጉ ነው፥ ስንዱም ሁልጊዜ የምታጉረመርመው፥ የዝቅ ተኛነት ስሜት፡ ስለሚያጠቃት ነው" ቢላቸው፥ ይሄ ችግራቸውን ሊያቃልል ይችላል ብለን እናምንም።

የሁለቱም ችግር የተመሠረተው በሌላ ነገር ላይ ሳይሆን "ከንግግራቸው" ላይ ነው። ወግደረስ በዝምተኛነቱ፥ ስንዱ ደግሞ ብዙ በመናገሯ ነው። ችግራቸውን መፍታት የሚችሉት፥ ሁለቱም እርስ በርሳቸው በአግባቡ መነጋገር የቻሉ እንደሆነ ነው። ስንዱ "ከቶ ከአ ፋችሁ ክፉ ቃል አይውጣ፥ ነገር ግን ለሚሰሙት ጸጋን የሚሰጥና ለማነጽ የሚጠቅም ለሰዎችም አስፈላጊ የሆነውን ቃል ተናገሩ" (ኤፌ. 4፥29) በሚለው ቃል ራሷን መምራት አለባት። ስለ ወግደረስ እናት ክፉ ቃል መናገር ጸጋን የማይሰጥ፥ ለማነጽ የማይጠቅም መሆኑን ተረድታ ራሷን መግታት አለባት። ወግደረስም፥ "ጥሩውን ቃል በተገቢው ቦታ መናገር እጅግ ያስደስታል" (ምሳሌ 15፥23) የሚለ ውን ቃል መመሪያ አድርጎ በመቀበል በጎ ቃል ከአፉ እንዲወጣ ራሱን ማለማመድ አለበት። የብዙዎች ትዳር የሚበላሽበት፥ ወይንም የሚ ፈርስበት ምክንያት አንደኛውና ትልቁ፥ "ከአፋቸው በሚወጣው ክፉ ቃል" ነው። ከሰዎች አፍ የሚወጣው ቃል ጎጂ ብቻ ሳይሆን፥ ጠቃ ሚም ሊሆን እንደሚችል የታወቀ ነው። ለእርስ በርሳችን ገንቢ የሆነ ንግግር ለመነጋገር፥ የልባችን ሁኔታ ወሳኝ ነው። ማንነታችን ወይም ውስጣዊው ሰውነታችን እንዳይታወቅ ተጠንቅቀን በመናገር ሌሎችን ለማሳሳት ብንሞክርም እንኳ፥ ምላሳችን አንድ ቀን እውነተኛውን እኛነ ታችንን መግለጹ አይቀርም። ኢየሱስ "...ሰው በአፉ የሚናገረው በልቡ ሞልቶ የተረፈውን ነው" አለ (ማቴ. 12፥34)። መጽሐፈ ምሳሌም የክፉም ሆነ የደግ ቃል ምንጩ "የሰው ልብ" እንደሆነ ይገ ልጻል። "...ክፉት በልቡ ላለ ፍቅርን የሚናገር ከንፈር..."(ምሳሌ 26፥23)፥ እንዲሁም ምሳሌ 23፥15 "...ልብህ ጠቢብ ቢሆን...ከንፈሮች ህም በቅን ቢናገሩ..." ሲል፥ ንግግራችን ከልባችን ሁኔታ ጋር የተያያዘ



መሆኑን ያሳየናል። ስለሆነም፥ ንግግራችን ጸጋን የሚሰጥ እንዲሆን ከተፈለገ፥ እውነተኛ የልብ መለወጥ እንዲኖረን ያስፈልጋል።

እግዚአብሔር ለሰዎች ልጆች ከሰጣቸው ልዩ ልዩ ስጦታዎች መካከል አንደኛው፥ ሰው በልቡ ውስጥ ያለውን አሳብ በቃላት መግ ለጥ እንዲችል ዕውቀትን፥ እንዲሁም መናገር የሚችል ጤናማ አካል የሰጠው መሆኑ ነው። ሰው ይህንን ታላቅ ስጦታ በአግባቡ ካልተጠ ቀመበት፥ በራሱም ሆነ በሌሎች ሰዎች ሕይወት ላይ ጉዳት ሊያደርስ እንደሚችል የታወቀ ነው። ይህንን ታላቅ ስጦታ በአግባቡ በመጠቀም ፈንታ፥ ተከራክሮ የራሱን ፍላጎት የሚያሟላበት፣ ራሱን ከፍ፣ ሌሎ ችን ግን የሚያሳንስበት፣ በማባበል ቃል ከሌሎች ጨምቆ የሚወስድ በት፣ መሣሪያ አድርጎ ሲጠቀምበት ይታያል። መልካም ምላስ የሰ ውን ሕይወት ማነጽ ብቻ ሳይሆን የፈውስና የደህንነትም ኃይል እን ዳለው መጽሐፍ ቅዱስ ያረጋግጥልናል። "የምትናገረው ሕይወትህን ሊያድን ወይም ሊያጠፋ ይችላል። ስለዚህ የንግግርህን ውጤት መቀ በል ይኖርብሃል" ይላል (ምሳሌ 18፥21)። እንዲሁም፥ "የደግ ሰው ንግግር የሕይወት ምንጭ ነው" ይላል (ምሳሌ 10፥11)። የደግ ሰው ንግግር የሕይወት ምንጭ ሲሆን፥ የክፉ ሰው ንግግር ግን በሌላው ላይ ጉዳትን የሚያመጣ ነው። "ጤናማ አነጋገር ሕይወትን ያሰገኛል፥ ተንኮል የተሞላበት አነጋገር ግን መንፈስን ይሰብራል" (ምሳሌ 15፥4) ይላል።

አንዲት እናት ልጇ እያለቀሰ ሲያስቸግራት ምርር ብሏት "ምነው ሞተህ ባረፍኩት" ብላ ተናገረች። ከጥቂት ቀናት በኋላ ያ ህጻን ልጅ አልጋው ላይ እንደተኛ ድንገት ሞቶ ተገኘ። የእናትየው አነጋገር ሕጻኑን ገደለው ማለት ባይሆንም፥ ብዙ ጊዜ ሰው በልቡ ውስጥ ያለ ውን ሀሳብ ወይም ፍላጎት በምላሱ የሚገልጽ መሆኑ ነው። "ሰው በአፉ የሚናገረው በልቡ የተረፈውን ነው" (የማቴ. 12፥34) የሚለው የእግዚአብሔር ቃል ይህንኑ ያረጋግጣል። ሰው በራሱ ጥረት ምላሱን ንጹህ ወይም ያማረ እንዲሆን ማድረግ አይችልም። ያ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው። እግዚአብሔር ኢሳያስን ለአገልግሎት ሲያዘጋጀው፥ የእ ግዚአብሔርን ቅዱስነት፥ ታላቅነትና ኃያልነትን እንዲያይ ራዕይ ተሰጠው (ኢሳ. 6፥1-4)። ኢሳያስ የእግዚአብሔርን አስደናቂ የሆነውን የክብሩን ነጸብራቅ ሲያይ፥ በእግዚአብሔር ፊት መቆም የማይገባው

ኃጢአተኛ ሰው መሆኑን ተገነዘበ። *"...እነሆ ከንፈሮቹ በረከሱበት ሕዝብ መካከል የምናር ከንፈሮቹ የረከሱብኝ ሰው ነኝ፥ የሠራዊት ጌታ የሆነ ንጉሡን እግዚአብሔርን በወይኖቹ አይቻለሁና መጥፋቴ ስለሆነ ወዮልኝ ለልሁ"* አለ (ኢሳ. 6፥5)። ምላሱ ንጹህ አለመሆኑን ሲገልጽ፥ ከመለአኩ አንዱ እየበረረ መጥቶ ከመሰውያው በወሰደው የእሳት ፍም ከንፈሮቹን አነከቶ *"እነሆ የእሳት ፍም ከንፈሮችህን ስለ ነካ በደልህ ተወግዶልሃል፥ ኃጢአትህም ይቅር ተብሎልሃል"* አለው (ኢሳ. 6፥7)። ከዚህ በኋላ ነው ኢሳያስ ለአገልግሎት መዘጋጀቱን አውቆ *"...እነሆ እኔ እሄዳለሁ፥ እኔን ላክኝ"* (ኢሳ. 6፥8) በማለት ራሱን ለአገልግሎት የሰጠው።

## 2. ምላስ ውስጣዊ ተንኮላችንን ያሳያል

ምላሳችን እውነተኛውን "ማንነታችንን" ያሳያል። መስኮት ለቤቱ ብርሃን መስጠት ብቻ ሳይሆን፥ ከውጪ ላለ ሰው እቤቱ ውስጥ ምንና ማን እንዳለ እንደሚያሳይ ሁሉ፥ አንደበትም ሰው ሀሳቡን የሚገልጽበት መሣሪያ ብቻ ሳይሆን፥ የተናጋሪውን ማንነት፣ ውስጣዊ ሰውነትና እንዲሁም ምን ዓይነት ባህሪ እንዳለው የሚያሳይ መስታወት ነው። አንድነታችን፥ ሕብረታችንና ፍቅራችን ምን ይመስላል? ዛሬ ሕብረታችን የምላሳችን ውጤት እንደሆነ እናውቅ ይሆን? ጤናማ ምላስ ካለን፥ እንቀራረባለን፥ እንያያዛለን፥ እንፋቀራለን። ጤናማ ምላስ ከሌለን ግን እንገፋተራለን፣ ሆድና ጀርባ እንሆናለን፣ እንከፋፈላለን፣ እንበታተናለን። የከፋ እንደሆነ እርስ በርሳችን እንነካከሳለን፥ እንጋደላለን።

*(1) "አንደበት" ተናጋሪው በአዕምሮው ምን ያህል እንደበሰለ ያመለክታል። "ከአዕምሮ የበሰሉ ሰዎች ቦግስተዋል ይናገራሉ" ይላል (ምሳሌ 10፥13)።*

*(2) አንደበት የሰውን ሞኝነት ያሳያል። መጽሐፍ ቅዱስ "ሐሜትን የሚያሰራጭ ሰው ሞኝ" ነው" ይላል (ምሳሌ 10፥18)።*

*(3) አንደበት የሰውን ግብዝነት ያሳያል። ነገርን አጋኖ፣ ከሆነው በላይ እንደሆነ አድርጎ የሚያወራ እንዲሁም ከሠራው በላይ እንደሠራ ራሱን አተልቆ የሚናገር፥ የተናገረው ነገር በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ እውነት አንኳን ቢሆን ንግግሩ የግብዝ ሰው ንግግር መሆኑ በቀላሉ ያስታውቃል። "አስተዋይ ሰዎች አዋቂዎች ነን እያሉ አይመጻደቁም፥ ሰነፎች ግን አዋቂዎች ነን በማለት ድንቁርናቸውን ይገልጣሉ" ይላል (ምሳሌ 12፥23)።*

*(4) አንደበት የሰውን ክፉትና ደግነት ያሳያል። በሌሎች ላይ የምን ሰጠው መጥፎ አስተያየት ማንነታችንን የሚያሳይ ብቻ ሳይሆን፥ ጎጂነትም አለው። "ክፉ ሰዎች ሌሎችን የሚጎዱበትን መንገድ ያስባሉ፥ ንግግራቸውም እንደ እሳት የሚያቃጥል ነው" ይላል (ምሳሌ 16፥27)። በሌላው ሰው ላይ የምንሰጠው አስተያየት ጎጂ ነት እንዳለው ሁሉ፥ መልካም ንግግራችንም ፈዋሽነት አለው።*

ምላስ የሰውን ማንነት የሚያሳይ መስታወት ስለሆነ፥ ምንም ያህል ቃላት እየመረጥን ጥሩ አስመስለን በመናገር ለጊዜው ሌሎችን ያሞኘን ቢመስለንም፥ እውነተኛውን ማንነታችንን የራሳችን ምላስ ይገልጠዋል። *"ከጋለሞታ ሴት ከንፈር ማር ይንጠባጠባልና፤ አፍዋም ከቅቤ የለሰለሰ ነውና፥ ፍጻሜዋ ግን እንደ እሬት የመረረ ነው"* ይላል (ምሳሌ 5፥3-4)። ጋለሞታ ሴት ለጊዜው በጥሩ ንግግሯ ማንነቷን ትሸፍነው እንጂ፥ አጥፊ ሴት እንደሆነች መታወቋ አይቀርም። ሼክስፒር በማስመሰል ንግግር ራስን መደበቅ የማይችል መሆኑን ሲገልጽ፥ *"ውስጣዊ ማንነቴን ለመደበቅ ብሞክር ምላሴ ይገልጸዋል፥ ባይገልጸው ግን ልቤ ምስጢሬን በመደበቁ ከሚጎቀት ብዛት ይፈነዳል"* አለ። የእግዚአብሔር ቃልም፥ *"ሰው በአፉ የሚናገረው በልቡ የተረፈውን ነው"* ይላል (የማቴ. 12፥34)። ሰው እንደ መልአክ ቢሰብክ፣ እንደ ማዘር ተሬሳ ያለውን ለድሆች ቢሰጥ፣ 24 ሰዓት ተንበርክኮ ቢጸልይ፣ በጾም ራሱን ቢያጎሳቁል፥ ከአፉ የሚወጣውን ቃል የማይቆጣጠር ከሆነ ግን በእግዚአብሔር ሚዛን ሲመዘን ቀሎ እንደሚገኝ ግልጽ ነው። ምላሳችን የልባችንን ተንኮልና ምናምንቴነታችንን እንደሚገልጽ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። *"ምናምንቴ ሰው ክፉትን ይምላል፥ በከንፈሩም የሚቃጠል እሳት አለ"* ይላል (ምሳሌ 16፥27)።

በባሏ ላይ ከፍተኛ ጥላቻ የነበራት ክሊቭላንድ ኩተማ፥ ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ የምትኖር አንዲት ሴት ነበረች። አንድ ቀን ባሏ ምርር ሲለው ቤቱን ትቶላት ወጣ። "ባሌ ጥሎኝ ሄደ" ብላ ከሰሰችው። የፍርድ ቤት ዳኛውም "ሚስትህን ጥለህ ሄደሃል ወይንስ አል

ሄድክም? ጥፋተኛ ነህ? አይደለህም?" ብሎ ጠየቀው። ሰውየውም "እውነት ነው ጌታዬ ሚስቴን ትቼ ሂጃለሁ። ይሁን እንጂ፥ ጥፋተኛ አይደለሁም። ጥዬ የሄድኩበት ጥሩ ምክንያት አለኝ። ሚስቴ አንድ ቀን ገቢያ ሂዳ አንድ በጣም አስቀያሚ የሆነ ውሻ ገዝታ መጣች። ያንንም ውሻ 'ከርስትና ማንሳት አለብኝ' ብላ ውሃ ውስጥ ነክራ አወጣችውና የከርስትና ሰም አመጣችለት። ያመጣችለትም፥ ካልጠፋ ሰም "አሌክስ" የሚለውን የእኔን ሰም ነው። እኔን ለማናደድ ስትፈልግ፥ ሁልጊዜ ቤት ውስጥ 'አሌክስ' ብላ ትጣራለች። እኔን የጠራችኝ እየ መሰለኝ እኔም ለጥሪዋ 'እመት!' ብዬ ስመልስላት፥ 'ዝም ብል! አንተን አልጠራሁህም፥ የጠራሁት ሌላውን እንስሳ ነው' ትለኛለች። በዚህ ሁኔታ ስድቧ ሲበዛብኝ ተበሳጭቼ 'ከሌላው አሌክስ ጋርሽ ማለትም ከውሻው ጋር ትኑር' ብዬ ቤቱን ትቼላት ወጣሁ" አለው። ዳኛውም ሴትዮዋ የልቧን ተንኮል በምላሷ የምትገልጽ ምናምንቴ ሴት መሆኗን ስለተረዳ፥ ለሰውየው ፈርዶ ፍቺውን አጽንቶ በነጻ አሰናበተው። መጽሐፍ ቅዱስ "ምናምንቴ ሰው ክፉትን ይምሳል፥ በከንፈሩም ሾሚ ቃጠል እሳት አለ" ያለው እንዲህ ዓይነቱን ነው።

## 3. ምላስ ውስጣዊ ውበታችንን ያሳያል

"አቤት! የእከሊት ቁንጅና ፍጹም ሌላ ነው! አፍንጫዋ፣ ጥር ሰጆ!፣ ከንፈሮቿ፣ ዓይኖቿ እንዴት ያምራሉ?" ብለን እናደንቃለን። ስለ ምላሷ ግን ምንም ዓይነት አስተያየት አንሰጥም። ለመሆኑ ስንቶቻችን ነን ጥዋት፥ ጥዋት ፊታችንን በመስታወት ስናይ ምላሳችንን አውጥተን፥ "ቆሽሿል" ብለን ጥርሳችንን በበብሩሽ እንደምንቦርሸው ምላሳችንን የምንቦርሸው? ወይም በሳሙና የምናጥበው? የምላሳችን አስቀያሚነት ወይም መቆሸሽና መሽተት ስንቶቻችንን አሳስቦን ያውቃል? ምላሳችንን ለማቆንጆት ገቢያ ሂደን ለምላሳችን የሚሆን ጌጣ ጌጥ ገዝተን እናውቃለን? ጸጉራችንን ለመሠራት፥ ጥፍሮቻችንን ለማስቀረጽ የቁንጅና ሳሎን እንደምንሄደው፥ ምላሳችን ረዝሞ እንደ ሆነ ለማሳጠር፣ የበለጠ ለማቆነጃጀት፣ በሳምንትም ሆነ በወር፥ ወይም በዓመት ሂደን እናውቃለን? ኤቨን እና ሬቭሎን የተባሉት ታዋቂ የቁንጅና ቅባት አቅራቢዎች ለምላስ የሚሆን ኮስሜቲክስ የላቸውም። ምላሳችን አመዳም እንዳይሆን የምንቀባው ቅባት፥ ወይም ወዛም



ሆኗል ብለን የምንቀባው ፓውደር አልተሠራለትም። ከንፈር እንዲያምር ቀለም ይቀባል፤ ጥርስ እንዳይንጋጠጥ ብዙ ብር ተከፍሎ በሽቦ ተጠፍሮ ይታሠራል፥ ቅንድብ ይላጫል፥ ቀለም ይቀባል፥ የዓይን ሽፋሽፍት በልዩ ልዩ ቀለም ያጌጣል፥ ለጆሮ ጉትቻ ይንጠለጠልለታል። ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ ለአፍንጫም ጉትቻ ማንጠልጠል ተጀምሯል። ለምላስ ግን ምንም አይደረግለትም። እርግጥ ነው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ጀምሮ በተለይ በምዕራቡ ዓለም ምላስም ላይ ቀለበትና የብረት ዘንግ ማድረግ እንደተጀመረ እናውቃለን። ያም ሆነ ይህ፥ ማወቅ የሚገባን እውነት ቢኖር፥ ሰውን ቆንጆ የሚያሰኘው የፊቱ ቅርጽ፣ ያለው ያማረ ቁመና ወይም የለበሰው ልብስ ሳይሆን፥ ውስጣዊ ሕይወቱን የሚያሳየው ምላሱ በሚናገረው ንግግር ነው። *"ሊዋሽ ምላስ የሕይወት ዛፍ ነው"* (ምሳሌ 15፥4) ይላል። ከአንደበቱ የሚወጣው ጠቃሚም ሆነ ጎጂ እንዲሆን ወሳኙ፥ ያ ሰው ያለው የልቡ አቋም ነው። ዊልያም ዊትመር የተባለው ጸሐፊ፥ *"በልቡ እውነትን የያዘ ሰው፥ ምላሴ ይሰት ይሆን? ብሎ አይፈራም"* አለ። መጽሐፍ ቅዱስም *"ክፉ ሰዎች ሌሎችን የሚጎዱበትን መንገድ ያስባሉ፥ ንግግራቸውም እንደ እሳት የሚያቃጥል ነው፥ ክፉ ሰዎች ሐሜት ያሰራጫሉ፥ ሁከትን በማነሳሳት ዐፍቅር የተሳሰሩትን ወዳጆች ይለያያሉ"* ይላል (ምሳሌ 16፥27-28)።

## 4. "ንግግራችን" ብቻ ሳይሆን "ዝምታችንም" አስፈላጊ የሚሆንበት ጊዜ አለ

ዝምታ "ወርቅ" መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። "ዝምታ" ሰው በኃይል ጮኾ ከሚገልጸው የበለጠ የልብን ሀሳብ በግልጽ የሚያሳይበት ጊዜ አለ። እየጮኸና እየደነፋ የሚሳደበውን ሰው በዝምታ ማለፍ፥ ለዚያ ተሳዳቢ ሰው ትልቅ መልዕክት ያስተላልፍለታል። ስድብን በስድብ በመመለስ ፈንታ ዝም ሲል፥ ሶተሳዳቢው *"እኔ እንደ አንተ ከአፈ ክፉ ቃል አይወጣም... በዚህም ማንነቴን አሳይሃለሁ፥ ራሴን መቆጣጠር እችላለሁ"* የሚል መልዕክት ማስተላለፉ ይሆናል። ተሳዳቢ ሰው፥ ተሰዳቢው መልስ ሳይሰጠው ዝም ከሚል ይልቅ ጮክ ብሎ መልሶ ቢሰድበው ደስ ይለው ነበር። "ለምን እንዲህ ብዬ ተሳደብኩ?" ብሎ በህሊና ጸጸትም አይጨነቅም ነበር። "በዝምታ" ተሰዳ

ቢው ተሳዳቢውን ማሸነፍ ይችላል። ይሁን እንጂ፥ "ዝምታ" ሁልጊዜ ወርቅ ነው ማለት አይደለም። "ዝም ማለት" እውነትን እንደመደበቅ የሚቆጠርበት ጊዜ አለ። ሰው በሚኖርበት ሕብረተሰብ ውስጥ፥ በቤቱና እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን አካባቢ ትክክል ያልሆነ ነገር በአንዳንድ ሰው ላይ ሲፈጸም እያየ፥ እውነቱን እያወቀ፥ በመፍራት ወይም "ለመኖር" ሲል ብቻ ዝም ቢል፥ እውነትን መደበቁ ይሆናል። እውነት ባልሆነ ምክንያት ጎጂ የሆነ ነገር በሌላው ሰው ላይ ሲሠራ በት፥ ያለአግባብ ሲፈረድበትና ሲተች ዝም ማለት፥ ውሸት ከሚያወ ሩት ጋር እንደመተባበር ነው።

ምላሳችንን በአግባቡ መጠቀማችንን የምናውቀው ጎጂ ያልሆነ ንግግር ባለመናገራችን ብቻ ሳይሆን፥ "ተገቢውን ቃል በተገቢው ቦታ መናገር" (ምሳሌ 15፥23) ስንችልም ነው። በመልካም አነጋገር የተ ሞላ አስተዋይ ሰው ከመናገሩ በፊት ያስባል፥ መቼ መናገር እንዳለ በት፥ መቼ ዝም ማለት እንዳለበት ያውቃል። ዳዊት *"እኔ በማደርገው ሁሉ እጠነቀቃለሁ፥ እንደበቴም ወደ ኃጢአት እንዲመራኝ አልፈቅ ድለትም፥ ክፉ ሰዎች ባሉበት ሥፍራ ምንም አልናገርም አለሁ"* ይላል (መዝ. 39፥1)። ዝምታን በሕይወቱ የተለማመደው ዳዊት *"ዝመ ኝታችሁ ሳላችሁ በልባችሁ አስቡ፥ ዝም በሉ"* ይላል (መዝ. 4፥4)። ሁከትና ረብሻ በበዛበት ዓለም ሰውን "ዝም በል" ማለት ከባድ ነው። አዋቂዎች እንደገለጹት፥ ሕጻን ልጅ ንግግር ለመማር ወይም ለመቻል አንድ ወይም ሁለት ዓመት ይፈጅበታል። በዕድሜ ከፍ ያለው ሰው ግን ዝም ለማለት 60 ወይም 70 ዓመት ይፈጅበታል ይላሉ። አንድ ጊዜ አንድ ወጣት ዝነኛው ፈላስፋ፥ ሶቅራጥስ "የንግግር ኪነ ጥበብ" እንዲያስተምረው ጠየቀው። ይሄ ወጣት በተፈጥሮው ብዙ መናገር የሚወድ ሰው መሆኑን ሶቅራጥስ ስለሚያውቅ፥ *"አንተን የማስከፍለህ ሌሎች ከሚከፍሉት እጥፍ ነው"* አለው። ወጣቱም በመደነቅ፥ *"እጥፍ የምታስከፍለኝ ምክንያቱ ምንድነው?"* ብሎ ጠየቀው። ሶቅራጥስም ሲመልስለት፥ *"ምክንያቱም አንተን የማስተምርህ ሁለት ዓይነት ሳይ ንስ ነው። አንደኛው ዝም ማለትን ሲሆን፥ ሁለተኛው ደግሞ የንግግር ኪነ ጥበብን ነው። የመጀመሪያው ከሁለተኛው የበለጠ ከባድ ነው"* አለው። መጽሐፍ ቅዱስ *"...ለዝምታ ጊዜ አለው፥ ለንግግርም ጊዜ አለው"* (መክብብ 3፥7) የሚለውን እውነት ባለመረዳት ዝም ማለት የሚያቅታቸው አንዳንድ ሰዎች አሉ።



ሠለሞን እንዳለው ዝም ለማለት ብቻ ሳይሆን *"ለመናገርም ጊዜ አለው።"* መናገር እየቻልን በአስፈላጊው ጊዜ አለመናገሩ፥ እግዚአብ ሔር በሰጠን ታላቅ ስጦታ አለመጠቀም ነው። ይሁን እንጂ፥ አንዳን ዶቻችን ምን ያህል እንደምንናገር፥ ምን ያህል ጊዜ ደግሞ ዝም እንደ ምንል የተረዳነው አንመስልም። አንድ መለስተኛ የሆነ ተናጋሪ ሰው ከጠቅላላ ዕድሜው ውስጥ አንድ አምስተኛውን (⅕) የሚያሳልፈው በመናገር እንደሆነ እናውቃለን። ይኸውም 75 ዓመት ዕድሜ ቢኖር፥ 15ቱን ዓመታት የሚያሳልፈው በመናገር ነው። በማንኛውም ተራ ቀን አንድ ሰው በቀን በአማካኝ 18,000 ቃላት ይናገራል። ንግግሩ በጽሑፍ ቢወጣ 54 ገጽ ይወጣዋል። በአንድ ዓመት ውስጥ የተና ገረው እያንዳንዱ 400 ገጽ ያለው 132 መጽሐፍት እንደሚወጣው አዋቂዎች ይናገራሉ። "ከዚህ ውስጥ ግን ምን ያህሉ የማይረባ፥ ሌላ ውን የሚጎዳ፥ መንፈሳዊ ሕይወታችንን የሚያጎድፍ ይሆን? ወይም ከዚህ ውስጥ ምን ያህሉ የሚጠቅምና ሌሎችን የሚያንጽ ይሆን?" ብለን እንጠይቅ ይሆን? አማኝ ማወቅ ያለበት እውነት ቢኖር፥ በዕድ ሜው ዘመን ሙሉ የተናገረው፥ አንድ ቀን በእግዚአብሔር ፊት የሚነበብ መሆኑ ነው። *"በእውነት እላችኋለሁ፥ ሰዎች በሚናገሩት ምንም ጥቅም በሌለው ከንቱ ቃል ሁሉ በፍርድ ቀን መልስ ይሰጡ በታል። ምክንያቱም ከቃልህ የተነሳ ይፈረድልሃል፥ ከቃልህም የተነሳ ይፈረድብሃል"* ይላል (የማቴ. 12፥36-37)።

ዝምታ ጠቃሚ የሚሆንበት ጊዜ እንዳለ ግልጽ ቢሆንም፥ "ዝም" ማለት ከባድ የሚሆንባቸው አንዳንድ ሰዎች አሉ። አንድ ጊዜ አን ዲት ብዙ መናገር የምትወድ ሴት ለምርመራ ሀኪሟ ዘንድ ሄደች። አንዴ መናገር ከጀመረች ማቆም የማትችል መሆኗን የሚያውቀው ሀኪሟ፥ ብዙ ጊዜ ሀኪሞች በሽተኞቸውን ሲመረምሩ እንደሚያደር ጉት፥ "እስቲ ምላስሽን አውጪ፥ አ! አ! በይ" አላት። ሴትዮዋም እንደታዘዘችው ምላሷን አወጣች። የሴትዮዋን ምላስ በመመርመር ፈንታ፥ መግዛት ያለባትን መድኃኒት መጻፍ ጀመረ። ጽፎ ከጨረሰ በኋላ "ይበቃል! አፍሽን ክደኚ። ይኸውልሽ ከፋርማሲ ይሄን መድሐ ኒት ግዢ" ብሎ የጻፈውን ወረቀት ሰጣት። ሴትዮዋም ተበሳጭታ "ዶክተር! ምላስሽን አውጪ አልኮኝ እንጂ፥ መቼ ምላሴን አየኸው? መቼ መረመርኸኝ?" አለችው። ሀኪሙም "አያስፈልግም፥ ምላስሽን

አውጪ ያልኩሽ፥ ወረቀቱን ጽፌ እስክጨርስ ድረስ ዝም እንድትይ ብዬ ነው" አላት። እንደዚች ሴት ዝም ማለት የሚያስቸግራቸው ሰዎች አጋጥመውናል። እንኳን ሰው እግዚአብሔርም ዝም የሚልበት ጊዜ እንዳለው እናውቃለን። መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ዝምታው የመሰከሩ ብዙዎች አሉ። ዕንባቆም *"አቤቱ! እስከ ስሮሽ የማትሰማው እስከ መቼ ነው?"* (ዕንባ. 1፥2) ብሎ ጠይቆታል። ኢዮብም *"እረ ተበደልሁ ብዬ ብጮሽ የሚሰማኝ አላገኘሁም"* (ኢዮብ 19፥7) ይላል። እንዲሁም ዳዊት *"አምላኬ! አምላኬ! ለምን ተውሽኝ? ለዕርዳታ በብርቱ በምጮኽበት ጊዜ ስለምን ከእኔ ራቅህ?"* (መዝ. 22፥1) ይላል። ይሄ ሁሉ የእግዚአብሔርን ዝምታ ያሳየናል።

እግዚአብሔር በዝምታ የሚያምን ይመስላል። ዝም እንዲሉ ካዘዛቸው ሰዎች መካከል አንደኛው ሕዝቅኤል ነው። *"...ወደ ቤትህ ሂድ፥ በርህንም ዘግተህ ተቀመጥ"* አለው (ሕዝ. 3፥24)። ሕዝቅኤል እግዚአብሔር ለአገልግሎት ሲጠራው "ይህን ዓይነት ትዕዛዝ ይሰጠኛል" ብሎ አልገመተም ነበር። ምናልባት ከንጉሥ ጋር ገበታ እየቆረሰ፥ በዓለም ታዋቂና ዝነኝ ሆኖ በክብር እንዳገለገለው እንደ ኢሳያስ፥ እንዲሁም በባቢሎን ግዛት ውስጥ ስልጣን ኖሮት ግስጋሴ ደር እንደቻለው እንደ ዳንኤል የሚያገለግል ሳይመስለው አልቀረም። እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲያደርግ የጠየቀው ግን፥ ሌላ ነገር ሳይሆን፥ በሩን ዘግቶ ዝም ብሎ እንዲቀመጥ ብቻ ነበር። ሕዝቅኤል ትዕዛዙ ባይገባውም፥ ሞኝነት ቢመስለውም፥ እግዚአብሔር እንዲያደርግ ያዘዘውን አደረገ። በሩን ዘግቶ ለብቻው ተቀመጠ። "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል" ብሎ ለሕዝቡ የሚያስተላልፈው መልዕክት አልተሰጠውም። እንዲያውም ምንም እንዳይናገር እግዚአብሔር ከልክሎት ነበር። *"ይህን ዐመጸኛ ሕዝብ ማስጠንቀቅ እንዳትችል አንደበትህ እንዲተሳሰር አደርገዋለሁ"* አለው (ሕዝ. 3፥26)። ሕዝቅኤል ከውጪም ሆነ ከውስጥ የሚሰማው ምንም ዓይነት ድምጽ አልነበረም። በሕይወቱ ፍጹም ጸጥታ የሆነበት ጊዜ ነበር። እግዚአብሔር "ና ውጣ! ይበቃሃል!" እስከሚለው ድረስ በትዕግስት ቤቱን ዘግቶ ጸጥ ብሎ ተቀመጠ።

የሕዝቅኤል የዝምታ ጊዜ በዚህ አላበቃም። ሁለተኛ ረጅም የዝምታ ጊዜ ነበረው። *"ራስህን በገመድ አስረህ በአደባባይ በቀኝ ጎንህ*



*ብቻ ሳትገላበጥ ለ390 ቀናች ተኛ፥ ያንን ስትጨርስ ለ40 ቀናት በግራ ጎንህ አሁንም ሳትገላበጥ ተኛ"* አለው (ሕዝ. 4፥4-6)። ሕዝቅኤል በጠቅላላው 430 ቀናት በአደባባይ ታስሮ ተኛ። በነዚህ ቀናት ውስጥ ምንም ዓይነት በቃላት የሚገለጥ መልዕክት ለሕዝቡ ሳያስተላልፍ ጸጥ ብሎ ተኛ። ኢሳያስ በእስራኤል ሕዝብ ፊት ቆሞ በተለይ በኢሳያስ ምዕራፍ 53 ላይ የተጻፈውን ትንቢት በታላቅ ድምጽ ሲተነብይ እግዚአብሔርን እንዳከበረው፥ በዚያው መጠን ሕዝቅኤልም እግዚአብሔር በነገረው መሠረት ለ430 ቀናት ምንም ሳይናገር በአደባባይ ጸጥ ብሎ በመተኛቱ እግዚአብሔርን እንዳከበረው እርግጠኞች ነን። በዚህም በመናገር ብቻ ሳይሆን፥ ዝም በማለትም ሰው እግዚአብሔርን ማክበር ወይም ማገልገል እንደሚቻል እንረዳለን። እኛንም እግዚአብሔር "ዝም ብላችሁ፥ አርፋችሁ ተቀመጡ" የሚለን ጊዜ አለ። ካለን፥ አርፈን እንቀመጥ። በመራራጥ ከምናከብረው የበለጠ በዝምታችን እናከብረዋለን። እግዚአብሔር "ዝም በሉ" ካለን፥ እንደ ሚጠቅመን አውቆ ነውና "እሺ!" ብለን እንታዘዘው። "ዝምታ" ብዙ ይጠቅመናል።

## 4.1. <u>ዝምታ የማስታመስ ችሎታችንን ያዳብራል</u>

እንደምናውቀው ንግግራችን አብዛኛውን ጊዜ የሚያተኩረው በራሳችን ላይ ነው። ቅሬታችንን የምንገልጽበት፥ የምናጉረመርምበት፥ ቁጣችንን የምንገልጽበት፥ በጠቅላላው ስለ ራሳችን የምንናገርበትና እንዲሁም ራሳችንን የምናዳምጥበት መንገድ ነው። ምን ጊዜም ራሳችንን መስማት አይሰለቸንም። ብዙዎቻችን ጸጥ ብለን የምናሰብበት የጥሞና ጊዜ የለንም። ሌላው ቀርቶ በጸሎታችን ጊዜ እንኳን "ጸጥ" የምንልበት ጊዜ የለንም። በእግዚአብሔር ፊት ሁልጊዜ እንናገራለን። እግዚአብሔር በውስጣችን እንዲናገረን ዕድል አንሰጠውም። ስልክ አንስተን ስንደውል፥ ሌላው መስመር ላይ ሰው መኖሩን ሳናረጋግጥ ዝም ብለን ማውራት እንጀምርም። መኖሩንም የምናረጋግጠው በመናገር ሳይሆን፥ ዝም በማለት ወይም በማዳመጥ ነው። የታወቀው ጆርጅ መለር *"ከጸሎት ጊዜዬ ውስጥ በጣም ዋና ነው ብዬ የምለው ክፍል፥ 'አሜን' ብዬ ጸሎቴን ከደመደምኩ በኋላ ጸጥ ብዬ የማሳልፈው አስራ አምስት ደቂቃ ነው"* አለ። ዝም ስንል፥ እግዚአብሔር በውስ

ጣችን ሲናገረን ማዳመጥ እንችላለን። ዝም ስንል፥ ያ ወቅት ወደ ጎላ መለስ ብለን በመመልከት ሕይወታችንን የምንመዝንበት፥ ያበላሸ ውን የምናይበት፥ ከየት ተነስተን የት እንደደረስን የምንመረምርበት ጊዜ ይሆንልናል። በዚህ ውስጥ የእግዚአብሔርን ደግነትና ቸርነትም ማስታወስ ያስችለናል። በሕይወታችን ፊጽሞ መርሳት የማንፈልጋ ቸው ነገሮች አሉ። ብዝምታ እንዳንዶቹን ማሰላሰል እንችላለን። በዝ ምታ ውስጥ እግዚአብሔር በሕይወታችን የሰጠንን ራዕይ መመርመር እንችላለን።

### 4.2. ዝምታ ምስጢራዊ የሆኑትን ነገሮች እንድናይ ይረዳናል

ጊዜ አግኝተን በዝምታ ውስጥ ስንሆን፥ የእግዚአብሔርን የእጅ ቹን ሥራ መመልከትና መመርመር ስንጀምር፥ የምንናገረውን እስክ ናጣ ድረስ በአድናቆትና በመገረም እንሞላለን። የእግዚአብሔር ቅድስና ለሰው አዕምሮ የሚተልቅ ምስጢር ነው። ኢሳያስ ስለ እግዚ አብሔር ታላቅነት ሲናገር፥ *"ንጉሥ ያዝያን በሞተበት ዓመት እግዚ አብሔርን በረጅምና ከፍ ባለ ዙፋን ላይ ተቀምጦ አየሁት። የልብሱም ዘርፍ መቅደሱን ሞልቶት ነበር። ሱራፌልም ከእርሱ በላይ ቆመው ነበር..."* ይልና ዝቅ ብሎ *"...ከንፈሮቼ የረከሱብኝ ሰው በመሆኔ ከን ፈሮቻቸውም በረከሱባቸው ሕዝብ መካከል በመቀመጤ ዓይናቼ የሠ ራዊትን ጌታ ንጉሡን እግዚአብሔርን ስለ ለዩ ጠፍቻለሁና ወዮልኝ! አልሁ"* ይላል (ኢሳ. 61፥5)። የእግዚአብሔርን ቅድስናና ክብር ለማ የት እንድንችል፥ እግዚአብሔር በሚገኝበት ጊዜና ቦታ ዝም ብለን እንድንቀመጥ የሚያስፈልግበት ጊዜ አለ።

### 4.3. ዝምታ ራሰን የመግዛት ኃይል ይሰጠናል

በማስተዋል የሚደረግ ወቅታዊ "ዝምታ" የትልቅነትና የአሸናፊነት ምልክት ነው። ኢየሱስ እንዲፈረድበት በጲላጦስ ፊት በቀረበበት ጊዜ፥ ጲላጦስ ኢየሱስን በጥያቄ ያጣድፈው ነበር። ኢየሱስ ግን ከዝ ምታ በስተቀር ምንም መልስ አልሰጠውም ነበር። እንዲሁም በመስ ቀል ላይ በተንጠለጠለበት ጊዜም በዚያ የተሰበሰበው ሕዝብ "እምላክ ከሆንክ ራስህን ከመስቀል አውርድ" እያሉ ሲቀልዱበት፥ ምንም ዓይነት መልስ አልሰጣቸውም። እኛም "ዝምታን" እንደ መሣሪያችን



አድርገን መጠቀም የሚያስፈልገን ጊዜ አለ። ሲሰድቡን፣ ያላደረግነ ውን አደረጉ ሲሉን፣ ያልሆንነውን ሆኑ ሲሉን፣ ስማችንን በጭታ ሲቀቡት፣ ያለአግባብ ሲያዋርዱን፣ ዝምታን መሣሪያ አድርገን እን ጠቀምበት። አንዳንድ ጊዜ ከቃላት ይልቅ "ዝምታ" የበለጠ ኃይል እንዳለው የታወቀ ነው። *"ከሰማይ በታች ለሆነ ነገር ሁሉ ጊዜ አለው፥ ዝም ለማለት ጊዜ አለው፥ ለመናገርም ጊዜ አለው..."* (መክብብ 3፥7) ። ዝም ማለት በሚያስፈልግበት ጊዜ ካቃተን እግዚአብሔር ዝም የምንልበትን ፀጋ እንዲሰጠን ልንጸልይ ይገባል።

ከመናገራችን በፊት አስቀድመን ማሰብ በንግግራችን ሌሎችን ከመጉዳት ይጠብቀናል። *"ደጋግ ሰዎች ከመናገራቸው በፊት ያስባሉ፥ አመጸኞች ግን በችኮላ ክፉ ቃል ይናገራሉ"* ይላል (ምሳሌ 15፥28)። ፕሉትርክ የተባለ ምሁር ደግሞ ብዙ ስለሚናገሩ ሰዎች እንዲህ አለ፥ *"በመናገራቸው ብዛት መወደድ የሚፈልጉ፥ ይጠላሉ። እናስደስታለን ብለው ሲጠብቁ ይሰለቻሉ። እንደነቃለን ብለው ሲጠብቁ፥ መሳቂያ ይሆናሉ። እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች ወዳጆቻቸውን ሲጎዱ፥ ጠላቶቻ ቸውን ደስ ያሰኛሉ፥ በመጨረሻም ራሳቸውን ያጠፋሉ።"* በአሁኑ ጊዜ የብዙዎች ችግር፥ ሳያስቡ የመጣላቸውን ሁሉ መናገራቸው ነው። በዚህም ምክንያት ምላሳቸው ሊፈውስ ሲገባ እያቆሰለና እያደማ እንዲ ሁም የብዙዎችን ሕይወት፥ ቤትና አገልግሎት እያፈረሰ ነው።

## 5. ምላሳችን ምንና ምን ያካተተ ነው?

ምላሳችን ብዙ ነገር ያካትታል። ከብዙዎቹ መካከል አራቱን ብቻ ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን።

(1) በሌላው ላይ መፍረድ (Judging);

(2) ሁኔታን ለይቶ ለማወቅ ጥያቄ መጠየቅ (Discerning);

(3) መገሰጽና (Reproving);

(4) ስም ማጥፋት ወይም ስድብ (Reviling) ነው።

### 5.1. ምላሳችን በሌላው ላይ "ፃፍርድ ቃል" (Judgment) ይናገራል፥

መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ቢያስጠነቅቅም፥ ብዙዎቻችን በማወቅም ሆነ ባለማወቅ፥ በሌላው ሰው ላይ የፍርድ ቃል የምንናገርበት ጊዜ

አለ። *"በእናንተ ላይ እንዳይፈረድባችሁ በማንም ሰው ላይ አትፍረዱ፥ ምክንያቱም በሌሎች ላይ በምትፈርዱበት ዓይነት በእናንተም ይፈረድባችኋል፥ እንዲሁም በምትሰፍሩበት መስፈሪያ ይሰፈርባችኋል። በአንተ ዐይን ያለውን ግንድ ሳታይ ስለምን በሌላው ሰው ዐይን ያለውን ጉድፍ ትመለከታለህ?"* ይላል (የማቴ. 7፥1-3)። በመንፈስ ቅዱስ የሚመራ ብርቱ ክርስቲያን በሌላው ላይ አይፈርድም። ይሁን እንጂ፥ ሌላውን የመመርመር ወይም የመለየት ችሎታ እንዳለው መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። መጽሐፍ ቅዱስ "በማንም ላይ አትፍረዱ" ስለሚል፥ መፍረድ ባንፈልግም፥ አልፎ አልፎ በሌላው ላይ ስንፈርድ ራሳችንን እናገኘዋለን። ምክንያታችን "መፍረድ" ምን እንደሆነ ካለ መረዳታችን ይሆን? "መፍረድ" አስተያየት ከመስጠት የተለየ መሆኑን ብዙዎቻችን አናውቅም። "አስተያየቴን ሰጠሁ እንጂ አልፈረድኩም" ብለን የምንከራከርበት ጊዜ አለ። በዚህ ዓይነት "አስተያየት የሰጠን" መስሎን ሳናውቀው በሌሎች ላይ የምንፈርድበት ጊዜ አለ። ለመሆኑ "መፍረድ" ማለት ምን ማለት ነው?

<u>ምሳሌ 1</u>:- አንድ አማኝ ቤተሰቡን ይዞ ከቤተ ክርስቲያን ሲመለስ፥ በልቡ ውስጥ የሚሰማውን ስሜት እንዲህ ሲል ገለጸ። *"በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ምንም ዓይነት ዕድገት አላይም። ለአለማደጋችን ምክንያት የሆነ አንድ ትልቅ ችግር መኖር አለበት። ፓስተሩ ራሱ፥ በትዳሩ ውስጥ የራሱ የሆነ ችግር ሊያለበት ለምን ይሰብክል? የሚሰቱ አለባበስ በብዙ ክርስቲያኖች ላይ ጥያቄን እየፈጠረ መጥቷል። አሰባበኩ ደግሞ በገንዘባቸው ቤተ ክርስቲያኒቷን በጣም የሚደግፉትን አንዳንድ የቤተ ክርስቲያኒቱን አባሎችን እያሰናከለ ነው ይባላል"* አለ። ይሄ ሰው ይህን ዓይነቱን ቃል ሲናገር መፍረዱ ነው? ወይስ ቤተ ክርስቲያኒቱ ምን እንደጎደላት ለማወቅ ፈልጎ የተናገረው ንግግር ነው? የሰውየው ንግግር እውነቱን ለማወቅ የተናገረው ሳይሆን፥ የፍርድ ቃል እንደሆነ ግልጽ ነው።

በሌላው ላይ የሚሰነዘር የፍርድ ቃል ምንድነው? በአዲስ ኪዳን የተጠቀሰው የግሪኩ ቃል፥ በሰው ሁኔታና እንቅስቃሴ ላይ ያተኮረ ፍርድ ነው ይለዋል። *"ክሪና"* የሚለው የግሪክ ቋንቋ ትርጉሙ ፍርድ ማስተላለፍ፥ ብያኔ መስጠት፥ በግል አስተያየትም ሆነ በሕግ በሌላው ላይ መፍረድ፥ መወሰን ማለት ነው። ያለእግባብ በሌላው መፍረዳችን



ለመሆኑ በምን ይታወቃል? ፈራጅ ሰው፥

1. ጠለቅ ብሎ የሌላውን ሰው አቋምም ሆነ ችግር ሳይመለከት፥ ራሱም ተመሳሳይ ችግር እንዳለበት ሳይመረምር በሌላው ላይ ይፈርዳል። *"በሌላው ሰው ላይ የምትፈርድ አንተ፥ ለራስህ የምታመካኘው የለህም፥ ምክንያቱም በሌላው ሰው ስትፈርድ በራስህ ላይ ትፈርዳለህ፥ አንተ በሰው ላይ እየፈረድህ ያ የፈረድህበት ሰው የሚያደርገውን ታደርጋለህ"* (ሮሜ 2፥1)።

2. አስቀድሞ አቋም ይይዝና ሀሳቡን የሚደግፍለትን ጉድፍ በሌላው ላይ ይፈልጋል። *"ወንድሞቼ ሆይ! እርስ በርሳችሁ አትተማሙ፥ ሰውን የሚያማ ወይም በሰው ላይ የሚፈርድ ሕግን ያማል፥ በሕግም ላይ ይፈርዳል፥ በሕግም ላይ ብትፈርድ፣ ፈራጅ መሆንህ ነው እንጂ ሕግን ፈጻሚ አይደለህም"* (ያዕ. 4፥11)።

3. ሌሎች እንዲፈርዱበት በአደባባይ የሌላውን ሰው ድካም ያወራል። *"በማንም ላይ አትፍረዱ፥ በእናንተም ላይ አይፈረድባችሁም፥ ሌሎችን አትንቀፉ፥ እናንተም አትነቀፉም፥ ይቅር በሉ እናንተም ይቅርታ ታገኛላችሁ"* (የሉቃ. 6፥37)።

ከላይ ባየነው ትርጉም መሠረት መጀመሪያ ላይ የሰጠነው ምሳሌ ምንድነው? ሰውየው ወደ ውስጥ ዘለቅ ብሎ ችግሩን ለማወቅ በመጣር ፈንታ ከውጪ በሚያየው ብቻ የሌሎችን አዕምሮ የሚበርዝ መጥፎ ሪፖርት ወይም አስተያየት በመስጠቱ መፍረዱ ነበር።

## 5.2. <u>ምሳሌችን "ሁኔታን ለይቶ ለማወቅ" (Discernment)</u>

### <u>ጥያቄ ይጠይቃል፥</u>

ይህንን ሀሳብ በበለጠ ለመረዳት፥ አዲስ ኪዳን የተጻፈበትን ግለ ትም የግሪኩ ቋንቋ በምን ዓይነት ሁኔታ እንደጠቀሰው መመልከት ይጠቅመናል። በግሪክ ቋንቋ "ሁኔታን ለይቶ ለማወቅ" (Discernment) በሦስት የተለያዩ ቃላት ተገልጿል።

*(1)* *<u>"ዶኪማዞ"</u>* - ትርጉሙም፥ መፈተን፣ መመርመር፣ መተርጎም፣ ማጽደቅ፣ ማረጋገጥ፣ ማመልከት ማለት ነው።

(2) *"አናክሪናለ"*- ትርጉሙም፥ ጥያቄ መጠየቅ፣ መመርመር፣ በጥንቃቄ መርምሮ መረዳት፣ ማጣራት፣ መፈለግ ማለት ነው።

(3) *"ዲያክሪና"* - ትርጉሙም፥ በሁለት ሰው መካከል ያለውን ልዩነት ማወቅ፣ እያንዳንዱን መለካትና መመዘን ማለት ነው።

ሁኔታን በትክክል አጣርቶ ለማወቅ የሚፈልግ ሰው፤

ሀ) በሌላው ላይ ከመፍረዱ በፊት አስቀድሞ የራሱን ሕይወት ይመረምራል። *"እያንዳንዱ ሰው የራሱን ሥራ መርምሮ ይፈትን፥ ከዚህ በኋላ ራሱን ከሌሎች ጋር ቦግዳደር ሳይሆን ለራሱ ብቻ የሚመካበትን ነገር ያገኛል"* (ገላት. 6፣4)።

ለ) አስተያየት ከመስጠቱ ወይም ከመፍረዱ በፊት አስቀድሞ የሁኔታውን እውነተኛነት ወይም ትክክለኛነት በጥንቃቄ ይመረምራል። *"የእግዚአብሔር መንፈስ ያለው ግን ሁሉን ነገር መመርመር ይችላል፥ እርሱ ራሱ ግን በማንም አይመረመርም"* (1 ቆሮ. 2፣15)።

ሐ) በሌላው ሰው ላይ ያየውን ድካም ከሚመለከተው ሰው ጋር ቦግል ይነጋገራል እንጂ በአደባባይ አያወራም። *"ወንድምህ ቢበድልህ አንተና እርሱ ብቻችሁን ሆናችሁ በደሉን ንገረው፥ ቢሰማህ እንደ ገና ወንድምህ እንዲሆን ታደርገዋለህ"* (የማቴ. 18፣15)።

*ምሳሌ 2*፦ ከቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች አንዱ ከዕውድ ስብሰባ በኋላ ከጥቂት ክርስቲያኖች ጋር ሲያወራ *"ባለፈው ሳምንት ፓስተሩ (መጋቢው) የሰበከው ስብከት ፍጹም ትክክል አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ ከሚለው ውጪ ነው። በዚህ አርዕስት በግሌ ብዙ ጥናት ወስጃለሁ። በሰጠው ትምህርት ፈጽሞ አልስማማም"* ይላል። እዚህ ላይ ሽማግሌው መፍረዱ ነው? ወይስ "ሁኔታን ለይቶ ለማወቅ" (Discernment) የተናገረው ነው?

ሽማግሌው ከላይ የሰማነውን ዓይነት አስተያየት ሲሰጥ መፍረዱ እንደሆነ ግልጽ ነው። እንዲህ ዓይነቱ አስተያየት፥ ምዕመናኑ በመጋ



ቢያቸው ላይ እምነት እንዳይኖራቸው ከማድረጉም በላይ በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ መከፋፈልን ሊፈጥር ይችላል። ከላይ የሰማነውን አስተያየት በመስጠት ፈንታ "ባለፈው ሳምንት መጋቢው በሰበከው ሀሳብ ላይ ጥያቄ ስለነበረኝ ተነጋግረን የደረስንበት ውጤት እንዲህ ነው..." ቢል መፍረዱ ሳይሆን፥ አስተያየት መስጠቱ ይሆን ነበር።

*ምሳሌ 3*፦ የቤተ ክርስቲያን አባል የሆነ፥ አንዱን የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ፦ *"እስሬን ካየሁት ብዙ ጊዜ ነው። ደሀና ነው ወይ? ከጸሎት ጓድ ስብሰባችን መምጣት ካቆመ ጀምሮ አይቼው አላውቅም። ከቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች አንዳችሁ ሄዳችሁ ብትነቅፉት ጥሩ ነው"* አለው። ይህን ሲል፥ መፍረዱ ነው ወይስ ሁኔታውን ለማወቅ የጠየቀው ጥያቄ፥ የሰጠው አስተያየት ነው? ሁኔታውን አጥርቶ ለማወቅ የተናገረው እንጂ፥ በክርስቲያን ወንድሙ ላይ ለመፍረድ የተናገረው እንዳልሆነ ግልጽ ነው።

## 5.3. *መገሰጽ (Reproving)*

"መገሰጽ" የሚለው ሀሳብ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ "መዝለፍን፥ መውቀስን" ያጠቃልላል። "መገሰጽ" የሚለው ቃል በግሪክ ቋንቋ በሦስት ዓይነት መልክ ተገልጿል።

1) *"ኤሌንኾ* - የሳተውን መንገር፣ መገሰጽ፣ መሳሳቱን ማረጋገጫ መስጠት ማለት ነው።

2) *"ኤፒቲማኦ"* - ማዘዝ፥ ኃላፊነት መውሰድ ማለት ነው።

3) *"ፓራካሊኦ* - መጠየቅ፣ ማደፋፈር፣ ይግባኝ (አቤቱታ) ማለት ማጽናናት፣ አንድ ዓይነት እርምጃ እንዲወሰድ መገፋፋት ማለት ነው።

የመገሰጽ ዋና ዓላማ፥ የተሳሳተውን ወንድም በሌላ ሰው ፊት ለማጋለጥ ሳይሆን፥ ለማደስ፥ ወደ ትክክለኛው አቅጣጫ ለመመለስ ነው። ትክክለኛ የሆነ ግሳጼ፥

(ሀ) የሚገሰጸው ሰው አንድ ዓላማ አለው። ዓላማውም የሳተውን ወንድም በምክር ከሳተበት አቅጣጫ ለመመለስ ነው። ጳውሎስ ቲቶን ሲመክረው *"እንግዲህ እነዚህን ነገሮች አስተ*

ምርቶ በሙሉ ሥልጣንም ምክርቶ ገሥጽምቶ ማንም አይና ቅሆ" አለው (ቲቶ 2፥15)

(ለ) የሚገስጸው ሰውቶ የሳተውን ወንድም በሚገስጽበት ወቅት በፍቅርና በእውነት ተሞልቶ መሆን አለበት። ግሳጼው ከፍ ቅር ጋር ካልቀረበ "ጠንካራ" ይሆናል። እንዲሁም "ፍቅር" ያለ "እውነት ከሆነ፥ በእውነት ላይ ማመንታት ይሆናል (ራዕይ 3፥19፣ 1ኛ ጢሞ. 5፥19-20፣ ሉቃስ 17፥3)።

(ሐ) የሚገስጸው ሰው ክልሉን ወይም ወሰኑን ያውቃል (1ኛ ጢሞ. 5፥11፣ ይሁዳ ቁ. 9)።

### 5.4. ሰም ማጥፋት ወይም ስድብ (Reviling)

ምሳሌ 4:- *የአንድ የቤተክርስቲያን ዲያቆን፥ የቤተ ክርስቲያኒቱ መጋቢ ከምዕመናን የተሰበሰበውን ገንዘብ ያለአግባብ ይጠቀማል ብሎ ሰላመነ፥ መጋቢውን ፊት ለፊት አነጋገረው። መጋቢው ግን "ለአንተ መልስ መስጠት አልፈልግም" በማለት ችላ አለው። በመጨረሻ ዲያ ቆኑ ሁኔታውን በመግለጽ ደብዳቤ ጽፎ ለያንዳንዱ ምዕመናን በተነ።*

ይሄ ዲያቆን ስቷል ብሎ ያሰበውን መጋቢ እንደ እግዚአብሔር ቃል መገሰጹ ነው? ወይስ ወንድሙን ማውገዙ ወይም ስሙን ማጥ ፋቱ ነው? "የመገሰጽ ዓላማ" ከላይ እንዳየነው የሳተውን ወንድሙን ለማትካከል እንጂ ለግጋለጥ አይደለም። ዲያቆኑ መጋቢውን ማስ ተካከሉ ሳይሆን ማውገዙ ወይም ማሳጣቱ እንደሆነ ግልጽ ነው። እን ዲህ ዓይነቱ ሁኔታ በአግባቡ ካልተያዘ፥ በቤተ ክርስቲያኒቷ ላይ ከፍተኛ ጉዳት እንደሚያመጣ ግልጽ ነው።

## 6. መንፈሳዊ ውበት እንዲኖረን፥ ከአፋችን ክፉ ቃል አይውጣ

ጳውሎስ ምላስን በሚመለከት ነጥብ ላይ ለክርስቲያኖች ሁሉ መመሪያ እንዲሆን የሰጠው ቃል አለ። ይኸውም፥ *"ክፉ ከአፋችሁ ክፉ ቃል አይውጣ፥ ነገር ግን ለሚሰሙት ጸጋን የሚሰጥና ለማነጽ የሚጠቅም፣ ለሰዎችም አስፈላጊ የሆነውን ቃል ተናገሩ"* (ኤፌ. 4፥ 29) የሚል ነው። ከመናገራችን በፊት "የምናገረው ቃል ጸጋን ይሰ ጣል ወይ? ለማነጽ ይጠቅማል ወይ? ለሰዎች አስፈላጊ ነው ወይ?" በማለት ራሳችን እንጠይቅ። የምናገኘው መልስ "አይጠቅምም፥ አያን ጽም፥ ጸጋን አይሰጥም" የሚል ከሆነ፥ ዝም እንበል ወይም አርዕስታ ችንን እንቀይር። ይህንን ማድረጋችን ለብዙ ነገር ይጠቅማል።

1ኛ/ አሉባልታን ያስወግዳል። እኔና እናንተ ተጠንቅቀን ስለማንና ገር፥ አብዛኛውን ጊዜ ንግግራችን ለሰሚው ጸጋ የሚሰጥ፥ ለማነጽ የሚጠቅም አይደለም። እውነቱን ለማወቅ ብንፈልግ ብዙ ጊዜ ንግግራችን አሉባልታ ወይም ሐሜት ላይ ያተኮረ እንደሆነ እንረዳለን። አሉባልታውም አብዛኛውን እውነትነቱ ያልተረጋገጠ ወይም ውሸት ከእውነት ጋር ተደባልቆ የቀረበ ነው። አሉባልታው እውነትነት ያለው እንኳን ቢሆን በዓለም ሁሉ መታወጅ አለበት ወይ? አሉባልታን የሚያሰራጩ ሰዎች ምን ዓይነት ሰዎች እንደሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ ሲገልጽ፥ *"ክፉ ሰዎች ሐሜትን ያሰራጫሉ፥ ሁከትንም በማነሣሣት በፍቅር የተሣሠሩትን ወዳጆች ይለያያሉ"* ይላል (ምሳሌ 16፥28)። ንግግሩ በጸጋ የተሞላ፥ ለሰዎች የሚጠቅም ቃል ብቻ ለመና ገር የሚፈልግ ሰውቶ ሁልጊዜ ራሱን አሉባልታና ሐሜት ከማውራትና ከማሰራጨት ይጠብቃል።

2ኛ/ አንድነትን ያጠነክራል። ምላሳችንን መግታት ስንችል፥ ብዙ ችግሮችን እናስወግዳለን። ያዕቆብ "ለቁጣ አትቸኩሉ" ሲል፥ በአግባቡ ያልተያዘ ቁጣ በራስም ሆነ በሌላው ላይ የሚያመ ጣውን ጉዳት ስለሚያውቅ ነው። የባልና የሚስት ግጭትቶ መለያየትና መፋታት ትልቁ ችግር፥ ብዙ ጊዜ ከሁለት አንዳ ቸው ወይም ሁለቱም ቁጣቸው ከመስመር በመውጣቱ ነው። ሰው ሲቆጣ፥ ሳያስብ ዝም ብሎ በመናገሩ ሌላውን ይጎዳል። ምላስ በሰው ላይ የሚያደርሰውን ስብራት ተናጋሪው ባያው ቀውቶ፥ የተወረወረበት ሰው ያውቀዋል። ክፉ ምላስ የባልና ሚስትን አንድነት ብቻ ሳይሆን፥ የቤተ ክርስቲያንንም አንድ ነት ያፈርሳል። የሚዋደዱትን ጓደኞችንም ይለያያል።

ኢቫንጀሊስቲክ ኢሉስትሬሽን (Evangelistic Illustration) በሚ ለው መጽሔት አንድ ጊዜ "ዌስሊ ባለስድስቱ አንቀጽ ቃል ኪዳን" (Six Articles of Wesley's Covenant) በሚል አርዕስት አንድ ጽሁፍ ወጥቶ ነበር። በ1752 ዓ.ም. (እ.አ.አ) ጆን ዌስሊና የተወሰኑ ጥቂት ሰዎች "ሜተዲስት" የሚል ቅጽል ስም የተሰጣቸው፥ አሉባልታን በሚ መለከት አሳብ ላይ ቃል ኪዳን አውጥተው ሁሉም ፊርማቸውን ካኖሩ በኋላ በክፍላቸው ግድግዳ ላይ እንዲለጥፉ ተስማሙ። ስድስቱ የቃል ኪዳን አንቀጽ እንዲህ ይላል፥

1. አንዳችን የሌላችንን ድካም አንሰማም፥ ሆን ብለንም ድካሙን አንጠይቅም።
2. አንዳችን የሌላችንን ድካም ብንሰማ፥ ሌላው አምኖ እንዲቀበለው አናደርግም።
3. አንዳችን ስለሌላችን የሰማነውን በአስቸኳይ በደብዳቤም ሆነ በቃል የሚመለከተው ሰው እንዲያውቀው የሰማነ ውን ነገር እናስተላልፍለታለን።
4. ቁጥር ሦስት ላይ ያለውን ሳናደርግ፥ አንድም ቃል ቢሆን ለሌላ ሰው አንነግርም።
5. ለሚመለከተው ሰው ከነገርን በኋላም፥ ከዚያ ውጪ ለማንም አንናገርም።
6. ለውጥ ያስፈልጋል ብለን በማመን ተሰብስብን ካልወሰንን፥ ከነዚህ ደንቦች ውጪ ሌላ የተለየ ነገር አናደርግም።

ክፉ ምላስ ቤተ ክርስቲያንን፣ ትዳርን፣ የሰዎችን አንድነት ከም ንጊዜውም የበለጠ እያጠፋ ባለበት በአሁኑ ዘመን፥ ይህንን የመሰለ ቃል ኪዳን ተጽፎ በየአብያተ ክርስቲያናቱ፥ እንዲሁም በየቤቱ ግድግዳ ላይ ቢለጠፍ ይጠቅማል ብለን እናምናለን።



# ምዕራፍ ፪

# መልካም ምላስ

*"ተገቢውን ቃል በተገቢው ቦታ መናገር እጅግ ያስደስታል።"*
*(ምሳሌ 15፥23)*

አንደበት የማቁሰል ኃይል እንዳለው ሁሉ የመፈወስም ኃይል አለው። መጽሐፍ ቅዱስ "ጥደግ ሰው ንግግር የሕይወት ምንጭ ነው" ይላል (ምሳሌ 10፥11)። ከአንደበታችን የሚወጣው ቃል ጎጂ ወይንም ጠቃሚ እንዲሆን ወሳኙ የልባችን አቋም እንደሆነ ከላይ ያየነው የመ ጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ያረጋግጥልናል። ልቡ በበጉ ደም ታጥቦ የነጻ፣ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ አማኝ፥ ከአንደበቱ የፈውስ ቃል እንጂ ሌሎ ችን የሚገድልና የሚያጠፋ ቃል መውጣት የለበትም።

## 1. <u>መልካም ምላስ ለሚሰማው ኃይል ይሰጣል</u>

ክፉ ቃል ተናግረውን ያልረሳናቸው ሰዎች እንዳሉ ሁሉ በጎ ቃል ተናግረውን ሁልጊዜ የምናስታውሳቸው ሰዎችም አሉን። መንፈሳችን ዝቅ ባለበት ወቅት፥ ተስፋ በቆረጥንበትና መንገዳችን ሁሉ ጨለማ በሆነብን ሰዓት፥ የማጽናኛ ቃል የሰጡንን ሰዎች ፈጽሞ አንረሳቸውም።

ከየአቅጣጫው በተወረወረብን መጥፎ ቃላት ምክንያት ስለ ራሳችን ዝቅተኛ አስተያየት በነበረን ወቅት በሰዓት ደርሰው የማደፋፈሪያ ቃል የሰጡንን አንረሳቸውም። ስለዚህ በአንደበታችን በጎ የሆነውን በመፈጸም ሌሎች በበጎ እንዲያስታውሱን ይሁን እንጂ ቃላችን በሌላው ሰው ሕይወት ውስጥ ጠባሳን የሚተው እንዳይሆን ልንጠነቀቅ ይገባል። ይህን ማለት ወዳጃችን ሲስት እያየን አንገሰጸውም ወይም ዝም እንለዋለን ማለት አይደለም። እኛም ስተን ከተገኘን በፍቅር የሚያርመንን "ሰበረኝ! ጎዳኝ!" እያልን የምራት ቃል እናሰማለን ማለት አይደለም። *"ተገቢውን ቃል በተገቢው ቦታ መናገር እጅግ ያስደሰታል"* ይላል (ምሳሌ 15፥23)። እርማት በሚያስፈልገው ወቅት ዝም ማለት ወዳጅን መጉዳት እንጂ መጥቀም አይሆንም። መጽሐፍ ቅዱስም ይህንን ያረጋግጥልናል። *"ሰውን በክፋር እመደሃለሁ ማለት ብቻ አይበቃም፥ በሚሳሳትበት ጊዜ በግልጥ መገሰጽም ይገባል"* ይላል (ምሳሌ 27፥5)። አንደበታችን በሌላው ሰው ሕይወት ጥሩ ወይም መጥፎ ነገር በልቡ ሊቀርጽ ይችላልና የምንናገረውን መምረጥ ይገባናል።

ክፉ ቃል የሚጎዳውን ያህል፥ መልካም ቃልም ይጠቅማል። ሰዎች በአሉታም ሆነ በአምንታ የተናገሩን አንዳንድ ቃል ከውስጣችን ለረጅም ጊዜ አይጠፋም። በልጅነታችን ወላጆቻችን፥ አስተማሪ ዎቻችንን፥ በቅርብ የሚያውቁን ሰዎች የተናገሩን ክፉም ሆነ በጎ ቃል፥ ክአደግንም በኋላ ከአዕምሯችን አይጠፋም። በሕይወቴ ፈጽሞ ከማልረሳቸው ትዝታዎች መካከል አንደኛው፥ የአንደኛ ክፍል ተማሪ ሆኜ፥ የአማርኛ አስተማሪዬ፥ አቶ ለማ ስለ እኔ የሰጡት አስተያየት ነው። አንድ ቀን በምሳ ሰዓት እጃቸውን ሳስታጥባቸው፥ ምሳ ይዘዉ ላቸው ከመጡት ባለቤታቸው ጋር ሲያስተዋውቁኝ፥ *"ይሁኟ ልጅ በትምህርት ዎዛ መሰለችሽ፥ ጥይት ነች"* አሏቸው። የአቶ ለማ ንግግር ውስጤን አሞቀው። እኔም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ "ጥይት ተማሪ ነኝ" ብዬ አመንኩ። ማመን ብቻ ሳይሆን፥ ጥይትነቴን ለማስመስከር ከዚህ በፊት ከማደርገው የበለጠ ትግል ማድረግ ጀመርኩ። የአቶ ለማ ጥሩ ንግግር ለዚያን ጊዜ ብቻ ሳይሆን፥ ዛሬም ለደረስኩበት ደረጃ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳደረገ እርግጠኛ ነኝ። አቶ ለማ በሕይወት የሉም፥ የተናገሩት ንግግር ግን በእኔ ውስጥ ይኖራል። በትጋት



ትምህርቴን እንድከታተል፥ ከድንቁርና ለመውጣት መማር ጠቃሚ መሆኑን እንዳምን ረድቶኛል። የአቶ ለማን መልካም ንግግር በሕይወቴ ፈጽሞ የማልረሳውን ያህል፥ አንዳንድ ጎጂ የሆነ ቃል የሰነዘሩብኝን የክፉ ሰዎች ንግግርም አልረሳም።

በንግግራቸው የጎዱኝን ክፉ ሰዎችና እንዲሁም የተናገሩኝን ክፉ ቃል፥ ከአዕምሮዬ ፍቄ ለማስውጣት ወይንም ለመርሳት የተቻለኝን ሁሉ አደርጋለሁ። በመልካም ንግግራቸው የጠቀሙኝን፥ ስደክም ያበረታቱኝን፥ ተስፋ ስቆርጥ "አይዞህ! በርታ!" ያሉኝን በጎ ሰዎችና "ገንቢ የሆነውን ቃላቸውን" ግን በሕይወቴ ፈጽሞ መርሳት አልፈልግም። ጌታ የሰጠኝ አገልግሎት ከማንም ጋር የማያገናኝ፣ የማያጋጭ፣ "ድንበሬን ነካህ፣ በጎቼን ሠረቅህብኝ" የማያሰኝ ቢሆንም፥ በማይገባኝ ምክንያት በመንገዴ ላይ የተለያየ እንቅፋት የሚዘረጉ አንዳንድ ሰዎች አሉ። እንደነዚህ ዓይነት ሰዎችን በአገልግሎት ዘመኔ ሁሉ ያጣሁበትን ጊዜ አላስታውስም። ዛሬ ብቻ ሳይሆን ወደፊትም ይኖራሉ። እግዚአብሔር ትዕግሥታችንን ለመፈተን ሆን ብሎ ያስቀመጣቸው ይሆናልና በማጉረምረም ፈንታ በጸጋ ልንቀበለው ይገባል። አገልግሎታችንን ለማዳከም፣ ብዙዎች በአገልግሎታችን እንዳይጠቀሙ ለማድረግ፥ የጠቢያና የሰንባላጥ መንፈስ ያለባቸው አንዳንድ ሰዎች የማያወሩብንና የማያስወሩብን ነገር የለም። ያላወቁት ወይንም ያልተገነዘቡት ነገር ቢኖር፥ በገሩን ቁጥር የበለጠ ኃይል የምናገኝ መሆናችንን ነው። ይህን ቢያውቁ ኖሮ፥ ዓላማቸው እኛን ለመጉዳት ስለሆነ ይተዉን ነበር። እግዚአብሔር በትክክል የጠራውን ሰው፥ ሰዎች ምንም ያህል ጥረት ቢያደርጉ ሊያጠፉት እንደማይችሉ በሕይወታችን ተለማምደን አይተነዋል። እንደ አንዳንድ ሰዎች ጥረት ቢሆን ኖሮ በአገልግሎት ላይ መቆየት ቀርቶ በሕይወትም መኖር አንችልም ነበር። ደግሉ እንዲህ ዓይነተኞቹ በጣት የሚቆጠሩ ጥቂት ሰዎች መሆናቸው ነው። ቁጥር ሥፍር የሌላቸው፥ በአገልግሎታችን የተለወጡ፥ በምንሰጠው ትምህርት የተባረኩ ሰዎች፥ ከምንገምተውና ከምንጠብቀው በላይ የሚያበረታታ፣ የሚያጽናና፣ እንዲሁም የሚገነባ ቃል ከዓለም ዙሪያ በደብዳቤም ሆነ በስልክ ያስተላልፉልናል። "አይዟችሁ! በርቱ! እንጸልይላችኋለን" የሚለው የማበረታቻ ቃላቸው ምን ያህል ጉልበት እየሰጠን እንደሆነ የምንገልጽበት ቋንቋ ያንሰናል። ለረጅም ጊዜ በገንዘባቸው፣ በጸሎታቸውና በምክራቸው ስላልተለዩን፥

በታማኝነት ከኅናችን ስለቆሙት ሰዎች እግዚአብሔርን እናመሰግ ናለን።

## 2. <u>መልካም ምላስ፥ ተገቢውን ቃል በተገቢው ጊዜ ይናገራል</u>

ጠቢቡ ሠለሞን *"ተገቢውን ቃል በተገቢው ቦታ መናገር እጅግ ያስደሰታል"* (ምሳሌ 15፥23) ይላል። "ተገቢውን ቃል በተገቢው ቦታ መናገር" እንዴት ዓይነት ይሆን? መጠገን በሚያስፈልግ ሰዓት የሚ ሰብር፥ መገሰጽ በሚገባ ጊዜ የሚያሞካሽ ቃል መናገር፥ ተገቢ የሆነ ውን ቃል በተገቢው ጊዜ መናገር አይደለም። አንዳንድ ሰዎች ለተ ጠየቁት ጥያቄ ትክክለኛ መልስ፥ በአስፈላጊው ጊዜ ወቅታዊ የሆነ አስተያየት የመስጠት ልዩ ችሎታ አላቸው። ሦስተኛው ልጃችን ዮሴፍ በልጅነቱ ፈጣን የሆነ ትክክለኛ መልስ የመስጠት ችሎታ ነበ ረው። በልጅነቱ ብዙ ጊዜ ምግብ አልበላም እያለ ስለሚያስቸግር አንድ ቀን *"አንተ ልጅ ለምንድነው ይህን... ያን ምግብ አልበላም እያልክ የምታስቸግረው? ምግብ ለጥተው ስንቶቹ እንደሚራቡ ታው ቃለህ?"* አልነው። እርሱም ረጋ ብሎ *"መብላት የማልፈልገውን ነገር እንድበላ ከምታስቸግሩኝ፥ ለምን ለእናርሱ ወሰዳችሁ አትሰጧቸ ውም?"* በማለት የሚገርመንን መልስ ሰጠን። አንዳንድ ጊዜ፥ ሰዎች ቅር የሚያሰኝ ቃል ተናግረውን፥ በወቅቱ አስፈላጊውን መልስ ሳንሰጥ ሁኔታው ካለፈ በኋላ "እንዲህ ሲለኝ፥ 'እንዲህ ብዬ ለምን መልስ አልሰጠሁትም?' ብለን የሚቆጨን ጊዜ አለ። አንዳንድ ሰው ግን ለሁኔታው ወይም በወቅቱ ትክክለኛ የሆነ መልስ፥ ሳይውል ሳያድር የሚሰጡት መልስ ወዲያው የሚመጣላቸው አንዳንድ ሰዎች አሉ። ከነዚህ መካከል አንደኛው በቅርብ የማውቀው ድፋቸው ነው (ትክክለኛ ስሙ አይደለም)። ድፋቸው አንድ መሥሪያ ቤት ተቀ ጥሮ ሲሠራ ምክንያት እየፈለገ የሚጨቃጨቀው አለቃ ነበረው። ድፋቸው "ሥራዬን በድንብ ከሠራሁ፥ ምክንያት እየፈለጋችሁ አት ንኩኝ" የሚል ሰው ነበር። አለቃውም ስለ ድፋቸው ኃይለኛነት፥ ወይም "አትንኩኝ" ባይነት ከሌሎች ሰዎች ቀደም ሲል ስለሰማ፥ ሥልጣኑን ለማሳየት ምክንያት እየፈለገ ይተናኮሰው ነበር። አንድ ቀን ድፋቸው አለቃውን መጻፊያ እርሳስና ላጲስ እንዲሰጠው



ጠየቀ። አለቃውም የተጠየቀውን በመስጠት ፈንታ እየተነጫነጨ "በቅርቡ ሰጥቼህ አልነበረም እንዴ? ምን አደረግኸው? በላኸው እንዴ?" አለው። የአለቃው አነጋገር ባያስደስተውም ድፋቸው ወዲያው በእርጋታ፥ "እሺይ፥ እስካሁን ድረስ እርሳስና ላጲስ የሚያ ስበላ ረሃብ ላይ አልደረስኩም።" በማለት መለሰለት። አለቃውም የጽሕፈት መሣሪያ ከሚታዘዝበት የመሥሪያ ቤቱ መጋዘን በማስመ ጣት "ይኸውልህ እንካ! ይበቃሃል?" አለው። ድፋቸውም "ይህን ሰው ማስተማር አለብኝ" ያለ ይመስላል፥ *"አዎን! ካልበላሁት ይበቃ ኛል!"* አለው።

በሌላ ጊዜ ደግሞ ድፋቸው ትንሽ ስላመመው፥ አለቃውን "አሞኛል ሆስፒታል ልሂድ ፈቃድ ስጠኝ" ብሎ ጠየቀው። አለቃ ውም ሳያመው "አመመኝ" የሚል መስሎት በመጠራጠር፥ "ያመመህ ምንህን ነው? እንዴት ያደርግሃል?" ብሎ ጠየቀው። እንደተጠራጠ ረው ስለገባው ቀጥተኛ መልስ በመስጠት ፈንታ *"ህመሜን ለእንተ ከነገርኩህ፥ ለህሊሙ ምን ልነግረው ነው?"* ብሎት ከክፍሉ ወጣ። እንዲሁም አንድ ቀን ድፋቸው የሥራ ዴስኩ ላይ ሆኖ ምድብ ሥራውን ሲሠራ፥ ሁለት የሥራ ባልደረቦቹ ተጣልተው በቦክስ ይደ ባደቡ ነበር። በመካከል ገብቶ ጠቡን ለማብረድ በመሞከር ፈንታ ቁጭ ብሎ ሥራውን ይሠራ ነበር። አለቃው ድብድቡን ሰምቶ ሮጦ ሲመጣ፥ ሁለቱ ሲደባደቡ ድፋቸው ግን ምድብ ሥራው ላይ ቁጭ ብሎ ሲሠራ አየውና ተቆጥቶ "እንዴ! በማስታረቅ ፈንታ ሲደባደቡ ቁጭ ብለህ ታያለህ እንዴ?" ብሎ ጠየቀው። ፈጣን መልስ የመስጠት ችሎታ ያለው ድፋቸው ለአለቃው፥ *"ስቀጠር የተሰጠኝ የሥራ ዝር ዝር ውስጥ 'የተጣላ ማስታረቅ' የሚል አለበት እንዴ?"* አለው። ከላይ እንዳየነው እንደ ድፋቸው ጥሩም ሆነ መጥፎ፥ ፈጣን የሆነ መልስ መስጠት የሚችሉ፥ ልዩ ችሎታ ያላቸው አንዳንድ ሰዎች አሉ። ከላይ ያየናቸው መልሶች "ትክክል ናቸው" ማለታችን ሳይ ሆን፥ አንዳንድ ሰዎች ወቅታዊ የሆነ መልስ የመመለስ ችሎታ እንዳ ላቸው ለማሳየት ብቻ ነው።

ሠለሞን *"ተገቢውን ቃል በተገቢው ቦታ መናገር እጅግ ያስደሰ ታል"* (ምሳሌ 15፥23) ሲል፥ ተገቢ የሆነው ቃል እንዴት ይታወ ቃል? ብለን መጠየቃችን አይቀርም። "ተገቢውን ቃል በተገቢ ቦታና

ጊዜ በመናገር ከሚደነቁት መካከል ተወዳዳሪ የሌለው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በመስቀል ላይ ሆኖ የተናገራቸው ንግግሮች፥ እንዲሁም የሃይማኖት መሪዎች በነገር ሊያጠምዱት ለጠየቁት ጥያቄዎች የሰጣቸው ረቂቅ የሆኑ መልሶች የሚደነቁ ናቸው። ተገቢውን ቃል በተገቢው ጊዜና ቦታ መናገራችንን የምናውቀው በንግግራችን ፍሬ ወይም ውጤት ነው። ተገቢውን ቃል በተገቢው ቦታና ጊዜ ከተናገርን፥ ንግግራችንን በሚሰማው ሰው ሕይወት ውስጥ እውነተኛ የሆነ ለውጥ ማምጣት ይቻላል። በተገቢው ጊዜ የተናገርናቸው ተገቢ ንግግሮች፥ ከሰሙት ሰዎች አዕምሮ ለዓመታት ጨርሶ አይጠፉም። እኛ ተናጋሪዎቹ ብንረሳው፥ የሰሙን ሰዎች ግን ጨርሶ አይረሱትም። "ከብዙ ዓመት በፊት ያስተማርከው፣ የሰበክው፣ የመከርከኝ ቃል ሕይወቴን ለውጠታል፥ እስከ ዛሬ ድረስ ከአዕምሮዬ አይጠፋም" የሚሉኝ ብዙ ሰዎች አጋጥመውኛል። እኔ በበኩሌ ምን ብዬ እንደተናገርኩ አብዛኛዎቹን ረስቼአቸዋለሁ።

"ተገቢውን ቃል በተገቢው ጊዜና ቦታ ለመናገር" የንግግር ችሎታን፥ ወይም ጥበብን አይጠይቅም። አንዳንድ ሰዎች ቃላት እየመረጡ ለጆሮ የሚጣፍጥ ንግግር ማድረግ ይችላሉ። ንግግራቸው ግን የሰውን ሕይወት የሚለውጥ፣ የሚያጽናና፣ በተስፋ የሚሞላና የሚባርክ ላይሆን ይችላል። በበኩሌ መንፈሴን ከፍ ያደረጉ፣ ያጽናኑኝና ያበረታቱኝ ብዙ ደብዳቤዎች አግኝቼአለሁ። በነርሱም ብዙ ተጽናንቻለሁ። ከሁሉም የበለጠ የማልረሳው አለ። በአገልግሎቴ ያለብኝን ትግል፥ አልፎ አልፎ የሚሰማኝን ብቸኝነት በቅርብ የሚያውቅ ወንድም፥ አገልግሎቴን ለመርዳት በየወሩ ከሚልከው ቼክ ጋራ፥ በትንሽ ወረቀት አንዳንድ ስዕሎችን እየሳለ፥ "በርታ! አይዞህ! ጋሼ ብረቱ" እያለ የሚልከልኝ ወቅታዊ የሆነ የማበረታቻ ቃል፥ በአሥር ገጽ ከተጻፈ ደብዳቤ የበለጠ ኃይል ነበረው።

ተገቢውን ቃል በተገቢው ጊዜና ቦታ በማግኘት ከሀዘናቸው የተጽናኑ፥ ከተስፋ መቁረጥ ስሜት ውስጥ የወጡ ብዙዎች አሉ። አንድ ጊዜ በአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በታማኝነት ለብዙ ዓመት የሰንበት ትምህርት አስተማሪ ሆኖ በትህትናና በቅንነት የሚያገለግል በዕድሜው ጠና ያለ ሰው ነበር። አንድ ቀን የመጋቢው ሚስት በመንፈስ ቅዱስ አሳብነት፥ በታማኝነት ስለሚሰጠው አገልግሎት አመስግና አጭር ደብዳቤ ጽፋ ላከችለት። በዚያን ወቅት ያ ሰው በቅርቡ ጡረታ የወጣበት ጊዜ ስለነበረ፥ ልቡ በሀዘን የተሞላበት ጊዜ፣ አንድም ልጁ አካባቢውን ለቃ ርቃ በመሄዷ ብቸኝነት የተሰማው፣ ስለ ወደፊት ሕይወቱ ሲያስብ ጨለማ ሆኖ የታየው ጊዜ ነበር። የጻፈችለት ደብዳቤ ይህን ያህል በጥሩ ቃላት ያሸበረቀ፥ ሙገሳ የሞላበት ሳይሆን ተራ ደብዳቤ ቢሆንም፥ መጽናናት ከምንጊዜውም የበለጠ በሚያስፈልገው ሰዓት የደረሰው በመሆኑ፥ ልዩ የሆነ ኃይል ሰጠው። ከአንድ ዓመት በኋላ ያ ደብዳቤ በሕይወቱ ውስጥ ያደረገለትን ሲገልጽ፥ "በሕይወቴ ተስፋ ስቆርጥ፥ ሳዝን ያን ደብዳቤ ከአስቀመጥኩበት ሥፍራ አውጥቼ እንደ ገና አነበዋለሁ። በዚያም ውስጥ ልዩ የሆነ መነቃቃትና መጽናናት አገኝበታለሁ" አለ።

በሌላ ጊዜ ደግሞ ከላይ የጠቀስናት ሴት "ተገቢ የሆነውን ቃል በተገቢው ጊዜና ቦታ" ስትናገር እናያታለን። በዚያው አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ከሰንበት አምልኮት በኋላ አማኞች ለሻይና ለቡና ሲሰበሰቡ፥ በካንሰር በሽታ ተይዛ የምትሰቃይ ሚስት የነበረችውን አንድ ሰው ቀረብ ብላ ማነጋገር ጀመረች። በተፈጥሮው ሩህሩህ ሰው ቢሆንም፥ የሚሰማውን የውስጥ ስሜት ገልጾ መናገር የማይችል ሰው ነበር። ይሄም ባህሪው ከሚስቱ ጋር ሊያቀራርበው እንደማይችል አወቀች። ሚስቱ የምትወስደው የኪሞቴራፒ ሕክምና ሊከብዳት ብዙ እየከፋት ታለቅሳለች። ሚስቱ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ስትሆን፥ ምን ማለት እንዳለበት ስላላወቀ ፍጹም ግራ ግብት ያለው ወቅት ነበር። በዚያ በቡናና በሻይ ሰዓት፥ የሰዎች ጩኸት በበዛበት ሥፍራ፥ በዚያ አጭር ጊዜ፥ ሀዘን ውስጡን ለሞደሸው ሰው ምን ብላ መናገር እንዳለባት ግራ ገብቷት ነበር። ምን ያህል እንዳዘነችለት በሁኔታዋ ገልጻ፥ *"አሁን በዚህ አጭር ጊዜና ጫጫታ በበዛበት ሥፍራ ብዙ ቃል ልነግርህ አልችልም።* እቤት ና ብዬ ብልህም እንደማትመጣ አውቃለሁ። ስለሆንም ባለችኝ አጭር ጊዜ የምነግርህ ነገር ቢኖር፥ ሚስትህ ሆድ ብሏት ሲታለቅስ ምንም ሳትናገር፥ እጁን ብቻ ያዛት። ምን ብዬ ላጽናናት ብለህ አትጨነቅ። እቀፋትና የፈለገችውን ያህል እንድታለቅስ ነጻነት ስጣት" አለችው። ያን ሰው ሚስቱ እስክትሞት ድረስ ያጸናውና ያቆመው ያ ምክር ነበር። በሰው ሕይወት ውስጥ ይህን የመሰለ ለውጥ ለማምጣት የሚፈልግ ክርስቲያን ሁሉ፥ አልፎ አልፎ

መንፈስ ቅዱስ ወደ ልቡ ላመጣቸው ሰዎች "የማነቃቂያና አይዞህ! አይዞሽ" የሚል ቃል መስጠት ትልቅ አገልግሎት ይሆናል። በእግዚ አብሔርም ፊት ትልቅ ዋጋ አለው። ክርስቲያኖች እርስ በርሳቸው የቃላት ጦርነት ከሚያካሂዱ፥ ተገቢውን ቃል፥ በተገቢው ሰዓት፥ ለተገቢው ሰው መላክ ቢችሉ ለቤተ ክርስቲያን ምን ያህል ትልቅ ፈውስ ያመጣ ነበር? ተገቢውን ቃል በተገቢው ጊዜ መናገር እንዴት ይቻላል?

## 2.1. ንግግራችን በመልካም ሰላምታ ይጀምር

ቀናችንን የምንጀምረው በምን ዓይነት ሁኔታ ይሆን? በመልካም ቃል ነው ወይስ በክፉ ቃል? ድምጻችን አስደንጋጭ ነው ወይስ በፍቅር የተሞላ ነው? መጣልን ይሉናል ወይስ እንግዲህ ጀመረው!" ይሉናል? ምርጫው የራሳችን ነው። ጥዋት ከእንቅልፍ እንደነቃችሁ ልጆች ካሏችሁ፥ ልጆቻችሁ በሰዓቱ ትምህርት ቤት እንዲሄዱ ለመ ቀስቀስ መኝታ ቤታቸው ስትገቡ ፈታኝ ነገር ያጋጥማችኋል። የበሉ በትን ሳህን አንስተው ወጥ ቤት በማስቀመጥ ፈንታ ትተውት ተኝተ ዋል። ምግብ ወለሉ ላይ ተደፍቶ ወለሉ ሌላ መስሏል። የቆሸሸውን ልብሳቸውን ቆሻሻ ልብስ ከሚቀመጥበት ቅርጫት ውስጥ በማስቀመጥ ፈንታ ክፍላቸው ውስጥ አዝረክርከውታል። በአጠቃላይ ክፍላቸው ቦምብ ፈንድቶ ትርምስምሱን ያወጣው ይመስላል። ቀደም ሲል መመ ሪያ አውጥታችሁ ሰጥታችኋቸዋል። ይሁን እንጂ አንዱንም መመሪያ አልጠበቁም። ከዚህ ሁሉ በላይ በሰዓቱ ተነስተው ለትምህርት ቤት መዘጋጀት ሲገባቸው ገና ከእንቅልፋቸው አልተነሱም። ያኔ ውስጣ ችሁ በቁጣ ይሞላል። ያጋጠማችሁን ሁኔታ የምታስተናግዱት በምን ዓይነት ይሆናል? እጃችሁን ወደ ሰማይ ዘርግታችሁ "ሃሌ ሉያ!" እን ደግትሉ እርግጠኛ ነኝ። በውስጡ አልፈለሰሁና ስሜቴን አውቃ ለሁ። ከረንቲ ያስጨብጣል። የለበሰውን ብርድ ልብስ ከላዩ ገፍችሁ፥ የመጣላችሁን ቃል ከአፋችሁ አውጥታችሁ ትወረውራላችሁ። *"... አንተ ደደብ! ዝርክርክ! የማትረባ! ሰነፍ! ያለ አንቅልፍ ሌላ ነገር መሥራት አይሆንልህ... እኔ በአንተ ዕድሜ በነበርኩበት ጊዜ ሌሊት ተነስቼ ለወላጆቼ ሰንት ሥራ እሠራ ነበር!"* ብላችሁ እንደ መብረቅ ትጮኽብታላችሁ። በዚያን ወቅት የምትናገሩት ቃል ምን ያህል



ጎጂ መሆኑን አታውቁትም። ሌላው ቀርቶ በጣም ከመናደዳችሁ የተ ነሳ ክርስቲያን መሆናችሁንም ትረሱታላችሁ። ጸጋ የማይሰጥ ቃል ከአፋችሁ ትወረውራላችሁ። ቀኑን በዚህ ዓይነት ስትጀምሩ፥ ልጃች ሁም ቀኑን በመሰደብ እንዲጀምር ማድረጋችሁ፥ ትንሽ ቆይቶ ሳይጸ ጽታችሁ አይቀርም። አንዴ ከአፋችሁ ወጥቷልና መልሳችሁ ልት ውጡት ስለማትችሉ፥ ህሊና ካላችሁ ቀኑን ሙሉ ሲጸጽታችሁ ይው ላል። የእናንተን ጩኸትና ስድብ ሲሰማ በርግጎ ይነሳል። ጥፋቱንም ቢያውቅ የእናንተ ስድብና ወቀሳ የበለጠ ያበሳጨዋል። ስለ እናንተ ያለው ፍቅር የቀነሰ ይሆናል። ዕድሜው ደርሶ ከቤት የሚወጣበትን ቀን መናፈቅ ይጀምራል። ክርስቲያኖች ከሆናችሁ፥ ቤተ ክርስቲያን ስትሄዱ ከሌሎች ሰዎች ጋር የምትናገሩት ቃል ከቤተሰባችሁ ጋር ከምታደርጉት ፍጹም የተለየ በመሆኑ፥ ይታዘባችኋል። ሁለት ዓይነት መልክ ያላችሁ ግብዞች ናችሁ ይላል። በዚህ ዓይነት ቤተ ክርስቲያን "ግብዞች" የሚሰበሰቡበት ሥፍራ ነው ብሎ ስለሚያስብ፥ ቤተ ክርስ ቲያን መሄድን ይጠላል።

እዚህ ላይ ወላጆች ሊያውቁት የሚገባ አንድ ነገር አለ። ጥንት ወላጆቻችሁ ቃላት ሳይመርጡ "ይጎዳቸው ይሆን?" ብለው ሳያስቡ፥ የፈለጋቸውን ቃል ወርውረውባችሁ፥ የተናገሯችሁን ሁሉ በጸጋ ተቀ ብላችሁ ምንም ሳትጎዱ አድጋችሁ ይሆናል። "ክፉ ቃል የሚሰብር ቢሆን ኖሮ እኔን ይሰብረኝ ነበር። እኔ ምንም ካልሆንኩ ልጆቼም ምንም አይሆኑም ብላችሁ" እናንተ በተደበደባችሁበት የስድብ ዱላ ልጆቻችሁን እንዳትደበድቡ ተጠንቀቁ። እኛ እንደቻልነው የዘመኑ ልጆች የስድብ ዱላ አይችሉም። አንድ ሰው ለልጆቹ የሚያደርገውን ጥንቃቄ ሲገልጽ፥ *"እኛ ልጆች በነበርንበት ጊዜ የወላጆቻችን አሽከ ሮች ነበርን። እኛ ደግሞ በተራችን ወላጆች ስንሆን ደግሞ፥ የልጆቻ ችን ሬቶች በመሆን ፈንታ አሽከሮቻቸው ሆንን"* አለ። ጥሩ አባባል ነው። ቀናችንን ከላይ በተመለከትነው ዓይነት በጭቅጭቅና በክፉ ቃል መጀመር ለራሳችንም ሆነ ለልጆቻችን ጤና አይሰጥም። ሁኔታው የሚያበሳጭ ቢሆንም በትዕግሥት ተሞልተን፥ ከተኛበት አልጋ ጠርዝ ላይ ቁጭ ብለን ራሱን እያሻሸን፥ "ነበዝ እንደምን አደርክ? ብዙ ተኝተሃል አሁን ይበቃል! ተነስ!" ብለን ብንቀሰቅሰው፥ ተገቢውን ቃል በተገቢው ጊዜ መናገራችን ይሆናል።

ባል ቀኑን ሙሉ በአድካሚ ሥራ ሥጋውም ሆነ መንፈሱ ተዳክሞ፣ በአለቃው ተበሳጭቶ፣ አስቸጋሪ ከሆነ የሥራ ባልደረባው ጋር ተጨቃጭቆ፣ በጠቅላላው ደስ የማያሰኝ ጊዜ አሳልፎ ወደ ቤቱ ይመጣል። በምን ዓይነት ሁኔታ እንዳሳለፈ የማታውቅ ሚስቱ፣ በቤቷ ውስጥ አንዳንድ ሁኔታዎች ልክ ሳይመጡላት ውላ ልክ ባሏ በሩን ከፍቶ ሲገባ፣ ብሶቷን በእርሱ ላይ መወጣት ትጀምራለች። "እንደምን ዋልክ?" የሚለውን ሠላምታዋን ከማስቀደም በፊት፣ ወትሮ እቤት ከሚመጣበት ጊዜ ግማሽ ሰዓት በማሳለፉ፣ *"ለምን አንደኛህን እዚያው አታድርም? ምግብ ጠረጴዛ ላይ አዘጋጅቼ አንተን መጠበቁ ለሁንስ ሰለቸኝ! ዛሬስ ምን ሆንኩ ልትል ነው? አንተ እንደሆንክ ምክንያት አታጣም"* በማለት ተበሳጭቶ የመጣውን ባሏን በነገር ትቀበለዋለች። ጊዜውን ያልጠበቀ ንግግር በመሆኑ፣ ምክንያቱን በማ ስረዳት ፈንታ እርሱም የመጣለትን ከፉ ቃል አንጣጥሮ ይተኩሰባ ታል። *"ምን አለ አንቺማ ቤት ተቀምጠሽ ተመችቶሻል። አለቃዬ ሆነሽ በዚህ ሰዓት ግባ! በዚህ ሰዓት ውጣ ትይኛለሽ። ምነው አለቆቼ በዙ! ለሁንስ ሰለቸኝ"* ብሎ በሩን ከፍቶ ይወጣና አምሽቶ ይመለ ሳል። በዚህ ዓይነት በመካከላቸው ያለችው ትንሽ ቀዳዳ ትሰፋና መጪ ረሻ ላይ በሁለቱም ላይ ትልቅ ችግር ያስከትላል። ይሄን ዓይነቱ ጊዜውን ያልጠበቀ ንግግር ገንቢ ባለመሆኑ ሰላምን ያደፈርሳል።

ሚስትም ቀኑን በከባድ ሁኔታ የምታሳልፍበት ጊዜ አለ። ከጥዋት እስከ ማታ ድረስ ጎንበስ ቀና ስትል ውላለች። የጣደችው ምግብ ሲያ ርባት፣ የምታብሰለው ነገር ገንፍሎ እሳቱን ሲያጠፋባት፣ ሕጻናት ልጆቿ ሲጫጫሁባት ውላለች። ባለቤቷ መጥቶ ምን ዓይነት ከባድ ቀን እንዳሳለፈች ነግራው መተንፈስ ስለምትፈልግ የሚመጣበትን ሰዓቱንና ደቂቃውን ትቆጥራለች። እንደማይደርስ የለምና ሰዓቱ ደርሶ ባሏ በሩን ከፍቶ ይገባል። ምግብ ጠረጴዛው ላይ ተደርድሮ ይጠብቀኛል ብሎ አስቦ ነበር። ባለቤቱ ግን ገና ምግቡን አብስላ አልጨረሰችም። "ቀኑ እንዴት ነው? እንደምን ዋልሽልኝ?" ብሎ በመጠየቅና ሰላምታ በመስጠት ፈንታ፣ *"ቀኑን ሙሉ ምን ሲታደርጊ ውለሽ ነው ለሁን ምግብ የምትሠሪው? ለሁንስ አበሳሽው!"* ይላታል። እርሷም ይታዘንልኛል ብላ ስትጠብቅ፣ የበለጠ የወቀሳ ቃል መሰማቷ ያበሳጫትና አጸፋውን ትመልሳለች። *"እኔ እኮ ሚስትህ እንጂ ገረድህ አይደለሁም። በዚህ ሰዓት እራት ይድረስ ብለህ ትዕዛዝ ልትሰጠኝ ለትችልም"* ብላ ምድጃውን አጥፍታ ያለውን እንዳለ ትታ መኝታ ቤት ሄዳ አልጋዋ ላይ በደረቷ ትተኛለች። የዚህ ችግር ምክንያት ጊዜውን ያልጠበቀ ንግግር ነው። ሁኔታውን ማብረድ ካልቻሉ፣ ቤታቸውን፣ ፍቅራቸውን ጨለማ ያደርግባቸዋል።

## 2.2. <u>ንግግራቸን የሌላውን ሰው ስሜት የሚጠብቅ ይሁን</u>

ተገቢውን ቃል በተገቢው ጊዜ የሚናገር ሰው የሌላውን ሰው ስሜት ይጠብቃል። መጽሐፍ ቅዱስ *"ከሚያዝኑት ጋር አዘኑ፣ ደስ ከሚላቸው ጋር ደስ ይበላችሁ"* ሲለን፣ ከሁኔታው ጋር የማይስማማ ነገር ማድረግ እንደሌለብን ሲገልጽ ነው። ለቅሶ ቤት ሄደን አንስ ቅም፣ እንዲሁም ሠርግ ቤት ሄደን አናለቅስም። ሀዘን ደርሶባቸው የተቀመጡ ሰዎች መሰማት የሚፈልጉት የሚያጽናናቸውን ቃል እንጂ፣ የሚፈርድባቸውንና የሚወቅሳቸውን ቃል አይደለም። ሰዎች መጽናናትን ሲፈልጉ፣ ለሚሰማቸው ሁሉ ልባቸውን አፍስሰው ይነግ ሩታል። የሚነግሩትም *"ምን ዓይነት ደካማ ሰው ነህ? እንዴት በዚህ በትንሽ ነገር ትረበሻለህ? እኔ አንተን ብሆን ኖሮ ንቄ አተወው ነበር"* ብለው ዝቅ አድርገው እንዲመለከቷቸው ሳይሆን፣ *"ምን ያህል እንደ ጎዳህ ይገባኛል! በጣም አዝናለሁ! አይዞህ! በትዕግስት ቻለው! ይሄም ያልፋል"* ብሎ እንዲያጽናናቸው ነው። ምናልባት በእግዚአብሔር ላይ የተቆጡ ሊሆኑ ይችላሉ። የተቆጡበት ምክንያት እኛ የማንስማ ማበት፣ ፈጽሞ ሊያስቆጣቸው የማይገባ ነገር ይሆናል። "ልክ አይደ ለህም" ብሎ መከራከር አስፈላጊ አይደለም። በዚህ ወቅት የሚፈል ጉት የሚያጽናናቸውን ቃል፣ ሀሳባቸውን የሚረዳላቸውን ሰው ነው። በዚህ ሁኔታ ላለ ሰው ምን እንበለው?...

> *"...ያለህበት ሁኔታ በመጠኑም ቢሆን ይገባኛል። ሁኔታው በጣም አሳዝኖኛል።"*
>
> *"...ምን እንደምልህ አላውቅም። ይሁን እንጂ፣ በጸሎት አብረህ እቆማለሁ።"*
>
> *"...እኔ ማድረግ ያለብኝ ነገር ካለ ንገረኝ። የተቻለኝን ሁሉ ለማድረግ እሞክራለሁ!"*

በችግር ውስጥ የሚያልፍ ሰው ከላይ የሰማነውን ዓይነት ንግግር እንጂ፥ የፍርድ፥ የትዝብት ቃል መስማት አይፈልግም።

## 2.3. ንግግራችን አይርዘም

ተገቢውን ቃል በተገቢው ጊዜ ለመናገር፥ ለማለት የምንፈልገውን በአጭሩ እንበል። በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚያልፉ ሰዎች ብዙ ጊዜ የሚሰማቸውን ሰው ይፈልጋሉ። የሚሰብካቸውን፥ ወይም ረጅም ንግግር የሚያደርግላቸውን ሰው አይፈልጉም። ሌላው ቀርቶ ተናግረው ሳይጨርሱ በየመካከሉ የሚያቋርጣቸውን ሰው እንኳ አይፈልጉም። በመጥፎ ሁኔታ ላይ ያሉ ሰዎች ሀሳባቸውን ሰብስበው ጥቂት ደቂቃም መስማት አይችሉም። ቢሰሙም ከተነገራቸው ነገር ውስጥ ብዙውን አያስታውሱትም። አንዳንድ ጊዜ ትልቅ ነገር ነው ብለን የምናስበው ነገር ብዙ ንግግር የሚያስፈልገው ስለሚመስለን፥ ረጅም ስብከት መሰበክ እንጀምራለን። ብዙ በመናገር የማታምን አንዲት እናት ልጆቿን "ጥርሳችሁን ቦርሹ!" ለማለት "የጥርስ ብሩሽ!" ትላቸዋለች። ልጆቿ ምን ማለቷ እንደሆነ ስለሚገባቸው ማድረግ ያለባቸውን ያደርጋሉ። በሀዘን፣ በተስፋ መቁረጥና በብስጭት ውስጥ የሚያልፍ ሰው መስማት የሚፈልገው ጥቂት ቃል እንጂ ረጅም ስብከት ወይም ንግግር እንዳልሆነ እንወቅ።

## 2.4. ለማሳመን አንከራከር

ተገቢውን ቃል በተገቢው ጊዜ መናገር፥ በችግር ላይ ያለውን ሰው ለማሳመን የምናደርገውን ክርክር አይጨምርም። ተከራክሮ የማሳመን ጊዜ አለው። ጊዜውን ያልጠበቀ ክርክር፥ ጊዜን ያጠፋል፥ ጉልበትን ያባክናል፥ ያዘነውን ሰው ያበሳጫል። "ከደረሰብኝ መጥፎ ሁኔታ የበለጠ ያሳዘኝ፥ ያጽናናኛል ብዬ የልቤን ባጫወተው፥ ራሱን በማመጻደቅ ፈርዶብኝና ተከራክሮኝ መሄዱ ነው" ብለው ቅሬታቸውን የሚያሰሙ ሰዎች አሉ። ዓላማችን ያም ባይሆን፥ በችግር ውስጥ ያሉ ሰዎች ያን መስሎ ስለሚሰማቸው ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አለብን። በመከራከር ራሳችንን እናደክማለን እንጂ ማንንም አንጠቅምም። እንዲያውም ያለንን ፍቅርና አንድነት ያሻክርብናል። በመከራከር "ትንሹን" ተራራ አድርገን እናሳድገዋለን። በቀላሉ የሚፈታውን የበለጠ የተወሳሰበ እናደርገዋለን።



## 3. መልካም ምላስ፥ ንጹህ ምላስ ነው።

ያለምንም ጥንቃቄ የመጣላቸውን የሚናገሩ ሰዎች አሉ። ብዙዎች የውሃ፥ የዓየርና የመሬት መበላሸት (pollution) ያሳስባቸዋል። የውሃ መበላሸት፥ የዓየር መበላሸት (air pollution) በሰዎች ጤንነት ላይ የሚያደርሰው ጉዳት የማይታያቸው ሰዎችም አሉ። መጥፎ ዓየር (pollution) ባለበት ቦታ ያለን ውሃ መጠጣት፥ ሰውነት ውስጥ ገብቶ ደምን ይመርዛል። መጀመሪያ ላይ በግልጽ ባይታወቅም፥ እየቆየ ሲሄድ በጤንነት ላይ ከፍተኛ ጉዳት እንደሚያመጣ የታወቀ ነው። የዓየር መበላሸት እንደሚያሳስበው ያህል፥ በዚያው መጠን የሰዎች የንግግር መበላሸትም ሊያሳስበን ይገባል። ስለሚበሉት፥ ስለሚጠጡት፥ ስለሚስቡት ዓየር የሚጨነቁትን ኢየሱስ *"ሰውን የሚያረክሰው ከአፍ የሚወጣው ነው እንጂ ወደ አፍ የሚገባው አይደለም"* ይላቸዋል (የማቴ. 15፥11)። አንዳንድ ሰዎች ማንንም ሳይነኩ "ጸያፍ ቃል" የሚናገሩ አሉ። እንደነዚህ ዓይነቶቹ "ጸያፍ ቃል መናገሩ መጥፎነቱ እምኑ ላይ ነው? ማንንም እስካልነካሁ ድረስ የፈለግሁትን ብናገር ምን አለበት?" በማለት ክፉ ቃል ለመናገር ለራሳቸው ነጻነት ይሰጡታል። መልካም ምላስ፥ ክብር ለሚገባው እግዚአብሔር ክብርን ይሰጣል፥ ጸጋ የሚሰጠውን፥ ጠቃሚ የሆነውን ብቻ ከሰዎች ጋር ይነጋገራል።

"ተራ ንግግር" መናገር የሚወዱ ሰዎች የንግግራቸው ዋና አርዕስት የእግዚአብሔር ስምና ፍትወተ ሥጋ (sex) ነው። አንዳንድ ንጹህ ምላስ የሌላቸው ሰዎች፥ ንግግራቸው በብልግና የተሞላ ነው። የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ ሲጠሩ አይዘገንናቸውም። የብልግና ወይም ጸያፍ ቃል መናገር ልዩ ደስታ ይሰጣቸዋል። በፀያፍ አነጋገራቸው ምክንያት ራሳቸውን ማስናቃቸውና ዝቅ ማድረጋቸውን አይረዱም። የእግዚአብሔርን ስም ያለአግባብ መጥራት ማንንም አይጎዳም ብለው ያስባሉ። እግዚአብሔርን እንደሚያስቆጣው ግን አልተገነዘቡትም። *"ኖእኔን የአምላክህን ስም በከንቱ አታንሣ ምክንያቱም እኔ ስሜን በከንቱ የሚያነሣውን ሁሉ እቀጣዋለሁ"* ይላል (ዘጸ. 20፥7)።

የእግዚአብሔርን ስም ያለአግባብ መጠቀም፥ የእግዚአብሔርን ኃያል ነትና ክብር መናቅ፥ የሚገባውን አክብሮት መከልከል ነው። ዘማሪው *"ክብር የሚገባውን የእግዚአብሔርን ስም አመስግኑ፥ የቅድስናው ክብር በሚገለጥበት ጊዜም ለእግዚአብሔር ስገዱ"* በማለት ይመክረ ናል (መዝ. 29፥2)። ጳውሎስም *"ይልቅስ ለእግዚአብሔር ምስጋና አትርቡ እንጂ የሚያሳፍርና ረብ የሌለው ወይም ጸያፍ ነገር መናገር አይገባችሁም፥ ምክንያቱም እንዲህ ያለ ነገር ለእናንተ ተስማሚ አይደለም"* ይላል (ኤፌ. 5፥4)። ጳውሎስ ይህን ምክር የሰጠው ለዓለ ማውያን ሳይሆን ለክርስቲያኖች በመሆኑ መጠንቀቅ ያስፈልገናል።

## 4. መልካም ምላስ የርህራሄና የፍቅር ቃል ይናገራል

ጳውሎስ *"...እንዴት እንድትመልሱ እንደሚገባችሁ ታውቁ ዘንድ ንግግራችሁ ሁልጊዜ በጨው እንደተቀመመ በጸጋ ይሁን"* (ቆላስይስ 4፥6) ሲል ይመክረናል። "በጸጋ" የተሞላ ንግግር ማለት፥ ከእኛ መል ካም ነገር መስማት የማይገባው መጥፎና ክፉ ሰው ቢሆንም፥ በመልካም ቃል ማነጋገር ማለት ነው። ክፉ ቃል ተናግሮ አስቀይሞን እንኳን ቢሆን፥ ክፉ በመመለስ ፈንታ በጎ መመለስ ማለት ነው። የፍቅር ቃል ለመናገር የፍቅር ሰው መሆንን ይጠይቃል። ጳውሎስ *"...ፍቅር ከሌለኝ እንደሚጮህ ናስና እንደሚንኳኳ ጸናጽል መሆኔ ነው"* ይላል (1 ቆሮ. 13፥1)። የሚንኳኳ ጸናጽል በኦርኬስትራ ውስጥ ጠቃሚ የሆነ ድምጽ አለው፥ ከኖቱ ውጪ ከሆነ ግን የኦርኬስትራውን ድምጽ ያበላሻል። የሚጮኽ ናስም አስፈላጊ የሚሆንበት ጊዜ አለ። ከእንቅ ልፋችን ቀስቅሶ ያስነሳናል፥ የእሳት አደጋ መኖሩን ይነግረናል፥ እን ዲሁም ተማሪዎች ወደ ክፍል የሚገቡበትንና የሚወጡበትን ሰዓት ለመግለጽ ይደውላል። ይሁን እንጂ ዝም ብሎ ቢደውል ወይም ቢጮኽ ጆሮን የሚያደነቁር ከመሆኑ ሌላ ያበሳጫል። ርህራሄ ወይም ፍቅር ያልተቀላቀለበት ምላስም ልክ እንደዚሁ ነው። ንግግራችን በጥሩ ቃላት፥ ደስ በሚል ድምጽ ሊቀርብ ይችላል። ርህራሄ ከጎደ ለው ግን በመጥቀም ፈንታ ይጎዳል። ሠለሞን ስለ መልካም ሴት ሲናገር፥ *"...ለፍዋን በጥበብ ትከፍታለች፥ የርኅራሄም ሕግ በምላስዋ*



*አለ"* ይላል (ምሳሌ 31፥26)። ዝቅ ይልና *"...ልጆችዋ ይነሣሉ፥ ምስ ጋናዋንም ይናገራሉ፥ ባልዋ ደግሞ እንዲህ ብሎ ያመሰግናታል..."* ይላል (ምሳሌ 31፥28)። የፍቅርና የርህራሄ ምላስ መጀመር ያለበት ከራስ ቤት እንደሆነ ግልጽ ነው። አንዳንድ ሰዎች ለውጪ ሰዎች ንግግራቸው ማር ማር ይላል፥ ቤታቸው ውስጥ ግን ከአፋቸው የሚ ወጣው ቃል መራራ፥ ፍጹም የሚዘገንና የሚያስደነግጥ ነው። ክርስ ቲያን ባልና ሚስት በፍቅርና በርህራሄ እርስ በርሳቸው ቢነጋገሩ፥ ሁሉንም ባይሆን፥ አንዳንዱን ችግራቸውን ማቃለል ይችላሉ።

ባልም ሆነ ሚስት ቀኑን ሙሉ በሥራ ደክመው፣ በአለቃቸውና እንዲሁም አብረውት ከሚሠሩት አስቸጋሪ ሰው በሚወረወሩ ቃላት ተጎድተው፣ ወደ ቤታቸው ሲገቡ፥ በርህርሄና በፍቅር የተሞላ ንግግር ቢጠብቃቸው ምን ያህል ነፍሳቸው ደስ ይለው ነበር? ይሁን እንጂ፥ እቤታቸው ውስጥ የሚጠብቃቸው ሰው ምን ዓይነት ምላስ እንደሆነ ስለሚያውቁ፥ ቤታቸው የሚገቡት በፍርሃትና በስጋት ተሞልተው ነው። የርህራሄና የፍቅር ንግግር የሚያስፈልጋቸው በዕድሜ የተለቁት ብቻ ሳይሆኑ፥ ልጆችም ያስፈልጋቸዋል። ትምህርት ቤታቸው አንዳ ንድ መጥፎ ልጆች የቅጽል ስም አውጥተው እየሰደቧቸው፥ ሌሎች ባጠፉት ጥፋት፥ እውነቱን ባለማወቅ አስተማሪዎቻቸው እንደጥፋ ተኛ ቆጥረዋቸው ተዘልፈው ውለው፥ እቤታቸው ሲገቡ ደግሞ "ውሃ ቀጠነ" በሚሉ ወላጆች ክፉ ቃል ሲወረወርባቸው የሚገቡበት የሚጠ ፋቸው መሆኑን ወላጆች ሊረዱ ይገባል። አሜሪካን አገር ራሳቸውን የሚገድሉ ልጆች ቁጥር ከምንጊዜውም የበለጠ ከፍ ያለ መሆኑን ምሁራን ይናገራሉ። ይሄ ችግር የኢትዮጵያውያንን ቤተሰብንም እን ዳያስደነግጥ አስቀድሞ መጠንቀቅ ያስፈልጋል። አንዳንድ ክርስቲ ያኖች ልጆቻቸውን ሲቀጡ፥ ክርስቲያኖች መሆናቸውን ይረሳሉ። *"አንተ ደደብ... የማትረባ"* በማለት እየሰደቡ ልጆቻቸውን ያስመር ራሉ። ጳውሎስ ክርስቲያን ወላጆችን *"ወላጆች ሆይ! ተስፋ እንዳይቆ ርጡ ልጆቻችሁን በቁጣ አታሳመርሯቸው"* (ኤፌ. 3፥21) እያለ ይመክራል። ሠለሞን *"ልጄ ይነሣሉ፥ ምስጋናዋንም ይናገራሉ..."* ያለው፥ ቀንና ማታ ልጆቿን በቁጣ፥ በስድብና በጉላ የምታስመርርን እናት እንዳልሆነ ማወቅ ያስፈልገናል።

አንዳንድ ክርስቲያኖች እንደፈለጋቸው የሚናገሩት፥ *"ዋተናገር*

*ኩት እውነት እስክ ሆነ ድረስ ምንም አይደለም"* በማለት ነው። ጳውሎስ *"...እውነትን በፍቅር እየተናገርን..."*(ኤፌ. 4፥15) ሲል፥ እውነትን መናገር ብቻ ሳይሆን፥ የምንናገረው እውነት በፍቅር የተቀመመ መሆን እንዳለበት መግለጹ ነው። ባሏ የብብት ጠረን ማጥፊያ (ዲዮድራንት) ሳይቀባ በመውጣቱ ሰውነቱ መሽተቱን ያወቀች ሴት ባሏን፥ *"...ብብትህ ይሸታልህ... ዲዮደራንት መቀባትን አትርሳ ብዬ ሁልጊዜ እነግርሃለሁ አትሰማኝም..."* ብላ ብትጮኽበት፥ እውነቱን በፍቅር ስላልነገረችው ትክክል አይደለችም። ወይም *"አፍህ ይሸታል ...አንተ ሁልጊዜ እውነቱን ሲነግሩህ መቀበል አትፈልግም፥ ሌላ ሰው ከሚነግርህ እኔ ብነግርህ ይሻላል"* ብትል በመካከላቸው የበለጠ ጠብ ያመጣል። እርግጥ ነው የተናገረችው እውነት ነው። በተለያየ ምክንያት አንዳንድ ሰው አፉ ይሸታል። የሴቶች አፍንጫ በተፈጥሮ በማሽተት ኃይለኛ ነው። ባሎች ይህን እውነት ከመካድ ይልቅ መቀበሉ ይሻለናል። ይሁን እንጂ፥ የሚሰቶችም ምክር፥ የባል ስሜት እንዳይጎዳ በፍቅር የተቀመመ መሆን ያስፈልገዋል። አንዳንድ አዋቂ ሴቶች፥ ለባላቸው ስሜት የሚጠነቀቁ፥ "አፍህ ይሸታል" ከማለት ይልቅ ከቦርሳቸው ውስጥ ማስቲካ አውጥተው ይሰጡታል። ባልየውም ምን ማለቷ እንደሆነ ይገባውና መስቲካውን ተቀብሎ ማኘክ ይጀምራል። አንዳንዱ ደግሞ መስቲካውን ተቀብሎ በማኘክ ፈንታ፥ "ያልሽውን አልቀበልም" የሚል መልዕክት ለማስተላለፍ፥ መስቲካውን እኪሱ ውስጥ ይከተውና አኩርፎ ይቀመጣል። ይሄ ትክክል አይደለም። በነገራችን ላይ ሁልጊዜ መስቲካ ሲሰጣጡ ስናይ፥ አንዱ ለሌላው "አፍህ ወይም አፍሽ ይሸታል" ማለታቸው ነው ብለን ድምዳሜ ልናደርግ አይገባም።

መልካም ምላስ "አይበቀልም"። ጴጥሮስ *"መርቄ እንጂ ክፉውን በክፉ ፈንታ፤ ሰድብንም በሰድብ ፈንታ አትመልሱ፥ ምክንያቱም እናንተ የተጠራችሁት ይህን በማድረግ በረከትን ለመውረስ ነው"* በማለት ይመክረናል (1 ጴጥ. 3፥9)። ያዕቆብም ምላስን መግራት ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሆነ ሲገልጽ፥ *"ንገር ግን ምላስን ሊገራ የሚችል ግንም የለም፥ የሚገድል መርዝ የሞላባትና ዕረፍት የሌላት ክፉ ነገር ናት"* ይላል (ያዕ. 3፥8)። ይሁን እንጂ፥ ምላስን ሊገታ የሚችል አንድ ነገር አለ። ያም "ፍቅር" ነው። ፍቅር ሁልጊዜ



ያስፈልገናል። ከማንኛውም ጊዜ የበለጠ ግን ሰዎች በጠላትነት በሚነሱብን ጊዜ ያስፈልገናል። የሚወደንን መውደድ ከባድ አይደለም። ከባድ የሚሆነው የሚጠሉንን መውደድ ነው። ኢየሱስ ንግግሩ ሁል ጊዜ በፍቅር የተሞላ ስለነበር በጠላቶቹ ሁሉ ፊት ሲቆም ይታይ ነበር። ሐዋርያው ጴጥሮስ ይህንን እውነት ሲያረጋግጥልን፥ *"ኀጢያትም መልሶ አልተሳደበም፥ መከራን ሲቀበል ዳድቅ ፈራጅ በሆነው አምላክ ተስፋ አደረገ እንጂ አልዛተም"* አለ (1 ጴጥ. 2፥23)። ሊገድሉት የሚፈልጉትን በቁጣ ተሞልቶ አልተቃወመም። በመስቀል ላይ ባረፈበት ጊዜም እንኳን *"አባት ሆይ! የሚያደርጉትን ስለማያውቁ ይቅር በላቸው"* (የሉቃስ 23፥34) ብሎ እንደጸለየላቸው እናውቃለን።

## 5. <u>መልካም ምላስ በምሳጋና የተሞላ ነው</u>

ሰው የተፈጠረው እግዚአብሔርን ለማመስገን ስለሆነ፥ ደስ በሚለውና ደስ በማይለውም ጊዜ እግዚአብሔርን ሁልጊዜ ማመስገን እንዳለበት መጽሐፍ ቅዱስ ይመክራል። እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘው ስናማርርና ስናጉረመርም ሳይሆን ስናመሰግነው ነው። እስራኤላውያን ትልቁ ችግራቸው፥ ብዙ አደጋ ላይ የጣላቸው፥ ከእግዚአብሔር ጋር ያጋጫቸው የነበረው ዋናው ምክንያት፥ የተደረገላቸውን በጎ ነገር እየረሱ ሁልጊዜ የሚያጉረመርሙ በመሆናቸው ነው። እግዚአብሔር ሲመሰገን ደስ እንደሚለው ሁሉ፥ በእግዚአብሔር አምሳልም የተፈጠረው ሰው፥ ሲመሰገን መሰማት ይወዳል። ክፉ ክፉውን እየጠቀሱ "እንዲህ ነህ! እንዲያ ነህ" መባባሉ ያራርቃል እንጂ አያቀራርብም። ጌታን አብረው የሚያገለግሉ ሦስት ወንድሞች በተለያየ ጊዜ፥ በልዩ ልዩ ምክንያት እየተጋጩ እነርሱን ለማስታረቅ ከባድ የሆነበት ጊዜ ነበር። የማስታረቅ ዕድል ገጠመኝና "የተበዳደላችሁት ለመሆኑ ማን ምን አድርጎ ነው?" ብዬ በመጠየቅ ፈንታ፥ "እስቲ በዚህ እንጀምር! አንዳችሁ የሌላውን ድካም በደንብ ታውቃላችሁ። የማታውቁት ነገር ቢኖር እያንዳንዳችሁ ያላችሁን ብርታት፥ ወይም ጥሩ ነገር ነው። አንዱን እስቲ ከእንተ እንጀምርና ስለነዚህ ሁለት ወንድሞች ብርታታቸው ምን እንደሆነ ተናገር..." አልኩት። "ምንም ብርታት የላቸውም" አላለም። አንድ በአንድ መዘርዘር ጀመረ። እርሱ

ሲጨርስ ሌላውን "ቀጥል" አልኩት። በዚህ ዓይነት እያንዳንዳቸው የሌላውን ብርታት ተናግረው ሲጨርሱ፥ አንዳንዶቹ ማልቀስ ጀመሩ። "እኔ እኮ እከሌ ስለ እኔ ጥሩ ነገር ያስባል ብዬ አላምንም ነበር..." ማለት ጀመሩ። በወቀሳ ፈንታ "ምስጋና" በመስማታቸው ልባቸው ወዲያው ተፈውሶ ተቃቅፈው ተሳሳሙ። ስብሰባችንም በአጭር ጊዜ ውስጥ ፍሬያማ ሆኖ አለቀ።

ልጆች ከወላጆቻቸው ሁልጊዜ "መነቀፍ" ሳይሆን፥ "ጎበዝ የእኔ ልጅ! ጥሩ ሠርተሃል!" መባልን ይፈልጋሉ። የጥንት ወላጆች፥ "ልጅ ከተመሰገነ ይበላሻል" ብለው ስለሚያምኑ፥ ልጆቻቸውን አያመሰግኑም ነበር። አንዳንድ ወላጆች ልጃቸው አምስት "ኤ" አምጥቶ አንድ 'ቢ' ቢያመጣ፥ "ጎበዝ የእኔ ልጅ!" ብለው በማድነቅና በማመስገን ፈንታ፥ "ይቺ ለምን 'ቢ' ሆነች?" ብለው የሚቆጡ አሉ። ከወላጆቻቸው ከነ ቀፋ በስተቀር ምንም ዓይነት ምስጋና ሳይሰሙ አድገው የሚወጡ ልጆች አሉ። "አንድም ቀን አባቴ 'እወድሃለሁ' ብሎ አላቀፈኝም። ምንም ያህል የትምህርት ውጤቴ ጥሩም ቢሆን፥ አንድም ጊዜ 'ጎበዝ የእኔ ልጅ!' ብሎኝ አያውቅም" የሚሉ፥ በወላጆቻቸው ከፍተኛ ቅሬታ ያላቸው ልጆች ብዙ ናቸው። ምስጋና ሲገባው፥ በወቅቱ ምስጋና ማጣት በጣም ይጎዳል። አንድ ጊዜ አንዲት እናት ስድስት ወንዶች ልጆች ወልዳ በብዙ ትግል አሳድጋ ራሳቸውን እንዲችሉ አደረገች። ስድስቱም የራሳቸውን ኑሮ መኖርን እንጂ አንዳቸውም ተመልሰው አላመሰገኗትም። ዘመኗን ጨርሳ ለመሞት ጥቂት ሲቀራት ስድሱቱም ልጆቿ ሊጠይቋት መጡ። የመጀመሪያው ልጇ ስልጣን ያለው ትልቅ ሰው ሆኗል። ተንበርክኮ ግንባሯ ላይ ያለውን ላብ እየጠረገላት፥ እንዲህ አላት። *"እኔ ናት፥ ለልጆችሽ፥ ለሰድሱቶቻችንም በጣም ጥሩ እናት ነበርሽ"* አላት። በሕመም ተዳክማ የነበረችው ያቺ እናት፥ ዓይኖቿን ከድን አድርጋ ሰንባዋን ካፈሰሰች በኋላ ዓይኗን ከፍታ የመጀመሪያውን ልጇን ዓይን እያየች እንዲህ አለችው። *"የእኔ ልጅ ስማንኛውም ነገር የበለጠ በሕይወቴ የጸለይኩት ለሰድሱቱ ልጆቼ ጥሩ እናት ሉድርገኝ' ብዬ ነው። ምናልባት እንደምፈልገውና እንደ ሚገባው ያህል ጥሩ እናት አልሆንኩም ይሆናል። ጥሩ እናት መሆን ስለመሆኔን እስክ ዛሬ ድረስ ከእናንተ ከልጆቼ ከአንዳችሁም አልሰ ማሁም። ለመጀመሪያ ጊዜ ጥሩ እናት መሆኔን የሰማሁት ዛሬ ነው"* አለቻቸው።



በጎ ነገር አድርገን መመስገንን ሁላችንም እንፈልጋለን። ሰውን የበለጠ እንዲሠራ የሚያደርገው እንደኛው ነገር መመስገን ነው። ከሌሎች ምስጋና መፈለግ የሰው ተፈጥሮ ነው። ፍቅራችንን፣ ድካሚ ችንን፣ መጨነቃችንና ፅንባችን በሌላው ሰው ሕይወት ውስጥ ስላመ ጣው በጎ ነገር መሰማት እንፈልጋለን። እኛ መመስገን የምንፈልገውን ያህል ሌሎችም መመስገን እንደሚፈልጉ መዘንጋት የለብንም። ይህ ንን ባለመረዳታችን ምክንያት በሕይወታችን ከፍተኛ ሚና ተጫው ተው "ምስጋና" የጎደግናቸው ለመሆኑ ስንቶች ይሆኑ? በማመስገን ፈንታ "ነቅፈናቸው ልባቸው የተሰበረ" ስንቶች ይሆኑ? መልካም ምሳሌ በምስጋና የተሞላ ነው።

# ምዕራፍ ፫

# ክፉ ምላስ

*"ክፉ ሰዎች ሌሎችን የሚጎዱበትን መንገድ ያስባሉ፥*
*ንግግራቸውም እንደ እሳት የሚያቃጥል ነው፥*
*ክፉ ሰዎች ሐሜት ያሠራጫሉ፥ ሁከትን በማነሳሳት*
*በፍቅር የተሳሰሩትን ወዳጆች ይለያያሉ።"*
*(ምሳሌ 16፥27-28)*

ምላስ ለመገንባትም ሆነ ለማፍረስ ልዩ የሆነ ኃይል አለው። መልካም ቃል የሰውን ሕይወት የማነጽ፣ የመፈወስና የማዳን ኃይል አለው። ዘማሪው ዳዊት የዚህን ምስጢር ስለተረዳ ነው *"የተሰፋ ቃልህ ሕይወቴን ስላደሰልኝ በመከራዬ ጊዜ እንኳ ተጽናንቻለሁ"* (መዝ. 119፥50) ያለው። ምላስ የመፈወስ፣ የመገንባት ኃይል እንዳለው ሁሉ፥ የማጥፋትም ሆነ የመግደልም ኃይል አለው።

## 1. ምላስ ልዩ ኃይል አለው

ምላስ ትንሽ የአካል ክፍል ትሁን እንጂ፥ በውስጧ ታላቅ ኃይል አለ። ከጥንት ጀምሮ ሰዎች መልካም ቃላትን በታሪክ፣ በግጥም፣ በጣፈጠ ድርሰት፣ በመዝሙር መልክ ለመስማት ይፈልጉ የነበረበት



ትልቁ ምክንያት፥ በቃላት ውስጥ ያለውን ኃይል ስለተረዱ ነው። *ማሪ አቪኖቭ* ከመሳፍንት ወገን የነበረች ራሻዊት ነበረች። *ሰታሊን* በሩሲያ ውስጥ ባካሄደው አብዮት፥ እንዲሁም በሁለተኛው ዓለም ጦርነት ውስጥ ያለፈችና ከሞት የዳነች ሴት ነበረች። ይህቺው ሴት *በስታንሊን* ወህኒ ቤት ያየችውንና የተለማመደችውን ታሪክ *"የመናኝ ጉዞ በሲኦል" (Pilgrimage Through Hell)* በተባለው መጽሐፏ ጽፋዋለች። ለ30 ሰዎች ብቻ እንዲሆን በተሠራ፥ ነገር ግን መቶ ሴቶች እንደ ሰርዲን ታጭቀው ወደታሠሩበት ወህኒ ቤት ውስጥ ተጥላ ነበር። በዚያ ወህኒ ቤት ውስጥ ተራ ሴተኛ አዳሪ የነበሩና በአለፈው አገዛዝ ሥር የመሳፍንት ወገን የነበሩ ሴት ወይዘሮች በአንድ ላይ ታሰረው ነበር። የወህኒ ቤቱ አስከፊነት በሰው አዕምሮ የሚታሰብና የሚገመት አልነበረም። እስረኞቹ በቂ ምግብ ስለማያገኙ ለአንዲት ትንሽ ስኳርና ደረቅ ዳቦ ሲሉ እርስ በርሳቸው መደባደብ፥ አንዱ ሌላዋን በጠርሙስ መፈንከት የተለመደ ተግባራቸው ነበር። ስፍራው ከመጥበቡ የተነሳ፥ ለመተኛት ቀርቶ ለመቆምም እንኳን በቂ ቦታ አልነበርም።

እነዚህ እንደ አውሬ እርስ በርሳቸው የሚባሉትን ሴቶች ሥርዓት አስይዞ ጸጥ ለማድረግ የቻለ አንድ ኃይል ብቻ እንደነበረ *ማሪ አቪኖቭ* በመጽሐፏ ገልጸዋለች። ይኸውም፥ በጽሁፍ የቀረበ የሰዎች ንግግርና ታሪክ ነበር። በታወቁ ታላላቅ ጸሐፊዎች የተጻፈ ልዩ ልዩ መጽሐፍት ተራ በተራ ሲነበብላቸው እነዚያ ሥርዓተ አልባ ሴቶች በጸጥታና በተመስጦ ያዳምጡ ነበር። የወህኒው ቤት ኃላፊ ሴቶቹ እየተንጫጩ ሲያስቸግሩት "ዝም ካላላችሁ ማንበቤን አቆማለሁ" እያለ ሲያስፈራራቸው፥ መልሰው ጸጥ ይሉ ነበር። ቃላት ብዙዎችን የመግዛት ኃይል ያለው መሣሪያ ነው። በዚያም የሰውን ስሜት፥ አዕምሮውንና መንፈሳዊ ሕይወቱን መቀስቀስና መንካት ይቻላል። በንግግር ችሎታቸው በጣም ከሚደነቁ ሰዎች መካከል የአሜሪካ ፕሬዚደንት የነበሩት *ፕሬዚደንት ሮናልድ ሬገን* ናቸው። በንግግራቸው አድማጮቻቸውን የመሳብ፥ የማሳመን ችሎታ ነበራቸው። ስምንት ዓመት የአሜሪካ ፕሬዚደንት በነበሩበት ዘመን ብዙ ተቃዋሚ ቢኖራቸውም ማሳመን በሚችለው ንግግራቸው ሳይሸነፉ ለአሜሪካ ሕዝብ ይጠቅማል ብለው ያመኑበትን ሁሉ መሥራት ችለዋል። ፕሬዚደንት መን

ግሥቱ ኃይለግርያምም በአካባቢያቸው የነበሩ ሰዎች ጥሩ ተናጋሪ፥ የማሳመን ችሎታ የነበራቸው ሰው እንደነበሩ ይናገሩላቸዋል። ኃይሉ በንግግር ችሎታቸው ይሁን ወይም በጦር መሣሪያ በማስፈራራት እንደሆነ ተዕይቶ አይታወቅም። ሥልጣን ይሻማሉ ተብለው የተጠረጠሩ ሁሉ ተገድለዋል። ይሄም በብዙዎች ላይ ፍርሃትን ፈጥሮ ነበር። የሚሰጡት ትዕዛዝ፥ የሚያደርጉት ንግግር ከፍርሃት የተነሳ ተቀባይ ነት አግኝቶ እንደሆነ አይታወቅም።

የአሜሪካ ሕገ መንግሥት ለሕዝቡ የመናገር ነጻነትን ይሰጣል። አሜሪካንን ልዩ ከሚያደርጉት ምክንያቶች መካከል አንደኛው ሕዝቡ ሀሳቡን የመግለጽ ነጻነት ያለው በመሆኑ ነው። ዲሞክራሲ ባለበት ሕብረተሰብ ውስጥ የመናገር ነጻነት ከፍተኛውን ሥፍራ ይዟል። "መናገር" የለውጥ ትልቅ ምክንያት ነው። በአገሪቱ ውስጥ የሚኖረ ውን መጥፎ አስተዳደርን፥ የተበላሸ አመራርን ያጋልጣል። ጥሩ ጥሩ የአመራር መርሆ (ፖሊሲ) እንዲፈጠር ያደርጋል። የአገር መሪው ጥሩ እስከ ሠራ ድረስ ለሕዝቡ የመናገር ነጻነት መሰጠቱ ሊያስፈራ ውና ሊያሳስበው አይገባም። እግዚአብሔር ለመጀመሪያዎቹ ሰዎች ለአዳምና ለሔዋን የመናገር ስጦታ ሰጥቶአቸው ነበር። ይህን ታላቅ ስጦታ በአግባቡ ባለመጠቀማቸው ምክንያት ምን ያህል ጥፋት በሰው ልጅ ላይ እንደደረሰ እናውቃለን። እባቢቱ በንግግር ችሎታዋ *"በፍጹም ሞትሞቱም! እግዚአብሔር ይህን ያዘዛችሁ እንደ እግዚአብሔር እንደምትሆኑና ደጉን ክፉ ለይታችሁ እንደምታውቁ አስቀድሞ ስለሚያውቅ ነው"* (ዘፍ. 3፥4-5) በማለት ሔዋንን አሳመነቻት።

ምላስ ምን ያህል ኃይል እንዳለው ለማሳየት በዘመናት ልዩ ልዩ ታሪኮች ተጽፈዋል። አንድ ጊዜ አንድ ሰው በህልሙ ከሰውነት ክፍ ሎቹ መካከል፥ ይኸውም እግር፣ እጅ፣ ዓይንና ልብ "ከሁላችሁ እበ ልጣለሁ" ካለው "ከምላስ" ጋር መጣላትና ቅሬታቸውን መግለጥ ጀመሩ። ምላስም በሁኔታው ተቀይሞ የምላስን የበላይነት አምነው እንዲቀበሉ የበቀል እርምጃ ለመውሰድ አመቺ ጊዜ ይጠብቅ ነበር። የዚያኑ ቀን ከሰዓት በኋላ የአገሪቱ ንጉሠ ነገሥት በአጃቢያቸው ታጅበው ሲሄዱ አይቶ "ምላስ" ጮክ ብሎ ክፉ ቃል በንጉሡ ላይ ተናገረ። የተናገረው ነገር ከንጉሡ ጆሮ ደርሶ ስለነበረ ተጎትቶ ከን ጉሡ ፊት ቀረበ። በተናገረው ነገር ተጸጽቶ "ምላስ" ይቅርታ ካልጠ



የቀ በዚያኑ ቀን በስቅላት እንደሚቀጣ የታወቀ ነበር። "ምላስ" ግን እግር፥ እጅ፥ ዓይንና ልብ የእርሱን የበላይነት እስኪያምኑና እርሱን ይቅርታ እስኪጠይቁ ድረስ ንጉሡን ይቅርታ እንደማይጠይቅ ገለጸላ ቸው። ነገሩ ተረት ይሁን እንጂ፥ ምላስ የሚያስከትለውን የሞት አደጋ፥ እንዲሁም ከሞት እንዴት ሊያድን እንደሚችል የሚገልጽ ነው። ምላሳችን ብዙ ጊዜ እየደጋገመ አደጋ ላይ ሲጥለን አይተናል። ገና በልጅነታችን ምላሳችን ከወንድሞቻችንና ከእህቶቻችን፥ እንዲሁም አብረን ከምንጫወታቸው የመንደር ልጆች ጋር ያጋጨን፥ ያደባድበን እንደነበረ እናስታውሳለን። በዕድሜ ከጎለመስንም በኋላ ምላሳችን ችግር ላይ እንዳይጥለን ብዙ ታግለናል፥ አሁንም ብዙ እየታገልን ነው። ክርስቲያኖች በምላሳችን ምክንያት መንፈሳዊ ሕይወታችን እንዳያቀጭጭብን ጥረት ማድረግ እንዳለብን እናውቃለን።

ሰው በልቡ ያለውን፥ የሚሰማውን እውነት ጨምቆ ቢናገርም ሰዎች ሊረዱት የማይችሉበት ዋናው ምክንያት ሀሳቡን በፍቅር ቀምሞ ስለማያቀርበው ይሆናል። በዓለም ላይ ለሰዎች ልጆች የተሰጠ አንድ ትልቅ ኃይል አለ። ያም ኃይል ተከራክሮ የራስን መብት ማስከበር አይደለም። ወይም ሰዎችን በንግግር ኃይል አንሰው እንዲታዩ የማ ድረግ ችሎታ አይደለም። ወይም ዓለምን በኒኩሊየር ቦምብ የሚያ ጠፋ፥ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ጥበብ ውስጥ የሚገኝ ኃይል አይደ ለም። ነገር ግን ትልቁ ኃይል ያለው በፍቅር ውስጥ ነው። ይህን ዓለም ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣው፥ እግዚአብሔር አብ ልጁን ወደዚህ ወደ ጠፋው ዓለም ልኮ ለጠፋነው ደህንነትን እንድናገኝ ያደ ረገው በፍቅር ነው። ፍቅር የኃጢአትን፣ የሞትንና የሰይጣንን ኃይል ሰብሮ የጣለ ነው።

## 2. <u>በአግባቡ ያልዋለ ክፉ ምላስ</u>

ዕውቀት የብዙ ነገር መረጃ ቁልፍና መስኮት ነው። ብዙዎች ካላቸው እውቀት የተነሳ "አያውቁም" ብለው በሚያስቧቸው ሰዎች ላይ ኃይል ማግኘት ችለዋል። የሥጎ አዕምሮ ዕውቀት ያላቸው ምሁ ራን የሰዎችን ተፈጥሯዊ ባሕሪ በማወቃቸው ሰዎችን በፈለጉት አቅጣጫና እነርሱን በሚመቻቸው መንገድ ለመጎተትና ለመምራት

ችለዋል። ሲ. ኤስ. ሉወስ (1898-1963) ሰዎች በዘመኑ ያለውን ከፍ ተኛ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ጥበብ በመጨበጣቸው ከፍተኛ ኃይል ይዘዋል። ይሁን እንጂ፥ ዕውቀታቸው በእግዚአብሔርና በሰው ፍቅር ላይ የተመሠረተ ባለመሆኑ ዓለም ወደ ከፍተኛ ጥፋት በመገስገስ ላይ ትገኛለች ብለው ጽፈዋል። ብዙዎች የሰዎችን ተፈጥሯዊ ባህሪ ለማወቅ ጥረት የሚያደርጉትን ዋናው ምክንያት ሰዎችን እነርሱ በሚፈልጉት መንገድ ለመምራትና ለመጠምዘዝ ችሎታ እንዲኖራ ቸው ነው። ስለዚህ ፍቅር የሌለበት ዕውቀት ሌሎችን መጠምዘዣና የራስን ፍላጎት ብቻ ማሟያ መሣሪያ ነው። ሰው በዕውቀቱ የሚፈል ገውን ከሌላው ሰው ጨምቆ ማግኘት በመቻሉ ፍቅርን ችላ ብሏል።

የዘመኑ የሥነ አዕምሮ ዕውቀት ከአካባቢዋ ወይም ከትምህርት ቤት የቀሰመች ሴት የባሏን አዕምሮና አሳብ በራሷ መንገድ ለመም ራት የተለያየ ዘዴ ትጠቀማለች። *"አንተ እኔ የምጠይቅህን ነገር እሺ ማለት ከተውክ ብዙ ጊዜ ነው፥ እስቲ ዛሬ ገበያ አዳራሽ አብረን እንሂድ"* ትለዋለች። *"ተቃራኒ ዘዴ" (Negative Approach)* በመጠ ቀም የምትፈልገውን ለማግኘት በመሞከሯ ባልዋ አመጣጧ (ዘዴዋ) ከገባው መልሱ 'አልችልም" የሚል ይሆናል። ከዚህ ይልቅ ግን *'እሰ ልዩ! እስቲ እባክህን ዛሬ አብረን ገበያ አዳራሽ እንሂድ"* ብትለው፥ ንግግሯ በፍቅር የተቀመመ በመሆኑ ቢደክመውና ገበያ መሄድ ባይ ወድም ስለ እርሷ ፍቅር ሲል ያደርገዋል። አዕምሯችን ምድራዊ በሆነ ዕውቀት ሲሞላ፥ የፍቅር ሕይወታችን ይሻሻትና በእነጋገር ዘዴና ጥበብ እኛን በሚመቸን መንገድና ሁኔታ የሰዎችን አዕምሮ ለመጠምዘዝ ሙከራ እናደርጋለን። መጽሐፍ ቅዱስ *"የደግ ሰው ንግግር የሕይወት ምንጭ ነው"* ይላል (ምሳሌ 10፥11)። ንግግራችን በፍቅር የተቀመመ ከሆነ ለሚሰማው የሕይወት ምንጭ ነው። በዘ መኑ ዕውቀት የተሸፈነ ከሆነ ደግሞ የራሳችንን ፈቃድ ማሟያ፥ የሰ ዎችን አዕምሮ መጠምዘዣ መሣሪያ ይሆናል።

ብዙ ጊዜ አንዳንድ አማኞች የእግዚአብሔርን ቃል ያለቦታው በመሸረፍ፥ ወይም ልዩ ትርጉም በመስጠት ለራሳቸው እንዲመቻቸው አድርገው ሲጠቀሙበት ይታያሉ። *"ሚስቶች ሆይ! ለባሎቻችሁ ተገዙ"* የሚለውን የእግዚአብሔር ቃል ፍቅር ሳይቀላቅሉበት ሚስቶቻቸውን በኃይል ለመግዛት የሚሞክሩ አሉ። *"የእግዚአብሔር ቃል ተገዢ ይላል። ...እኔ የቤት እራስ ነኝ"* በማለት ፍላጎታቸውን ሚስቶቻቸ ውን ዋጋ ቢያስከፍልም፥ በዚያ ፍላጎታቸውን ለማሟላት የሚሞክሩ ባሎች ጥቂቶች አይደሉም። *"መንፈሳዊ መሪዎቻችሁን አክብሩ"* የሚ ለውን ቃል አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ደግሞ ያለአግባብ ሲጠቀሙበትና ምዕመናኖቻቸውን መብት አሳጥተው ሲያስጨንቋቸው ይታያሉ። በፍቅር በመግዛት ፈንታ በእነርሱ ሀሳብ የማይመሩትን ከቡድናቸው እንደሚያስወጧቸው በማስፈራራት ሲያስበረግጓቸው ይታያሉ። የፍቅር ልብ ከሌለው ሰው አፍ የሚወጣው ቃል ሌሎችን የሚገሰፅ፥ የሚያንጽ፥ ሳይሆን የሚያፈርስ ነው።

## 3. ክፉ ምላስ ብዙ ጉዳት ታደርሳለች

ሳናስብና ሳንጠነቀቅ የምንወረውራቸው ተራ ቃሎች ሌሎችን ሲጎዱ እናያለን። ሙሉጌታ ጸጉሩን እያበጠረ ሳለ፥ ሚስቱ አጸደ ፎጣ ፍለጋ የመጸዳጃ ቤቱን በር ከፍታ ገባች። *"አጸድዬ፥ ተመልከቺ! የጸጉር አበጣጠር ስታይሌን ቀየርኩት! ይሄኛው አይሻልም? ምን ይመስልሻል?"* ብሎ ጠየቃት። አጸደም የምትናገረውን በደንብ ሳታ ስብ፥ ከአጁ እንደመጣላት ከጓደኛቸው መካከል የአንዱን ሰው ስም ጠርታ *"እሱን ለመምሰል ነው እንዴ? ይልቁንስ እንደ ሴት የጸጉር አበጣጠር ስታይል መቀያየርህን ትተህ፥ ሌላ ወንዶች የሚሠሩትን ሥራ ብትሠራ ምን አለበት?"* ብላ በንግግሯ ጠቅ አድርጋው ወጣች። ሙሉጌታ የሚስቱ አነጋገር አስደንቆት ፈዝዞ ቀረ። ክፉም ሆነ ደግ አልተናገረም። አጸደ ለማጠብ ያዘጋጀቻቸውን ጨርቆች ማጠቢያ ማሽን ውስጥ እየከተተች፥ ለሙሉጌታ የሰጠችው መልስ የማይጠ ግን፣ ክርስቲያናዊ ያልሆነ፣ ጠብ የሚጭር፣ ሙሉጌታን የሚያሳንስ ክፉ ቃል የተናገረች መሆኗን ለመረዳት ጊዜ አልፈጀባትም። *"አንዴ ተናግሬዋለሁ፥ ከዚህ በኋላ የተናገርኩትን መመለስ አልችልም"* ብላ ነገሩን አለባብሳ ማለፍ አልቻለችም። ሀሊናዋን ቆረቆራት። መንፈስ ቅዱስ ይቅርታ መጠየቅ እንዳለባት እየነገረ አስጨነቃት። በዚህ ጊዜ በሙሉጌታ ልብ ውስጥ ምን ዓይነት ሁኔታ እንደተፈጠረና በዚህም ምክንያት ሰላማቸው ሊጠፋ እንደሚችል ለመገንዘብ አልተቸገረችም።

ሮጣ ሄዳ *"ሙሉጌታ! ስለ መጥፎ አነጋገሬ ይቅርታ አድርግ ልኝ። በመጥፎ ምላሴ ጎድቼሃለሁ! ወደ አንተ ዘንድ ሰመጣ በጣም*

ተናድጀ ነበር። የልጆቹን ልብስ ማጠቢያ ውስጥ ስከት፥ ምን ያህል ልብሳቸውን እንዳቆሸሹት አይቼ ተበሳጭቼ ነበር። በነርሱ ላይ የነበረኝን ብስጭት በአንተ ላይ ተወጣሁት። ይህ ትክክል እንዳልሆነ ገብቶኛል። በጣም ጎድቼሃለሁ። ከአፌ የወጣው ሁሉ በልቤ ውስጥ የማምንበት አይደለም። እባክህን በሙሉ ልብህ ይቅር በለኝ" አለችው። ሙሉጌታም በተናገረችው ቃል ልቡ ያዘነ፥ ውስጡ በቁጣ የተሞላ ቢሆንም፥ የአጸደ ከልብ መጸጸትና ይቅርታ መጠየቅ ወዲያው ሁኔታውን እንዲለውጥ አደረገውና፥ "ንግግሽ ምንም አይደለም፥ አልጎዳኝም አልልሽም። በጣም ጎድቶኛል። ሁለተኛ እንዲህ ዓይነት ክፉ ቃል ከአፍሽ አይውጣ። የእግዚአብሔር ቃል በሚያዘው መሠረት ይቅርታ ኢድርጊልሻለሁ" አላት። ሳናስብ የምንወረውራቸው ቃሎች ብዙ ጊዜ ሌሎችን ይጎዳሉና ከመናገራችን በፊት እንደ አስተዋይ ክርስቲያን ማሰቡ ይጠቅማል። ደሊል የተባለ ጸሀፊ፥ "አስተዋይ አስቦ ይናገራል፥ ሞኝ ግን ከተናገረ በኋላ ንግግሩን ይመረምራል" አለ። ለምንናገረው ንግግር ጥንቃቄ መውሰድ ያለብን ከመናገራችን በፊት እንጂ ከተናገርን በኋላ አይደለም። ጥንቃቄ የጎደለው ንግግራችን ሁልጊዜ ዋጋ እንደሚያስከፍለን አንዘንጋ። መጽሐፍ ቅዱስ "ያለጥን ቃቄ በሚናገር ሰው ላይ ጥፋት ይደርስበታል" ይላል (ምሳሌ 13፥3)።

ብዙ ጊዜ ተራ ቃላት፥ ጸጋ የማይሰጡ አስተያየቶች ከአፋችን የሚወጡት ሳናስብ ስለምንናገራቸው ነው። እነዚህ ጸጋ የማይሰጡ ንግግሮቻችን እኛ ከምንገምተው በላይ ሌሎችን የሚጎዱ መሆናቸውን አንርሳ። አንድ ጊዜ አንድ የቤተ ክርስቲያን መጋቢ አንዱን አገልጋይ "አስቴር፥ አንድ ጊዜ እፈልግሻለሁ" ብሎ ወደ ቢሮው ወሰዳትና "ይህን ጤናማ ያልሆነ ወሬ በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ የሚያወራውን ምላስሽን ዝጊ። መንፈሳዊ ሕይወትሽን እስከታስተካክዪ ድረስ ደግሞ ከድቁና አገልግሎትሽ ታግደሻል" አላት። "ምን ብዬ ወሬ አሰራጫሽ?" ብላ ለመጠየቅም ጊዜም ሆነ ዕድል አልሰጣትም። የተናገራት ቃል መጀመሪያውም መጨረሻውም ይሄ ነው። ምክንያቱ ፈጽሞ አልገባት ስላለ የበለጠ ግራ ተጋባች። ሁኔታው ጨለመባት። ዓለም በላይዋ ላይ የተደፋባት መስሎ ተሰማት። ሮጣ ወደ ቤቷ ሄዳ፥ ወለሉ ላይ ተዘርራ ስቅስቅ ብላ አለቀሰች።

ሀዘኑ ትንሽ ጋብ ሲልላት እራሷን መመርመር ጀመረች። "ምን



አደረግሁ? ምን አጠፋሁ? ለማን፣ ምን ብዬ አወራሁ? የቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ለንስቼ ከማን ጋር ተነጋገርኩ?" ብላ ራሷን አጥብቃ መረመረች። ይሁን እንጂ፥ ምንም ነገር ማስታወስ አልቻለችም። በመካከሉ አንድ ነገር ትዝ አላት። ከመጋቢው ሚስት ጋር ብዙ ጊዜ በሀሳብ አትጣጣም ነበር። የፓስተሩ ሚስት "አለቃ ልሁን፣ ሁልጊዜ እኔ ያልኩት መሆን አለበት" የምትል፣ ፈላጭ፣ ቆራጭ መሆኗን በግልጽ የምታሳይ በመሆኗ፥ ከአስቴር ጋር አይጣጣሙም ነበር። አስቴር በተፈጥሮዋ እንደ ሌሎች "እስልየ! እንትንዬ! ፓስተርዬ!..." እያለች እጅ መንሳት አትወድም። "ከሌሎች እህቶች የበለጠ ለመጋቢው ሚስት እጅ መንሳት አለብኝ" ብላ አታምንም። ይሄን ጠባይዋን የመጋቢውም ሚስት በደንብ ታውቃለች። በዚህ ሁኔታዋ ለካስ ቂም ይዛባት ኖሮ፥ በባሏ በኩል አስቴርን የምትጎዳበትን መንገድ ታውጠነጥን ነበር። ጊዜ ጠብቃ አስቴርን የምትጎዳበትን ነገር ማድረግ ቻለች። አስቴር መጋቢው ያን በመሰለ ከባድ ቃል ለምን እንደተናገራት ገባት። ይሁን እንጂ፥ ሁኔታው አስቴርን በጣም ጎዳት። የጎዳት ከአገልግሎት መታገዱ አይደለም። ነገር ግን የመጋቢው አነጋገር ነው። ..ንዴ!..." አለች አስቴር ነገሩ አስደንቋት። "በቤተ ክርስቲያኔ ውስጥ መብት የለኝም እንዴ? ሊፓስተሩ ሚስት እጅ ካልነሳሁ እንትንዬ!.. ካላልኩ፥ ከመሰመር የወጣ ነገር ሰታደርግ እያወቅሁ 'እንዳልሽ' ካላልኩ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሥፍራ ላይኖረኝ ነው? ቤተ ክርስቲያኒቱ የክርስቶስ እንጂ፥ የፓስተሩና የሚስቱ የግል ሀብት ነች እንዴ?" ብላ ራሷን ጠየቀች።

አስቴር ልቧ አዘነ። ከዚህ በኋላ ቤተ ክርስቲያን መሄዱን አቆመች። ብትቀርም፥ "ምን ሆንሽ? ለምን ቀረሽ?" ብሎ የሚፈልጋት ሰው አልነበረም። "በሕይወቷ ቀዝቅዛ ከቤተ ክርስቲያን ቀረች" እንደሚሏት ታውቃለች። "የፈለጉትን ይበሉ እንጂ፥ ሁለተኛ አልሄድም" ብላ ወሰነች። የሚያሳዝነው፥ አስቴር በሁኔታው በጣም ስላዘነች ብዙ ሌሊቶች ያለዕንቅልፍ ማደር ጀመረች። ሳታውቀው የመንፈስ ጭንቀት ውስጥ ገባች። ከእንቅልፍ ማጣት የተነሳ፥ ሥራዋን መሥራት ስላልቻለች ከሥራዋ ወጣች። ሀኪም ቤት ሄዳ የአዕምሮ ጭንቀት ማስታገሻ ተሰጥቷት መውሰድ ጀመረች። ለሁለት ዓመት ያህል ከሆስፒታል፥ ሆስፒታል ተንከራተተች። በዚህ ጊዜ ውስጥ ከቤተ ክርስ

ቲያን ውስጥ "ምን ሆንሽ?" ብሎ ሊጠይቃትና ሊፈልጋት የሞከረ ሰው አልነበረም። ያ የበለጠ ጎዳት። በክርስቲያኖች ላይ የነበራት እምነት ሁሉ ተሟጠ በማለቁ፥ ክርስቲያኖችን ስታይ ትሸሽ ጀመር። ታሪኩ የፈጠራ ታሪክ ይሁን እንጂ፥ በዚህ ዓይነት መልክ የሚጎዱ ክርስቲያኖች እንደሚኖሩ ግን እርግጠኛ ነን። "ስለ ምላስ" ወደፊት በመጽሐፍ መልክ ይወጣል ብዬ ይሄን ከላይ የሰማችሁትን የፈጠራ ታሪክ ጽፌ ካስቀመጥኩት ሰባት ወይም ስምንት ዓመት ይሆነዋል። ያስደነቀኝ፥ በቅርቡ ይህንኑ የሚመስል ነገር የደረሰባት አንዲት እህት ታሪኳን ያጫወተችኝ መሆኑ ነው።

ከአፋችን የሚወጡትን ቃላት መምረጥ ካልቻልን፥ ይህን የመሰለ ጉዳት በብዙዎች ሕይወት ላይ ልናደርስ እንችላለን። እርግጥ ነው በእኛ ምላስ ምክንያት የተጎዱት ሰዎች ዕርዳታ ወይም ምክር ፍለጋ ወደ እኛ ስለማይመጡ፥ በስንቶቹ ላይ ምን ያህል ጉዳት እንዳደረስን ልናውቅ አንችልም። መጽሐፍ ቅዱስ *"ያለጥንቃቄ የተነገረ ቃል፥ እንደ ሰይፍ ያቆስላል፥ በጥበብ የተነገረ ቃል ግን ይፈውሳል"* ይላል (ምሳሌ 12፥18)። እንደ ሰይፍ በሚዋጋው አነጋገራችን የምን ኮራ አንጠፋም። ዋሽንግተን ኤርቪንግ *"ስለት ካላቸው ነገሮች መካከል፥ በሠራ ቁጥር ስለቱ እየጨመረ የሚሄደው ሹል ምላስ ብቻ ነው"* አለ። ንግግራችን ጎጂ መሆኑን ነግሮ የሚያስቆመን ከሌለ፥ በዚህ ባህሪያችን የምንጎዳቸው ብዙ እንደሚሆኑ ግልጽ ነው። "ያለ ጥንቃቄ የተነገረ ቃል" ማለት፥ ግዴለሽ የሆነ፥ በሌላው ሰው ላይ የሚያስከትለውን ጉዳት ሳያስቡ መናገር ማለት ነው። ግዴለሽ አስተያየቶችን፥ ጎጂ የሆኑ ቃላትን በሌሎች ላይ እንዳንወረውር ራሳችንን የምንገታበት ኃይል እግዚአብሔር እንዲሰጠን በየጊዜው መጸለይ አለብን።

መጠኑ ይለያይ እንጂ ሁላችንም የምላስ ችግር አለብን። ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ በዓለም ዙሪያ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች በምላስ ምክንያት እንደተጎዱ ወይም እንዳለቁ ታሪክ ይመሰክራል። ምላስ ብዙ ሰዎችን ገድሏል፥ ብዙዎችን እርስ በርስ አጋጭቷል። ብዙዎችን ያለወዳጅ አስቀርቷል። በአጥፊነቱ የሚስተካከለው የለም። ጎልቶ የሚታየው በዓለማውያን መካከል ይሁን እንጂ ክርስቲያኖችም ምላስ ከሚያመጣው መዘዝ ፍጹም ነጻ አይደሉም። ዛሬ ቤተ ክርስቲያን የምትታመሰው፥ መከፋፈል፣ መለያየትና የቡድን መንፈስ



ጎልቶ የሚታየው፥ ጤናማ ምላስ በሌላቸው ክርስቲያኖች ምክንያት እንደሆነ የታወቀ ነው። ጳውሎስ የምላስ ችግር ስላለባቸው ሰዎች ለጢሞቴዎስ ሲጽፍለት፥ *"...ቤት ለቤት እየዞሩ ሥራን መፍታት ደግሞ ይማራሉ፥ የማይገባውንም እየተናገሩ ለፍላፊዎችና በነገር ገቢዎች ይሆናሉ"* ይለዋል (1 ጢሞ. 5፥13)። ጳውሎስ ይህን ቃል የተናገረው ስለ ዓለማውያን ሳይሆን፥ በክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስላሉት፥ ራሳቸውን "ክርስቲያኖች" ብለው ስለሚጠሩት ነው። በ1ኛው ክፍለ ዘመን የነበሩ ክርስቲያኖች የማይገባውን ነገር ይናገሩ የነበሩት ስልክ ስላልነበራቸው፥ በየቤቱ እየዞሩ ነበር። ለእኛኖቹ ክርስቲያኖች ግን በየሰው ቤት እንዳንዞር ቴሌፎን ሥራችንን ያቀለለልን ይመስላል። በእሁኑ ጊዜ በሰዎች መካከል የሚፈጠረው ግጭት፥ ዘጠና ከመቶ (90%) ምክንያቱ "ምላስ" እንደሆነ አዋቂዎች ይናገራሉ።

## 3. <u>ክፉ ምላስ ታቆሰላለች</u>

ምላስ ትንሽም ቢሆን ኃይል አለው፤ ራሱ አጥንት ባይኖረውም፥ አጥንት ይሰብራል። ሐዋርያው ያዕቆብ እንደበት ያለውን ኃይል ሲገልጽ፥ *"ምላስም እንደ እሳት ናት፥ ምላስ በአካል ከፍሎቻችን መካከል የምትገኝ ክፉ ዓለም ናት፥ ሥጋችንንም ሁሉ ታረክሳለች፥ እንደ ገሃነመ እሳት ሰውነታችንን ሁሉ ታቃጥላለች"* ይላል (ያዕቆብ 3፥6)። ከሰዎች አንደበት የሚወጣው ቃል በሌላው ሰው ሕይወት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስ እንደሚችል ብዙዎችም ጽፈዋል።

> <u>ጆን ዊከሊፍ</u>፥ *"ምላስ አጥንት ባይኖረውም አጥንት ይሰብራል"* ይላል።
>
> <u>ቻይናዎችም</u> *"ከአፍ ያመለጠ አንድ መጥፎ ቃል በሰይጣት ፈረሶች የሚሳብ ሠረገላ አይመልሰውም"* የሚል አነጋገር አላቸው።
>
> <u>ጃፓኖችም</u> እንዲህ የሚል አነጋገር አላቸው፥ *"የምላስ ርዝመቱ 3 ኢንች ብቻ ነው፥ ይሁን እንጂ፥ 6 ጫማ (feet) ርዝመት ያለውን ትልቅ ሰው ገርስሰው ይጥላሉ"* ይላሉ።

ምላስ የሰውን ሕይወት የመጠገን፥ የማደስ ኃይል እንዳለው ሁሉ፥

የመግደልና የማፍረስም ኃይል አለው። ከሰው አንደበት የሚወጣው ቃል ምን ዓይነት ኃይል እንዳለው የምንገነዘበው በህጻንነት ዘመናችን የሰማናቸው ክፉም ሆነ መልካም ቃላት፥ ከረጅም ዘመን በኋላም ፈጽሞ ከአዕምሮአችን ያልጠፉ መሆናቸውን ስናስብ እንደሆነ ቀደም ሲል ገልጸናል። እነዚያ የሰማናቸው ንግግሮች፥ በጥሩውም ሆነ በመጥፎ ሕይወታችንን ነክተውትና ቀርጸውት አልፈዋል።

ጥንት ኢትዮጵያውያን ወላጆች፥ ክፉ አነጋገራቸው በልጆቻቸው ሕይወት ውስጥ ሊያስከትል የሚችለውን ከፍተኛ ጉዳት ባለማወቅ፥ ውስጣቸውን ሰንጥቆ የሚገባ፥ ከአዕምሯቸው ፈጽሞ ሊጠፋ የማይችል የስድብና የርግማን ቃል ያወርዱባቸው ነበር። *"...ለምን እንደ ወን ድምህ ሉትሆንም? ወንድምህን እከሌን በተሸከምኩበት ማህጸኔ እን ተን የማትረባውን ተሸከምኩ?....ምነው በማሕጸኔ ውስጥ ውሃ ሆነህ በቀረህ!...የማትረባ!...ደደብ!...የወንድ አልሜ!...አንተ ሰው ትሆናለህ ብዬ አላምንም..."* በማለት በሙጥኝ ንግግራቸው እንዳይሞቱ እንዳ ይሽሩ አድርገው ክፉ ቃል ይወረውሩባቸው ነበር። ይህን ዓይነቱን ክፉ ቃል እየሰሙ ያደጉ፥ እንዳንዶቹ እልህ ይዟቸው የወላጆቻቸውን ስድብና ዕርግማን ለጥቅማቸው ያዋሉት እንዳሉ እናውቃለን። *"እና ትና አባቴ 'አትረባም! ዋጋ የለህም!' ብለውኛል፥ እኔ ደግሞ መርባቴ ንና ዋጋ ያለኝ መሆኔን ላሳያቸዋለሁ!"* በማለት እልህ ይዟቸው ቢኃ ይል በመሥራት ከፈለጉበት የኑሮ ደረጃ የደረሱ አሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ *"አባቴ ወይም እናቴ ሉትረባም ብለውኛልና፥ እውነታቸውን ነው! እኔ አልረባም! ዋጋ የለኝም"* ብለው የወላጆቻቸውን ክፉ ንግግር አምነው የተቀበሉ፥ ራሳቸውን ለማሻሻልም ሆነ ለማሳደግ ምንም ዓይነት ጥረት ባለማድረጋቸው ምክንያት፥ ሊደርሱ ከሚችሉበት የኑሮ ደረጃ ሳይደርሱ የቀሩም እንዳሉ ግልጽ ነው።

## 4. <u>ክፉ ምላስ የቆሰለውን፥ መልሳ ታቆስላለች</u>

ማንኛውም ሰው በሕይወቱ አልፎ አልፎ ችግር፣ መከራ፣ ትግ ልና ፈተና እንደሚያጋጥመው ሁሉ፥ እኔም በሕይወቴ ከምንጊዜውም የበለጠ መራራ ጽዋ የጠጣሁበት፣ ብዙ ዕንባ ያፈሰስኩበት አንድ ወቅት ነበር። ሁሉ ነገር ይበላሽብኝ ነበር። የያዝኩት የሚወድቅበት፥



የጀመርኩት የሚፈርስበት ጊዜ ነበር። በሕይወቴ "ይሆንልኛል" ብዬ የምጠብቀው ምንም በጎ ነገር አልነበረኝም። እንዲያውም ያልጠበቅ ኳቸው ችግሮች ላይ በላዩ እየተደራረቡ በቅርብ ጓደኛ የተከዳሁበት፥ በክፉ አለቃ የተንገበገብኩበት፥ በኑሮ ጥበት የተሰቃየሁበት፥ ክፉ ጊዜ ነበር። በአጠቃላይ ሕይወቴ መጠጊያም ሆነ ማረፊያ ፍጹም ያጣችበት፥ እግሮቼ እኔነቴን መሸከም አቅቷቸው ይንቀጠቀጡ ነበር። በዚያን ወቅት *"አይዞህ! ሁሉም ያልፋል!..."* ብሎ የሚያጽናናኝ ሰው ከምንጊዜውም የበለጠ የምፈልግበት ወቅት ነበር። ይሁን እንጂ፥ የሚያስፈልገኝን አጽናኝ የሆነ ቃል የሚሰጠኝ አንድም ሰው አልነበ ረኝም። ሌላው ቀርቶ እግዚአብሔርም ራሱ ሆን ብሎ ከእኔ የተደበቀ መስሎ የተሰማኝ ጊዜ ነበር።

በዚህ ሁኔታ ላይ እያለሁ አንድ ቀን ተላላኪዬ ከፖስታ ቤት የመጣ ደብዳቤ ሰጠኝ። ከመከፈቴ በፊት ከየትና ከማን እንደመጣ ለማወቅ አገላብጬ አየሁት። ፖስታው ላይ የላኪው ስምም ሆነ አድ ራሻ ስላልነበረበት በሁኔታው ተገርሜ፥ ከማን እንደተላከ ሳላውቅ ፖስታውን ከፍቼ ደብዳቤውን ማንበብ ጀመርኩ። ይሀን ደብዳቤ የጻፈልኝ ሰው፥ በቅርብ የሚያውቀኝ፥ የማልፍበትን መከራ ሁሉ በቅርብ የሚያውቅ ሰው መሆን አለበት አልኩ። የደብዳቤው አሳብ በአጭሩ፥ "አይ የሽማግሌያችን መከራ!... እስከ አሁን ከደረሰብህ መከራ ሁሉ የበለጠ ገና ብዙ መከራ ይደርስብሃል... ጠብቅ..." የሚል የዛቻና የማስፈራሪያ የሚመስል ቃል ነበር። ከእግዚአብሔር ጋር የተማከረ ይመስል "ገና ምኑን አየህ!" ይላል። በመከራዬ ደስ እንዳለው ከአጻጻፉ ተረዳሁ። ደብዳቤውን እያነበብኩ *"ምን ዓይነት ጨካኝ ሰው ነው? በሰው መከራ ለምን ደስ ይለዋል?"* ብዬ ራሴን ጠየቅሁ። መከ ራና ችግር ቀጥቅጦ ባቆሰለኝ ቁስል ላይ ዘይት በማፍሰስ ፈንታ አሲድ ነስንሶ የበለጠ አቃጠለኝ።

ይህን ዓይነቱን ደብዳቤ የጻፈ ሰው ምን ዓይነት ሰው ነው? ብላ ችሁ መጠየቃችሁ አይቀርም። የቤተ ክርስቲያን ሰው፥ ራሱን ክርስ ቲያን ብሎ የሚጠራ ሰው መሆኑን፥ እንዲሁም እኔው ራሴ ከማመ ልከበትና ከማገለግልበት ቤተ ክርስቲያን እንደሆነ አንዳንድ ደብዳ ቤው ላይ ባሠፈራቸው ቃላት መረዳት አላስቸገረኝም። "ምን ተሰ ማህ?" ብላችሁ ብትጠይቁኝ፥ የተሰማኝን በቃላት መግለጽ እንደማ

ልችል እነግራችኋለሁ። ሰውነቴ ደነገጠብኝ፥ ወረቀቱን የያዙት እጆቼ ይንቀጠቀጡ፥ ዐይናቼ ዕንባ ያፈሱ ነበር፥ እንዲሁም ትንፋሼ ቁርጥ፥ ቁርጥ ይል ነበር። *"ምን ያህል ብዘድለው ነው መከራዬና ችግሬ እንዲህ ደስ ሊያሰኘው የቻለው?"* ብዬ ራሴን ብጠይቅም፥ መልስ አላገኘሁለትም። ጠላቴ ነው፥ ጠበኛዬ ነው የምለው አንድም ሰው በወቅቱ አልነበረኝም። ከሁሉም ሰው ጋር በሰላም ለመኖር የም ፈልግ ሰው ነበርኩ። ቀደም ሲል ከደረሰብኝ መከራና ችግር የበለጠ፥ ያ ደብዳቤ ውስጤን ጎዳው። በወቅቱ ከደረሰብኝ ድንጋጤና ሀዘን እወጣለሁ ብዬ አልገመትኩም። ነገር ግን ጌታ ጸጋውን ሲሰጥ ይቻላ ልና፥ የአእምሮ ቁዘማ ሳይደርስብኝ አለፍኩት።

ያን ደብዳቤ በጌታ ፊት ይዤ ቀረብኩ። እጄንም እዚያ ደብዳቤ ላይ ጭኜ ዕንባዬን እያንጠባጠብኩ፥ ይህን ደብዳቤ በጻፈው ሰው ምን ያህል እንደተጎዳሁ ለእግዚአብሔር የውስጤን ገላልጬ ነገር ኩት። በዚያን ወቅት ከክርስቲያን ወንድሞቼም ሆነ እህቶቼ የጠበቅ ሁት የሚያጽናና፥ "አይዞህ! በርታ!" የሚል የማጽናኛ ቃል እንጂ፥ በቁስሌ ላይ አሲድ እንዲነሰንሱብኝ አልነበረም። በዚህ ምክንያት በልቤ ውስጥ መራራነት እንዳይፈጠር ጌታዬን ተማጠንኩት። ማንነቱን ስላልገለጸ፥ ያንን ደብዳቤ የጻፈውን ሰው ባላውቀውም፥ ጌታን *"አንተ ታውቀዋለህና አባክህን ባርከው፥ ማንነቱን ብትገልጥልኝ ደስ ይለኛ ነበር"* ብዬ ጸለይኩ። ይሁን እንጂ፥ ፈቃዱ ስላልነበረ አልገለጸ ልኝም። እስከ ዛሬም ማንነቱን አላውቀውም። ይሄ ሁኔታ ከተፈጠረ 31 ዓመት አልፎታል። የጻፈውን ሰው ባላውቀውም ይቅርታ አድር ጌለታለሁ። ይሁን እንጂ ያ ሰው የጎዳኝ፥ ጠባሳው ዛሬም አለ። ከአ ዕምሮዬ ፈጽሞ አይጠፋም። ያንን ደብዳቤ የጻፈውም ሰው የሚረ ሳው አይመስለኝም። ህሊናው ካልደነዘዘ በስተቀር በአዕምሮ ጸጸት ከእኔ የበለጠ እንደሚጨነቅ አምናለሁ። እግዚአብሔር ለእኔ የሰጠውን ዕድሜ ለእርሱም ሰጥቶት እንደሆነ፥ ባለፉት 31 ዓመታት እግዚአብ ሔር በሕይወቴ ያደረገውን ታላቅ ሥራ ማየቱ አይቀርም። ምን ይሰማው ይሆን? ትንቢቱ እንዳልሠራ ሲያይ ምን ይል ይሆን? አንድ ያላወቀው እውነት ቢኖር፥ ያ መከራና ችግር ከምወደው ጌታ ፊት ከማሸሽ ይልቅ፥ የበለጠ እየገፋ በጌታዬ እቅፍ ሥር የጣለኝ መሆኑን ነው። የዛሬውን እኔነቴን ከቀረጹትና ካስተካከሉት ሁኔታዎች መካ



ከል አንዱ ያ ደብዳቤ ነው። ሰይጣን በዚያ ክፉ ደብዳቤ እንድሰበር በት አስቦልኝ ነበር፥ ጌታ ግን ለበጎ እንድጠቀምበት ረዳኝ።

በአዕምሮም፥ በመንፈሳዊ ሕይወቴም አሁን ባለሁበት ደረጃ ስላ ልነበርኩ፥ "ምንም አይደለም!" ብዬ ንቄ መተው አልቻልኩም። ከዚህ የበለጠ የከፋ ነገር እንዳይደርስብኝ ጌታዬን ከምንጊዜውም የበለጠ ተማጠንኩት። የተማጠንኩትም ችግሩን ፈርቼ ሳይሆን፥ ሌሎቹም ሆኑ ያ ክፉ የሚመኝልኝ ሰው በእኔ ሀዘን ደስ እንዳይለው ብዬ ነው። የፈራሁት አልቀረም። ሁለተኛው ልጃችን ጉንጩ ምንም ነገር ሳይነ ካው እንዲሁ አበጠ። ሆስፒታል ስንወስደው ሀኪሙ መረመረውና "መተኛት አለበት" አለን። "ተመላልሰን እናሳክመው" ብለን ሀኪሙን ለመንነው። ይህን ያልነው ለገንዘቡ ሳይሆን፥ "ክፉ የሚመኙልን ሰዎች ይህን ሲሰሙ ደስ ይላቸዋል፥ መሳቂያ ያደርጉናል" ብለን ስለፈራን ነበር። ክርስቲያን መከራን ከሚፈራው የበለጠ እንዴት ክርስቲያኖችን ይፈራል? ክርስቲያኖችስ እንዴት የሰው መከራ ያስደስታቸዋል? በወቅቱ ሀኪሙ ጥያቄያችንን ስላልተቀበለ፥ ልጃችንን በድብቅ ሆስ ፒታል አስተኛነው። ብንደብቅም፥ እዚያ ሆስፒታል ክርስቲያን ነር ሶች ስለነበሩ ወሬው መዛመቱ አልቀረም። ይሁን እንጂ፥ ተመሳሳይ ደብዳቤ አልደረሰኝም።

ከዚህ ልምምዴ ያገኘሁት ትምህርት ክፉ ምላስ ጎጂ መሆኑን ብቻ ሳይሆን፥ ያለአግባብ ለሚገፉት፥ ለሚቆስሉትና ለሚደሙት፥ አጽናኝ ላጡት ወገኖቼ እንድራራና እንዳዝን ያደረገኝ መሆኑ ነው። እንደ እኔ አጽናኝ ያጡ፥ በመከራ ውስጥ የሚያልፉ አማኞች ስንት ይሆኑ? የሚያጽናና ቃል በመስማት ፈንታ የፍርድ ቃል ሰምተው ልባቸው የተሰበረ ስንቶች ይሆኑ? ያ ሰው የጠበቀው "ድሌን" ሳይ ሆን "ሽንፈቴን" ነበር። በዘመናት ያገኘኋቸውን መንፈሳዊ "ድሎች" ሲያይና ሲሰማ ምን ያህል ተበሳጭቶና አንጀቱ አርሮ እንደሆነ አላ ውቅም። ጌታ ሲጠራኝ "የአበባ ምንጣፍ አነጥፍላሃለሁና፥ ና! ተከተ ለኝ" ብሎ አልጠራኝም። የጠራኝ "መስቀሌን ተሸክመህ ተከተለኝ!" ብሎ ነው። ስለሆነም የክርስትና ጉዞዬ መስቀል የሌለበት አይደለም። በብዙ ትግልና ፍልሚያ ውስጥ አልፌአለሁ። ቢሆንም እዚህ የደረስ ኩት መራራ ጽዋ እየጠጣሁ ብቻ ሳይሆን፥ ከመስቀሉ ጋር የበረከቱ ንም ጽዋ አብሬ እየጠጣሁ መሆኑን መግለጽ እወዳለሁ። ምላስ መግ

ደል ብቻ ሳይሆን፥ መረመሰም ይችላል። ተስፋ ግስቶረጥ ብቻ ሳይ ሆን በተስፋም ይሞላል።

አንድ ጊዜ የታወቀ የሕግ መምህር የነበረው ገማሊል ከአሽከሮቹ መካከል አንዱን ጠርቶ "ዝሪያ ሂድና በጣም ጥሩ ነው ብለህ የም ታስበውን ምግብ ግዛና አምጣልኝ" ብሎ አዘዘው። አሽከሩም የበሬ ምላስ ይዞለት መጣ። እንደገና ጠራውና "ወደ ዝሪያ አሁንም ሂድና መጥፎ ነው ብለህ የምትገምተውን ምግብ ግዛና አምጣልኝ" አለው። አሽከሩም ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ገበያ ሄዶ በድጋሚ የበሬ ምላስ ይዞለት መጣ። ይህን ያደረገበትን ምክንያት ሲያስረዳ፥ "ጌታዬ ምላስ ጥሩም ሆነ መጥፎ መሆን ይችላል። ጥሩ ከሆነ፥ ከምላስ የተሻለ ሌላ ምን ጥሩ ምግብ ይገኛል? እንዲሁም መጥፎ ከሆነ፥ ከምላስ የከፉ ሌላ ምን ምግብ ይገኛል?" በማለት ሀሳቡን ገለጸ። ከአንደበታችን የሚወጣው ቃል ገንቢ ወይም አፍራሽ ሊሆን ይችላል። ወሳኙ ግን የልባችን ሁኔታ ነው። የጥንት ሰዎች "ጥሩ ንግግር" መድኃኒት እንደሆነ ይና ገራል። ልባችን ሲያዝንና ስሜታችን ሲጎዳ፥ ከትክክለኛ ሰው ልብ የወጣ ትክክለኛ ቃል ሁኔታችንን ሊፈውስ ይችላል። "ያለ ምንታቄ የተነገረ ቃል እንደ ሰይፍ ያቆስላል፥ በጥበብ የተነገረ ቃል ግን ይፈ ውሳል" ይላል (ምሳሌ 12፥18)። ኢዮብ ሊያጽናኑት በመጡት ጓደኞቹ ንግግር ምን ያህል እንደተጎዳ ሲገልጽ፥ "ነፍሴን የምትዘንዙ፥ በቃልስ የምታደቋኝ እስከ መቼ ነው? ይኸው ስትሰደቡኝ አሥር ጊዜ ነው፥ ሲታችኩኝም አላፈራችሁም" ይላል (ኢዮብ 19፥ 2-3)። አንድ ጸሀፊ የምላስን አደገኛነት ሲገልጽ፥ "ምላስ መንጋጋ ሥር እንደተቀበረ ፈንጂ (dynamite) ስለሆነ በጥንቃቄ መያዝ ይገባዋል" አለ። ብዙ ሺ ሕዝብ ያለቀበት ጦርነት የተጫረው ትንሽ በሆነችው ምላስ ነው። በምላስ ምክንያት የብዙዎች ትዳር (ቤት) ፈርሷል፥ ብዙ ሕጻናት ያለ ወላጆች ቀርተዋል፥ የሚዋደዱ ጓደኞች ተጋጭተው ተለያይተዋል፥ ብዙዎች ንብረታቸው ጠፍቶ ያለመጠጊያ ቀርተዋል። "ምላስ ትንሽ የሰውል ክፍል ስትሆን በታላላቅ ነገሮች ትመካለች፥ ትልቅ ጫካ የሚቃጠለው በትንሽ እሳት ነው። ምላስም እንደ እሳት ናት፥ ምላስ በሰውል ክፍሉ ቻችን መካከል የምትገኝ ክፉ ዓለም ናት፥ ሥጋችንንም ሁሉ ታረከ ሳለች፥ እንደ ገሃነመ እሳት ሰውነታችንን ሁሉ ታቃጥላለች" ይላል (ያዕ. 3፥5-6)።



## 5. ክፉ ምላስ መርዛም ናት

ሐዋርያው ያዕቆብ ምላስን ሲገልጽ፥ "...የሚገድል መርዝ የሞላ ባትና ፈረፍት የሌላት ክፉ ነገር ናት.." ይላል (ያዕ. 3፥8)። ሀኪሞች እንደሚገልጹት አንዳንድ የእፍ በሽታ መጥፎ የሆነ የአፍ ጠረን ወይም ሽታ ያመጣል ይላሉ። ኃጢአትም ልክ እንደዚሁ ነው። ከኃ ጢአተኛ ልብ የኃጢአት ንግግር ይፈልቃል። ጳውሎስ ለሮሜ ክርስ ቲያኖች በጻፈው መልዕክቱ ይህን ጥሩ አድርጎ ገልጾታል። "ሰውን የሚጎዳ ክፉ ቃል ለመናገር አፋቸው እንደ መቃብር የተከፈተ ነው፥ በምላሳቸው ያታልላሉ፥ የከንፈራቸውም ንግግር እንደ እባብ መርዝ የሚጎዳ ነው፥ አፋቸው በመራራ እርግማን የተሞላ ነው" (ሮሚ 3፥ 13-14) ይላል። ጳውሎስ "አፋቸው እንደተከፈተ መቃብር ነው" ሲል፥ የተከፈተ መቃብር የሞት ሽታ እንዳለው ሁሉ፥ ምላሳችንም ከውስጥ ያለውን መንፈሳዊ ሕይወታችንን ይገልጻል። ጤናማ የሆነ መንፈሳዊ ሕይወት ከሌለን ከአፋችን የሚወጣው ቃል ጎጂነት ያለው ነው። ልክ መናገር ስንጀምር ማንነታችን ይገለጻል። "ዝናፍ ዝም ቢልና አፉን ቢዘጋ ጠቢብና አስተዋይ ሊመስል ይችላል" ይላል (ምሳሌ 17፥28)። ሰው መጥፎ ንግግር ልማዱ ከሆነ፥ ችግሩ ከምላሱ ሳይሆን የልቡ ትክክለኛ አለመሆን ነው።

በአንደበታቸው ስተው ሌሎችን የሚጎዱ ዓለማውያን ብቻ ሳይ ሆኑ አማኞችም ጭምር ናቸው። ይሄም በእኛ ዘመን ብቻ ሳይሆን በጥንት አማኞችም መካከል ይታይ የነበረ ትልቅ ድክመት ነው። የጥንት ቤተ ክርስቲያን መሪዎች የምላስ ጦርነት እርስ በርሳቸው ያካሂዱ እንደነበረ ታሪክ ጸሀፊዎች ይናገራሉ። ፊልፕ ሰክፍ የተባለው ታሪክ ጸሀፊ ስለ ማርቲን ሉተር ሲጽፍ፥ "ማርቲን ሉተር ጽሁፍ ጦርነት የሚጭር የመርዝ ጢስ ነበር። ተቃዋሚ መስለው የሚታዩትን ሁሉ ምሀረት የሌለው የቃላት ጥይት ያወርድባቸው ነበር" አለ። ማርቲን ሉተር ለብዙ ጊዜ ሲያደንቀው የነበረው ኢራስመስ በተጣላው ጊዜ "በዓለም ውስጥ ካሉት አደገኛ እባቦች መካከል መርዘኛው ኢራ ስመስ ነው፥ ሙልጭልጭና ድብቅ ከሃዲ ነው" ሲል ተናገረ። የታወ ቀው የሥነ መለኮት ምሁር የነበረው አሰክር ኮማን "ኤፕሮስ" በሚለው መጽሐፉ "ሰማዕታት ጳውሎስና ጴጥሮስ ሳይቀሩ ለሕይወታቸው መጥፊያ ምክንያት ራሳቸውን ከርስቲያን ብለው የሚጠሩ የርም

*ቤተ ክርስቲያን አባል የነበሩ አማኖች በቅናትና በምቀኝነት የሰነዘሩ ባቸው ቃላት ነው። ጠባቸው እጅግ ከፍተኛ ስለነበረ ሌላውን አማኝ 'የመንግሥት ጠላት ነው' በማለት የክርስትናን እምነት ለሚቃወሙ ሰዎች አሳልፈው ይሰጡ ነበር" አለ። በኮልማን አጻጻፍ ብዙ አማኖች ለአንበሳ የተጣሉት፥ በኔሮ ዘመን በእሳት የተቃጠሉት፥ አንዳንድ ክርስቲያኖች እያጋለጡ ለገዳይ በመስጠታቸው ነበር። ያልታረመ አንደበት የእግዚአብሔርን አገልጋዮች ከአገልግሎታቸው እንዲሸሹ አድርጓል። ጋብቻን አፍርሶ የብዙዎችን ልብ ሰብሯል። መጽሐፍ ቅዱስም ክፉ አንደበት የሚያስከትለውን ጉዳት ሲገልጽ "ክፉ ሰዎች ሌሎችን የሚጎዱበትን መንገድ ያሰላሉ፥ ንግግራቸው እንደ እሳት የሚያቃጥል ነው፥ ክፉ ሰዎች ሐሜት ያሰራጫሉ፥ ሁለትን በማነሳሳት በፍቅር የተሳሰሩትን ወዳጆች ይለያያሉ" ይላል (ምሳሌ 16፥27-28)።*

አንደበት የማቁሰል ኃይል እንዳለው ሁሉ የመፈወስም ኃይል እንዳለው ደጋግመን ገልጸናል። መጽሐፍ ቅዱስም "የደግ ሰው ንግግር የሕይወት ምንጭ ነው" ይላል (ምሳሌ 10፥11)። ከአንደበታችን የሚወጣው ቃል ጎጂ ወይም ጠቃሚ እንዲሆን ወሳኙ የልባችን አቋም እንደሆነ ከላይ ያየነው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ያረጋግጥልናል። ልቡ በበጉ ደም ታጥቦ የነጻ፥ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ አማኝ ከአን ደበቱ የፈውስ ቃል እንጂ ሌሎችን የሚገድልና የሚያጠፋ ቃል መውጣት የለበትም። ክፉ ቃል ተናግረውን ያልረሳናቸው ሰዎች እንዳሉ ሁሉ በጎ ቃል ተናግረውን ሁልጊዜ የምናስታውሳቸው ሰዎ ችም አሉን። ስለዚህ በአንደበታችን በጎ የሆነውን በመፈጸም ሌሎች በበጎ እንዲያስታውሱን ይሁን እንጂ ንግግራችን በሌላው ሰው ሕይ ወት ውስጥ ጠባሳን የሚተው እንዳይሆን እንጠንቀቅ። ይህን ማለት ወዳጃችን ሲስት ዝም እንለዋለን ማለት አይደለም። ወይም ስንስት በፍቅር የሚያርመንን አንቀበልም ማለት አይደለም። *"ተገቢውን ቃል በተገቢው ቦታ መናገር እጅግ ያስደስታል"* ይላል (ምሳሌ 15፥23)። እርማት በሚያስፈልገው ወቅት ዝም ማለት ወዳጅን መጉዳት እንጂ መጥቀም አይሆንም። መጽሐፍ ቅዱስም ይህንን ያረጋግጥልናል። *"ነውን በስውር አወድሃለሁ ማለት ብቻ አይበቃም፥ በሚሳሳትበት ጊዜ በግልጥ መገሰጽም ይገባል"* ይላል (ምሳሌ 27፥5)። አንደበታችን በሌላው ሰው ሕይወት ጥሩ ወይንም መጥፎ ተጽእኖ ሊያደርስ ይች ላልና የምንናገረውን መምረጥ ይገባናል።



# 6. ክፉ ምላስ በማጉረምረም የተሞላች ናት

አንዳንድ ክርስቲያኖች ውስጣቸው በማጉረምረምና በማማረር የተሞላ ነው። በሆነላቸው በመደሰት ፈንታ ባልሆነላቸው ነገር ላይ ሲያማርሩ ይሰማሉ። ብዙ የተደረገላቸውን ረስተው፥ ባልተደረገላቸው ወይም ባልሆነላቸው አንድ ነገር በማዘን ሲያማርሩ የታያሉ። ስላገ ኙትና ስለሆነላቸው ነገር "ተመስገን" በማለት ፈንታ፥ "ምነው ይሄ ነገር በኖረኝ ኖሮ!" ይላሉ። አዲስ ቤት ሠርተው ሲገቡ፥ "ጌታ ሆይ ተመስገን!" በማለት ፈንታ፥ "ምነው አዲስ የቤት ዕቃ በኖረን" በማለት ያጉረመርማሉ። ስለ አንዲት አሮጊት ሴት የተነገረ አንድ ታሪክ አለ። እኚህ አሮጊት ባሕር ዳር ከባላቸው ጋር ሆነው ሲዝናኑ፥ ድን ገት ማዕበል መጥቶ ባላቸውን ካጠገባቸው ጠርጎ ይዞባቸው ሄደ። በሁኔታው ተደናግጠው ለባላቸው ተንበርክከው መጸለይ ጀመሩ። በጸሎት ላይ እያሉ፥ ማዕበሉ ባላቸውን አጠገባቸው ገፍቶ ጥሎላቸው በመደነቅ ሁኔታውን ካዩ በኋላ፥ "ጌታ ሆይ! ባሌን ስላዳንከው አመሰ ግንሃለሁ፥ ግን አርጎት የነበረው ባርኔጣ በራሱ ላይ የለም" አሉ ይባላል። የማጉረምረም ትልቁ ምክንያት በራሳችን፥ በአካባቢው ሁኔታና እንዲሁም በሰዎች ላይ እርካታ በማጣታችን ይሆናል። ስለሆነም ሁልጊዜ የማማረር ድምጽ እናሰማለን።

የምናማርርበት ሌላው ምክንያት ራሳችንን ከሌሎች ጋር ስለም ናወዳድር ነው። በሁኔታችን ደስ ሳይለን ሲቀር፥ ከእኛ የተሻለ ነው ብለን የምናስበውን ሰው እንፈልግና ራሳችንን ከዚያ ሰው ጋር ማነ ጻጸር እንጀምራለን። የሚገርመው የምናወዳድረው ደካማ የሆንበትን ጎን፥ ከሌሎች ብርቱ ጎን ጋር ነው። በዚህ ዓይነት ከሆነ፥ ሁልጊዜ የምናየው የማንረባ መሆናችንን ነው። መገንዘብ ያለብን እውነት ቢኖር፥ ሰው በሁሉም አቅጣጫ ብርቱ መሆን የማይችል መሆኑ ነው። ጥሩ መጻፍ የማይችል፥ ጥሩ ተናጋሪ ሊሆን ይችላል። ጥሩ ጸሀፊዎች ሆንን፥ ጥሩ ተናጋሪዎች ላንሆን እንችላለን። ታዲያ ራሳች ንን ከጥሩ ተናጋሪዎች ጋር ስናወዳድር ከድካማችን በስተቀር ብርታ ታችንን ማየት አይሆንልንም። እግዚአብሔር እኔን የፈጠረኝ "መለሰን" እንድሆን ነው። ሌላ ሰው እንድሆን ከፈለገ፥ ሌላ ሰው አድርጎ ይሠ ራኝ ነበር። ስለሆነም ራሴን መሆን ትቼ ሌላውን ለመሆን ስሞክር መሆን ባለመቻሌ ምክንያት እግዚአብሔርን "ስትሠራኝ ትክክል አድርገህ አልሠራኸኝም" ማለቴ ነው። ይህም እግዚአብሔርን ያስቀ

ይመጣል። ራሳችንን ከሌላው ጋር ማወዳደር መጽሐፍ ቅዱሳዊ እን ዳልሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። *"ይሁን እንጂ፥ ራሳቸውን ከሚ ያመሰግኑ ከአንዳንድ ሰዎች ጋር ራሳችንን ልናወዳድር ወይም ራሳ ችንን ልናንጻጸር አንደፍርምና እነርሱ ግን ራሳቸውን ከራሳቸው ጋር በማመዛዘናቸውና ራሳቸውንም ከራሳቸው ጋር በማወዳደራቸው አስተ ዋዮች አይደሉም"* ይላል (2 ቆሮ. 10፥12)። የእግዚአብሔር ቃል ራሳ ችንን ከሌሎች ከማወዳደር ይልቅ፥ *"ባትሕትና ተሞልታችሁ ሌሎች ሰዎች ከእናንተ እንደሚሻሉ አድርጋችሁ ቁጠሩ እንጂ ወገን በመለየ ትና በራስ ወዳድነት ወይም ያለ አኔ ግን አለ በሚል ትምክሕት ምንም ነገር አታድርጉ"* በማለት ይመክረናል (ፊልጵ. 2፥3)።

ሁልጊዜ ከማማረርና ከማጉረምረም በስተቀር ከአፋቸው ጨርሶ የምሰጋና ቃል የማይወጣቸው ክርስቲያኖች አሉ። ምንም ያህል ቢኖ ራቸው የሚረኩ አይደሉም። እንደነዚህ ዓይነቶቹ የራሳቸውን ደስታ አጥተው አብረዋቸው ለሚኖሩት ሰዎችም ሲአል ይሆናሉ። በማማረ ርና በማጉረምረም የተሞሉ ሰዎች ምንጊዜም ቢሆን የሚያማርሩበት ወይም የሚያጉረመርሙበት ምክንያት አያጡም። አንድ ጊዜ በአንድ ከተማ ውስጥ በማማረሩ በጣም የታወቀ አንድ ገበሬ ነበር። ከምንጊ ዜውም የበለጠ ገበሬዎች ጥሩ ምርት ያመረቱበት ዓመት ነበር። ከእርሻቸው ያገኙት ፍሬ በጣም ጥሩ ነበር። ድንቾቻቸው በጣም ትልልቅ ነበሩ። የአካባቢው ገበሬዎች "ያ አጉረምራሚ ሰው ለማጉረ ምረም ምንም ዓይነት ምክንያት የማያገኝበት ዘመ" ቢኖር ይሄ ዓመት ነው" በማለት ሄደው "ስለ ዘንድሮ ጥሩ የመከር ጊዜ ምን ትላለህ?" ብለው ጠየቁት። እርሱም "አሳማዎቼን የምመግብበት ትና ንሽ ድንች የት አለ?" በማለት አሁንም ሁኔታውን አጨልሞ መልስ ሰጣቸው። ምክንያት እየፈለጉ የሚያማርሩና የሚያጉረመርሙ ሰዎች ግን ይወዳል? ሁልጊዜ "የማማረርና የማጉረምረም ቃል" የሚያሰሙ ሰዎች በሕይወታቸው እርካታ ያጡ እንደሆኑ ተመልክተናል። እንዲህ ዓይነቶቹ መንፈሥት ሰማይም እንኳን ቢሆን፥ ቆረቆረን፣ አልተመቸ ንም እንደሚሉ የታወቀ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ በሕይወቱ የተማ ረውን ትልቅ ነገር ሲገልጽ *"ስለዚህ ማግኘትንም ሆነ ማጣትን ዐው ቃለሁ፥ በማንኛውም ቦታ ሆነ በየትኛውም ጊዜ የመጥገብንና የመራ ብን፥ የማግኘትንና የማጣትን ምስጢር ተምሬአለሁ"* ይላል (ፊልጵ. 4፥11-12)።



# ምዕራፍ ፭

# ነቃፊ ምላስ

*"ሳያስብ በችኮላ ከሚናገር ሰው ይልቅ*
*አዕምሮ የጎደለው ሰነፍ የተሻለ ተስፋ አለው።"*
*ምሳ. 29፥20*

የክርስትና ሕይወት አንድ ቦታ የሚቆም ሳይሆን፥ ዕድገት ያለበት ሕይወት ነው። እግዚአብሔር የጠራን እንድናድግ ነው። *"ይልቅስ በጌታችንና በአዳኛችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና እርሱንም በማወቅ እደጉ..."* ይላል (2 ጴጥ. 3፥18)። ዕድገታችንም በግል፥ ከእግዚአብ ሔርን እንዲሁም ከሌሎች ሰዎች ጋር በሚኖረን ግንኙነት ነው። ዕድገታችን ምን ዓይነት እንደሆነ ሐዋርያው ጳውሎስ ሲገልጽ፥ *"እውነትን በፍቅር እየተናገርን ራስ የሆነውን ክርስቶስን ለመምሰል በሁሉ ነገር እናድጋለን"* (ኤፌ. 4፥15) ይላል። የዕድገታችንም ፈጻሚ መንፈስ ቅዱስ ነው። *"የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ደግነት፣ ቸርነት፣ ታማኝነት፣ ገርነት፣ ራስን መግዛት ነው..."* ይላል (ገላት. 5፥22-23)። ሲጋዊው የሕይወታችን ዕድገት ግብዂያ አለው። መንፈሳዊው ዕድገታችን ግን እንደ ሥጋ ዊው ዕድገታችን ግብዂያ የለውም። በመንፈሳዊ ሕይወታችን ባደ